# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 047 ጥቅምት 17 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


# “አሸባሪው ትሕነግ በግብርና ሥራ ወቅት ጦርነት የሚከፍተው የሀገሪቷን ኢኮኖሚ በማዳከም የውጭ ኃይሎች ጥገኛ ለማድረግ ነው”

\- አምባሳደር ድሪባ ኩማ
የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር



**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ትሕነግ የግብርና ሥራ ወቅቶችን እየጠበቀ ተደጋጋሚ ጦርነት የሚከፍተው በጸረ ሕዝብ ባህሪው ሀገርን በማዳከም ለጠላት አጋልጦ ለመስጠትና የውጭ ኃይሎች ጥገኛ ለማድረግ ከሚያራምደው የኢኮኖሚ አሻጥር የተነሳ ነው ሲሉ የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ድሪባ ኩማ ገለጹ።

አምባሳደር ድሪባ ኩማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አሸባሪው ትሕነግ የምርት ጊዜን ጠብቆ ሀገርን በኢኮኖሚ ለማዳከምና ተረጂ በማድረግ ለጠላት አጋልጦ ለመስጠት ባለው የጸረ ሕዝብ ባህሪው ነው።

ቡድኑ የሀገርን ኢኮኖሚ ለማዳከም ለጠላት አጋልጦ ለመስጠት ከምን ጊዜውም በላይ አትኩሮ እየሠራ ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር በማበር የሀገር ክህደት ወንጀል የፈጸመው ንጹሓንን በመጨፍጨፍና ንብረት በማውደም ነው ብለዋል።

በአማራና አፋር ክልሎች በወረራ በገባበት ወቅትም ንጹሓንን በጅምላ ከመረሸን ባለፈ ምንም አይነት የፖለቲካ ተሳትፎ የሌላቸው ግለሰቦችን ንብረት በመዝረፍና በማውደም የሀገር ጠላት መሆኑን በአደባባይ አሳይቷል ያሉት አምባሳደሩ፤ መንግሥት በችግር ውስጥ ሆኖ ያሳካውን የእርሻ ሥራና የኢኮኖሚ ልዕልና በማደናቀፍ

“አሸባሪው ትሕነግ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# “የዜጎች ሰብዓዊ እርዳታም ሆነ ጥበቃ ለድርድር አይቀርብም”

\- ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር)
የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የዜጎች ሰብዓዊ እርዳታም ሆነ ጥበቃ ለድርድር እንደማይቀርብ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር) አስታወቁ።

ሚኒስትሩ የኢትዮጵያ መንግሥት የዜጎችን ደኅንነት ለማስጠበቅና የሰብዓዊ ዕርዳታ እንዲሁም የመሠረታዊ አገልግሎት አቅርቦትን ለማረጋገጥ ሕገ መንግሥታዊ ተልዕኮውን ለመወጣት ቁርጠኛ መሆኑን አስታውቀዋል።

የትግራይ ሕዝብ ሰብዓዊ እርዳታም ሆነ ጥበቃ

“የዜጎች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የውጭ ኃይሎች አሸባሪውን ሕወሓት የሚደግፉት በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ አድራጊ ፈጣሪ ለመሆን ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የውጭ ኃይሎች አሸባሪውን ሕወሓት እየደገፉ ኢትዮጵያ ላይ ተፅዕኖ የሚያደርጉት በሀገሪቱም ሆነ በቀጣናው አዛዥ እና ናዛዥ ሆነው መቀጠል ስለሚፈልጉ መሆኑን አርቲስት ደበበ እሸቱ ገለጹ።

አርቲስት ደበበ እሸቱ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ምዕራባውያን በኢትዮጵያ የሚፈልጉት አሜን ብሎ ትዕዛዝ የሚፈፅምላቸው መንግሥት ነው። አሸባሪውን ሕወሓትን እየደገፉ ኢትዮጵያ ላይ ተፅዕኖ እያደረጉ ያሉትም በዚህ ምክንያት ነው።

እነዚህ ኃይሎች ኢትዮጵያ ካለችበት ፖለቲካዊ ሁኔታና ስትራቴጂካዊ አቀማመጥ የተነሳ አሸባሪውን ሕወሓት ደግፈው ወደ ሥልጣን በማምጣት በሀገሪቱም ሆነ በአፍሪካ ቀንድ አዛዥ እና ናዛዥ ሆነው መቀጠል ይፈልጋሉ።

ኢትዮጵያ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጠ እና ለሕዝቡ መልስ የሚሰጥ መንግሥት አላት ያሉት አርቲስት ደበበ፤ በኢትዮጵያ ያለው መንግሥት ለየትኛውም የውጪ ጣልቃ ገብነት እጁ የማይጠመዘዝ መሆኑን አመላክተዋል። በዚህ ምክንያትም በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ እንደፈለጉ መሆን የሚፈልጉ አንዳንድ የውጭ ኃይሎች ለራሳቸው ፍላጎት የሚታዘዘውን አሸባሪውን ሕወሓት ወደ ሥልጣን ለመመለስ እየሠሩ እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

አሸባሪው ሕወሓት ለኢትዮጵያ ሆነ ለአፍሪካ ቀንድ



ብሎም ለዓለም አቀፍ ሰላም ስጋት በመሆኑ እነዚህ የውጭ ኃይሎች ለእውነት ቢቆሙ ቡድኑን መደገፍ እንደሌለባቸው የተናገሩት አርቲስት ደበበ፤ በኢትዮጵያ ላለው እኩይ ተግባር ሁሉ መንስዔ የሆነውን ወያኔን መደገፍ ተገቢነት የለውም ሲሉ አስረድተዋል።

የምሥራቅ አፍሪካ ሰላም መጥፋት ለሌላውም ዓለም ከፍተኛ ጉዳት ነው ያሉት አርቲስት ደበበ፤ በመሆኑም አሸባሪው ሕወሓትን የሚደግፉ እና በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ የሚገቡ ኃይሎች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ አሳስበዋል።

እኛ ኢትዮጵያውያን የነፃነት ዜጎች ነን ያሉት አርቲስቱ፤ ከመላው አውሮፓ፣ አሜሪካ እና ከሌሎቹ በፊት ኢትዮጵያ ግዛት እንደነበራት በማስታወስ በሃይማኖት፣ በቋንቋና በሕግ የተዋቀረ መንግሥት የነበራት ሀገር በመሆኗ ይህችን

የውጭ ኃይሎች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# በአሸባሪው ሕወሓት የወደሙ የኤሌክትሪክ መሠረተ-ልማቶች ጥገና በአንድ ወር ውስጥ ይጠናቀቃል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በአሸባሪው ሕወሓት በአማራ እና በአፋር ክልሎች ውስጥ ውድመት የደረሰባቸው የኤሌክትሪክ መሠረተ-ልማቶች ጥገና በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል ሲል የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አሳወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሞገስ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሰሜን ኢትዮጵያ በተካሄደው ጦርነት በሽብር ቡድኑ ውድመት የደረሰባቸው የኤሌክትሪክ መሠረተ-ልማት ጥገና እየተካሄደ ይገኛል፡፡

ሥፍራዎቹ ከሽብር ቡድኑ መላቀቃቸውን ተከትሎ

በአሸባሪው ሕወሓት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# በሦስት ወራት ወደ ውጭ ከተላከው ቡና ከ 426 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኘ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ ከ20 ሺህ ቶን በላይ ቡና ወደተለያዩ የዓለም ሀገራት በመላክ ከ426 ነጥብ 15 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘቱን የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን አስታወቀ።

ባለሥልጣኑ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ፣ ከሐምሌ 2014 ዓ.ም ጀምሮ በሶስት ወራት ውስጥ 25 ሺህ 853 ነጥብ 43 ቶን ቡና ለዓለም ገበያ በማቅረብ 122 ነጥብ 94 የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት አቅዶ 20 ሺህ 438 ነጥብ 37 ቶን ቡና ወደ ዉጭ በመላክ 426 ነጥብ 15 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ አግኝቷል።

ይህም ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ የሦስት ወራት የኤክስፖርት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር በመጠን ቅናሽ ቢኖረውም በገቢ ግን 27 ነጥብ 3 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ጭማሪ ማሳየቱ የተገለጸ ሲሆን የአፈጻጸም እድገቱም 30 ነጥብ 59 በመቶ መሆኑ መረጃው ያመለክታል።

በበጀት ዓመቱ ሦስት ወራት የተላከው ቡና በመዳረሻ ሀገራትና በገቢ መጠን ሲታይ ጀርመን 14ሺህ 934 ነጥብ 75 ቶን ወደ ውጭ ከተላከው ከጠቅላላው የቡና ምርት 21 በመቶ ድርሻ በመግዛት፣ 72 ነጥብ 05 የአሜሪካን ዶላር ገቢ በማመንጨት ከጠቅላላው ገቢ አንጻር 17 በመቶ ድርሻ በመያዝ ቀዳሚ ስፍራ ላይ መሆኗን በመረጃው ተገልጿል።

በተመሳሳይ መልኩ ወደ ሳዑዲ ዓረቢያ የተላከው የቡና ምርት 8 ሺህ 991 ነጥብ 94 ቶን ሲሆን ወደ ውጭ ከተላከው ከጠቅላላ የቡና መጠን 13 በመቶ ድርሻ እንደሚሸፍን መረጃው ጠቅሶ፣ ከገቢ አንጻር ደግሞ 45 ነጥብ 54 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የተገኘበት ሲሆን ከጠቅላላው ገቢ 11 በመቶ ድርሻ እንዳለው ተጠቁሟል።

በሦስት ወራት ወደ ውጭ ከተላከው ቡና ቤልጅየም 6ሺህ 98 ነጥብ 16 ቶን በመግዛት ከጠቅላላው መጠን 10 በመቶ ድርሻ ያላት ሲሆን ገቢ ከማመንጨት አኳያ ደግሞ መጠን ደግሞ 44 ነጥብ 56 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በማመንጨት ከጠቅላላው ገቢ 11 በመቶ ድርሻ በማበርከት 3ኛ ደረጃ መያዟን ከመረጃ ለመረዳት ተችሏል።

የተቀሩት በ2015 ዓ.ም በገቢ ቅደም ተከተል አሜሪካ፣ ዩናይትድ አረብ ኤሜሬትስ፣ ደቡብ ኮሪያ፣ቻይና ፣ ጃፓን ፣ ጣሊያን እና ፈረንሣይ በቅደም ተከተል ከ4ኛ እስከ 10ኛ ደረጃ ሲይዙ በጥቅሉ አስሩ ሀገራት በሦስት ወር ውስጥ ወደ ውጭ ከተላከው ቡና በመጠንም ሆነ በገቢ ደረጃ 82 በመቶ ድርሻ እንዳላቸው ባለሥልጣኑ አስታውቋል።

እንደ ባለሥልጣኑ ማብራሪያ፣ ወደ አስሩ ዋና መዳረሻ ሀገራት የተላከ ቡናና የገቢ መጠኑ ከ2014 አፈፃፀም ጋር ሲነጻጸር በመጠን 17 በመቶ ቅናሽ ቢያሳይም በገቢ 30 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል።

በ2015 በጀት ዓመት የሦስት ወራት ወደ ውጭ የተላከው ቡና በዓይነት ሲታይ ሲዳማ 18 ሺህ 815 ነጥብ 54 ቶን ሲሆን ከጠቅላላው መጠን 26 በመቶ ድርሻ ሲይዝ፣ 118 ነጥብ 33 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በማስገኘት ከጠቅላላው ገቢ 29 በመቶ ድርሻ መያዝ ቀዳሚ ደረጃ ላይ መሆኑን ያመላከተው መግለጫው፤ የነቀምት ቡና ደግሞ 16 ሺህ 705 ነጥብ 99 ቶን ሲሆን ከጠቅላላው መጠን 23 በመቶ ድርሻ በመያዝ፣ በገቢ ደረጃ 60 ነጥብ 73 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ በማስገኘት ከጠቅላላው ገቢ በ18 በመቶ ድርሻ 2ኛ ደረጃ ላይ መሆኑን አስታውቋል።

ወደ ውጭ የተላከው የይርጋጨፌ ቡና 8ሺህ 679 ነጥብ 95 ቶን ሲሆን ከጠቅላላው መጠን 12 በመቶ ድርሻ እና በገቢው ደግሞ 68 ነጥብ 2 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ በማስገኘት ከጠቅላላው ገቢ 16 በመቶ ድርሻን በመያዝ 3ኛ ደረጃ ሲይዝ፤ የቀሩት ስድስቱ የቡና ዓይነቶች ደግሞ ከጠቅላላው መጠን 89 በመቶ የሚሸፍኑ ሲሆን በገቢ ደረጃ 89 በመቶ ድርሻ አላቸው።

# የልዩ ተሰጥዖ ባለቤቶች

ጌትነት ምህረቴ




ባለ ሶስት እግር ተሽከርካሪ መኪናዋ በአንድ ሊትር ናፍጣ 27 ኪሎ ሜትር ድረስ ትሄዳለች።በአንድ ሰዓት ከ55 እስከ 63 ኪሎ ሜትር የመሄድ አቅም አላት። የንፋስ፤የእጅና የእግር ሦስት አይነት ፍሬን አላት። ይችን ተሽከርካሪ የሠራት ወጣት ከድር ረሽድ ሲሆን ተሽከርካሪዋ ፈርጀ ብዙ አገልግሎት የምትሰጥ ናት፡

ወጣት ከድር የምስራቅ ሐረርጌ የጭናቅሰን ወረዳ የቆጨር ቀበሌ ነዋሪ ሲሆን በመካኒካል ኢንጂነሪንግ ዲግሪውን አግኝቷል፤ በሙያውም 12 ዓመታት በላይ የሥራ ልምድ አለው። የአካባቢውን የውሃ ችግር የምታቃልል የውሃ መያዣ ያላት ባለ ሦስት እግር ተሽከርካሪ በመሥራት ለአገልግሎት ማብቃቱን ይናገራል።

ካሉኝ አምስት የፈጠራ ሀሳቦች ውስጥ ለውድድር ይዤው የቀረብኩት አንዱን ብቻ ነው የሚለው ወጣት ከድር፤ ባለ ሶስት እግር ቦቴ መኪና አስር አገልግሎት እንደምትሰጥ በተግባር አሳይቷል።ከእነዚህ አገልግሎቶች መካከልም አስፓልት መንገድ ማጠብ፣ውሃ በሌለባቸው አካባቢዎች ውሃ እስከ ቤት ድረስ የማቅረብ አገልግሎት፣መኪናዎችን ማጠብ እንደሚገኙበት ጠቅሷል።

ተሽከርካሪዋ ስድስት መቶ ሊትር ውሃ የመያዝ አቅም እንዳላት የሚገልጸው ወጣቱ፤በራሴ ፈጠራ ሀሳብ ተነስቼ የሠራኋት ተሽከርካሪ አሁን ብዙ አገልግሎቶችን ለኅብረተሰቡ እየሰጠሁ ገቢ ማግኘት ጀምሬለሁ ባይ ነው። ወጣት ከድር፤ ተሽከርካሪውን ከወዳደቁ ዕቃዎች ሰብስቦ የሠራት ሲሆን ከዚህ ቀደምም ለከተማ ልማት የቆሻሻ መጣያ የደረቅ ጭነት ገልባጭ ሠርቶ ማስረከቡና ተቋሙም እስካሁን ድረስ እየተጠቀመበት መሆኑን ገልጾልናል።

መንግሥት ድጋፍ ካደረገልኝ ከዚህ የበለጡ ዘመናዊ ተሽከርካሪዎችንም የመሥራት ሀሳብ አለኝ ያለው ወጣት ከድር፤ በአሁኑ ጊዜ ተሽከርካሪ የመሥራት ችሎታ እንዳለኝ በተግባር አሳይቻለሁ፤የወደፊት ህልሜ በኢትዮጵያ የተሠራ መኪና በስፋት ለገበያ ማቅረብ ነው ብሏል።

ይህን ተሽከርካሪ የሠራሁት በራሴ ወጪ ነው ያለው ወጣቱ፤217 ሺህ ብር ወጪ አድርጌ ራሴ ሠርቼ ያቀረብኩት የባለ ሦስት እግር ተሽከርካሪ በፈጠራ ሀሳብ ውድድር ተቀባይነትና ዕውቅና አግኝቶ የኦሮሚያ ክልል ሳይንስና ቴክኖሎጂ ቢሮ ሁለት መቶ ሺህ ብር ተሸልሜበታለሁ ሲል ይናገራል። በዚህ ሽልማት ቀደም ሲል ሁለት ዓይነት አገልግሎት ይሰጥ የነበረውን ባለሦስት አግር ተሽከርካሪ አሻሽዬ አስር አገልግሎት እንዲሰጥ አድርጌዋለሁ ብሏል።

ታዳጊ አሚር ጀማል የአዳማ ከተማ ነዋሪ ነው። የ11ኛ ክፍል ተማሪው ከሌባና ከእሳት አደጋ የሚከላከል የፈጠራ ሥራ ነው የሠራው። የሠራው ማሽን የሌባ ኮቴውን ፣ ድምጹን፣ትንፋሹንና አካሉን አጤኖ ድምጽ በማሰማትና መብራት በማብራትና በማጥፋት የማስጠንቀቂያ መልዕክት እንደሚያስተላልፍ ይገልጻል።

ይኸው የፈጠራ ሀሳቡ ሌባን መከላከል ብቻ ሳይሆን በቤትም ሆነ በድርጅት ውስጥ የእሳት አደጋ ሲከሰት እሳቱ የሚፈጥረውን ከፍተኛ ሙቀት ተረድቶ እሳቱን ማጥፋት የሚያስችል ማሽን ጭምር መሆኑን ተናግሯል። ታዳጊው ይህን የፈጠራ ሀሳቡን ፋብሪካ አቋቁሞ በማምረት ለገበያ በስፋት ተደራሽ ለማድረግ የወደፊት ዕቅድ እንዳለው ነግሮናል።

በቅርቡ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በቡራዩ ከተማ የተገነባውን የተሰጥዖ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤት እንደ ወጣት ከድርና እንደ ታዳጊ አሚር ያሉት ኢትዮጵያውያን ልዩ ተሰጥዖ ባለቤቶች ይበልጥ ተሰጥዖዋቸውን የሚያበለጽጉበት ማዕከል እንደሚሆን ተናግረዋል።

አሁን ላይ በኢትዮጵያ በተለያየ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በርካታ ባለተሰጥዖዎች መኖራቸው ተመላክቷል።

እነዚህ ባለተሰጥዖዎች ያላቸውን ተሰጥዖ አበልጽገው ወደ ምርትና አገልግሎት ለመቀየር ሲያስቡ የትምህርት ቆይታቸውን ማጠናቀቅ ግድ ይላቸዋል፣ አሊያም ምቹ ሁኔታ ሳይፈጠርላቸው ባክነው ይቀራሉ። የቡራዩ የተሰጥዖ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤትም ይህንን ችግር የሚቀርፍ መሆኑ ነው የተገለጸው።

ለዚህም ነው የትምህርት ቤቱ የማደሪያ ሕንጻ፣ የመመገቢያ አዳራሽ፣ የአስተዳደር ሕንጻ ፣ የሕክምና ማዕከል፣ መማሪያ ክፍሎች፣ ቤተ ሙከራ ፣ ቤተ መጽሐፍ እና ወርክ ሾፖች ያሉት መሆኑም የተጠቆመው። በተጨማሪም ሁሉንም አገልግሎቶች የሚሰጡ ግብዓቶች የተሟሉለት መሆኑ በምረቃ መርሐ ግብሩ ላይ ተገልጿል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ወቅት እንዳሉት ፤ዓለማችን በቴክኖሎጂ መጥቃለች፤ሀገራችን ኢትዮጵያም ቴክኖሎጂ ከሚያስገኛቸው እንደ ኢኮኖሚ ያሉ ትሩፋቶች ተጠቃሚ ለመሆን፣ በዘርፉ የላቀ ዕውቀት ያላቸው ባለሙያዎችን ማፍራቷ ግድ ነው ።

ባለ ተሰጥዖ ታዳጊዎችና ወጣቶች ክህሎታቸውን እያዳበሩ፣ ሀገራቸውን በቴክኖሎጂ ከበለጸጉ ሀገራት ተርታ እንዲያሰልፉ፣ እንደ ቡራዩ የተሰጥዖ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤት ያሉ የተሰጥዖ ማዕከላትን ማብዛት ይጠበቅብናል ነው ያሉት።



የቀድሞ ጦር የሠራዊት አባል አቶ ኃይለየሱስ ገረመው

# በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምና ደህንነትን ለማስፈን በምክንያት የሚያምን ወጣት መኖር አስፈላጊ ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- የመከላከያ ሠራዊት በኢትዮጵያ ሰላምና ደህንነት ለማስፈን ከሚከፍለው መስዋዕትነት ጎን ለጎን በምክንያት የሚያምን ወጣት መኖር ለሀገር ሁለንተናዊ እድገት አስፈላጊ ነው ሲሉ የቀድሞ ጦር የሠራዊት አባል አቶ ኃይለየሱስ ገረመው ተናገሩ።

የቀድሞ ጦር የሠራዊት አባል አቶ ኃይለየሱስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ እድገት ለማምጣት በምክንያት የሚያምን ወጣት ሊኖር ያስፈልጋል። ይህም በኢትዮጵያ ሰላምና ደህንነት ለማስፈን ጉልህ ሚና አለው።

በአሁኑ ወቅት እየተፈጠረ ያለውን የጥላቻና ብሔርን መሠረት ያደረገ ግጭት ለመቀየር ለወጣቶች የስብዕና ስልጠናዎችን መስጠት አስፈላጊ ነው ያሉት አቶ ኃይለየሱስ፤ በኢትዮጵያ በተለያየ አካባቢ እየተከሰተ ያለውን አለመረጋጋት በሰከነ መንፈስ ለመመርመር ያስችላል ብለዋል።

ወጣቶች በሄዱበት ሁሉ በእኔነትና አገራዊ ስሜት በመንቀሳቀስ ከማኅበረሰቡ ጠቃሚ ወግ፣ ባህል፣ እሴትና እውቀትን መውሰድ እንጂ ለየትኛውም ወገን ማድላት እንደሌለባቸውም አንስተው፤ ምሑራን ኢትዮጵያ ከገባችበት ችግር ለማውጣት ምክንያታዊና መፍትሔ አመላካች ሃሳቦችን ማቅረብና የሀገርን አንድነትና ሉዓላዊነት ለማስከበር በሚደረግ ጥረት ግንባር ቀደም ሆነው መሰለፍ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

እንደ አቶ ኃይለየሱስ ገለፃ፤ ወጣቶች ችግሮች ሲፈጠሩ ወደ ሁከት አብረው ከመሄድ ይልቅ ችግሮችን በውይይት የሚፈቱበትን ባህል እንዲያዳብሩ የስብዕና ስልጠናዎችን መስጠት አስፈላጊ ነው። ይህም ሁሉንም በእኩል ዓይን የሚያይ ወጣት እንዲፈጠርና አጥፊዎች የሚፈነጩበት ሥርዓት በሀገሪቷ ላይ እንዳይኖር ያደርጋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ምድር ከአሁን በኋላ የተትረፈረፈ ምግብ የሚመረትበት መሆን ይኖርበታል እንጂ፣ መድፍና ታንክ የሚያጓሩበት እንዲሆን መፈቀድ የለበትም። ሀገራቸውን በልማት የሚያኮሩ አርበኞች የሚከበሩበት እንጂ፣ አገር ለማፍረስ የሚያሴሩና ሕዝብ የሚያስጨንቁ መሰሪዎች የሚንጎማለሉበት መሆን አይገባውም።

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ጦርነት ውስጥ ነው ያለችው። ይህንን አውዳሚ ጦርነት ለማስቆም የሁሉንም ኢትዮጵያውያን ርብርብ ይጠይቃል። ለዚህ ስኬት ደግሞ ብሔራዊ ምክክር አስፈላጊ ነው። የሀገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ ተቀራርበው መነጋገር ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

ጠመንጃ አንግቶ መነጋገር አይቻልም። ጠመንጃ ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ መውጣት አለበት። ጦርነቱ ሲጠናቀቅ ኢትዮጵያ ዳግም ወደ ጦርነት እንዳትመለስ ተደርጎ መሆን ይኖርበታል። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎችም ሆኑ ሌሎች የአገር ጉዳይ የሚመለከታቸው ወገኖች፣ ኢትዮጵያ ከግጭት የፀዳች አገር እንድትሆን ቁርጠኝነታቸውን በተግባር ሊያሳዩ ይገባል።

ለሰላም መስፈን ከዘመናዊ የውይይት ሂደቶች በተጨማሪ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ የሰላምና የእርቅ ሥርዓትን መጠቀም እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፤ ሰላም ከግለሰብ የውስጥ ስሜት ይጀመራል። የግለሰቦችን የሰላም እና የመረጋጋት ሁኔታን ለማፅናት የሃይማኖት አባቶች እና መሪዎች ሚናቸው የጎላ ነው ብለዋል።

ይህንን መልካም የሆነ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ሁሉም የሃይማኖት ተቋማት እንዲተገብሩትና ምዕመኑን ስለ ሰላምና እርቅ ማስተማር እና ማስገንዘብ የእለት ተእለት ሥራቸው እንዲያደርጉትም ጥሪ አቅርበዋል።



ወይዘሮ ዓይናለም ንጉሴ

## ሚኒስቴሩ ከ450 ቢሊዮን ብር በላይ ለመሰብሰብ እየሠራ ነው

### - በሦስት ወራት ከ93 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ሰብስቧል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የገቢዎች ሚኒስቴር በ2015 በጀት ዓመት 450 ነጥብ 29 ቢሊዮን ብር ከሀገር ውስጥ ታክስ እና ከውጪ ንግድ ቀረጥና ታክስ ለመሰብሰብ እየሠራ እንደሆነ ገለጸ። በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 93 ነጥብ 348 ቢሊዮን ብር መሰብሰቡንና ይህም ከዕቅዱ አንፃር ከ98 በመቶ በላይ እንደሆነ ሚኒስቴሩ አክሎ ገልጿል።

የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይዘሮ ዓይናለም ንጉሴ እንደገለጹት፤ በተያዘው በጀት ዓመት ከአምናው በተሻለ መልኩ ገቢዎችን ለመሰብሰብ እየተሠራ ነው። በበጀት ዓመቱ ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በምክንያታዊነት በማስላት በታቀደው ዕቅድ መሠረት ከ2014 በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር ከ113 ነጥብ 289 ቢሊየን በላይ ብር ብልጫ ያለው ገንዘብ ለመሰብሰብ እየተሠራ ነው።

በ2014 በጀት ዓመት በአጠቃላይ ከ336 ነጥብ 7 ቢሊዮን በላይ ብር መሰብሰቡን እና ከተጠቀሰው ገንዘብ ውስጥም 196 ነጥብ 2 ቢሊዮን በላይ ብር ከሀገር ውስጥ ታክስ፤ 140 ነጥብ 4 ቢሊዮን በላይ ብር ደግሞ ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ መገኘቱን የገለጹት ሚኒስትሯ፤ በ2015 ይህን መጠን ከፍ በማድረግ ከ450 ቢሊዮን በላይ ብር ለመሰብሰብ እየተሠራ እንደሆነ ተናግረዋል።

በ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ከሀገር ውስጥ ታክስ እና ከወጪ ንግድና ቀረጥ 93 ነጥብ 348 ቢሊዮን በላይ ብር ገቢ መሰብሰቡን ያሳወቁት ወይዘሮ ዓይናለም፤ አፈጻጸሙ ከተያዘው የ95 ነጥብ 184 ቢሊዮን ብር ዕቅድ አንጻር ከ98 በመቶ በላይ መሆኑን ገልጸዋል።

አፈፃፀሙ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት 70 ነጥብ 39 ቢሊዮን ብር ገቢ አኳያ ከ33 በመቶ በላይ ዕድገት ማሳየቱን ሚኒስትሯ ወይዘሮ ዓይናለም ተናግረዋል።

ሚኒስትሯ አክለውም ከተሰበሰበው ገቢ ውስጥ የሀገር ውስጥ ገቢ 51 ነጥብ 576 ቢሊዮን በላይ ብር ሲሆን ከወጪ ንግድና ቀረጥ ደግሞ 41 ነጥብ 7 ቢሊዮን በላይ ብር ገቢ የተገኘ መሆኑን ጠቁመዋል።

ታክስ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን ማሳደግ፤ ዲጂታል የገቢ አሰባሰብ ሥርዓትን መገንባት፤ የታክስና ጉምሩክ አስተዳደር ፍትሐዊነትን ማረጋገጥ፤ የውስጥና የውጭ ስትራቴጂክ አጋርነትን ማጠናከር እና የዳበረ የሥራ ባህል መፍጠር ለነገ የማይባሉ ተግባራት መሆናቸውንና ገቢን ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሠራባቸው መስኮች መሆናቸውን ሚኒስትሯ አስረድተዋል።

የሁሉም ሥራዎቻችን መቋጫ ጠንካራ ሀገር መገንባት ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ በኢኮኖሚ የበለጸገች ሀገር ዜጋ በሄደበት ሁሉ የሚከበር መሆኑን አስታውሰው፤ ኢትዮጵያ የብዙ ክብር ባለቤት ብትሆንም ያላት ታሪካዊ የሀገር ክብር በኢኮኖሚው ካልተደገመ ክብሯ ሙሉ ሊሆን እንደማይችል ተናግረዋል።

በኢኮኖሚው መስክ ኢትዮጵያን ተምሳሌት የማድረግ ራዕይ ከማይጨበጥ ተራ ፍላጎት የተነሳ አለመሆኑንና ኢትዮጵያ ያላትን ሁለንተናዊ አቅም ለሚያሻግራት ፕሮግራሞች የማዋል የተረጋጋ ዕድል ካገኘች የማይሳካ አንዳች ኢኮኖሚያዊ ተግባር እንደሌለ በማረጋገጥ ነውም ብለዋል።

የገቢዎች ሚኒስቴር የጀመረውን የግብር አስተዳደር ሥርዓት የማዘመን አጠናክረን የምንቀጥል ይሆናል ያሉት ሚኒስትሯ እስካሁን ባለው ጊዜ ውስጥ 17 ባንኮች የኤሌክትሮኒክ ክፍያ ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጋር መፈራረማቸውን ገልጸው፤ ሌሎችን ምቹ አማራጮችን ተግባራዊ ለማድረግ በትኩረት እንደሚሠሩ አብራርተዋል።

በበጀት ዓመቱ ወደ ብልሹ አሠራር የገቡ አካላትን በበቂና አስተማማኝ መረጃ ተደግፈን አስፈላጊውን ሕጋዊ እና አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰዳችንን አጠናክረን እንቀጥላለን ሲሉም ጠቁመዋል።

# የውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት ሊቀጥል የሚችለው የእኛ አንድነት እስከሌለ ድረስ ብቻ ነው

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት ሊቀጥል የሚችለው የእኛ አንድነት እስከሌለ ድረስ ብቻ መሆኑን ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ተናገሩ። ሁሉም ኢትዮጵያዊ ልዩነቱን ወደጎን በመተው በአንድነት በመቆም ለየትኛውም የውጭ ጫና የማንበገር መሆናችንን ልናሳይ ይገባል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) ና የኦሮሞ ነጻነት ግንባር(ኦነግ) አመራሮች ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የውጭ ጠላቶች ኢትዮጵያን በመከፋፈል ፍላጎታቸውን በኢትዮጵያ ላይ ለመጫን በተደጋጋሚ ሙከራ እያደረጉ ነው።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ አቶ ዋስይሁን ተስፋዬ እንደገለጹት፤ የውጭ ኃይሎች ጫና ዛሬ የተፈጠረ አይደለም። ባለፉት ሦስትና አራት ዓመታት ጭምር አሸባሪው ሕወሓት በሰሜን ዕዝ ላይ ጥቃት ከከፈተ ጊዜ ጀምሮ በተደጋጋሚ ከፍተኛ ጫና ሲያደርጉ ቆይተዋል። ሁልጊዜ ሀገር ክፍፍል ውስጥ ገብታለች ብለው ባሰቡበት ጊዜ እጃቸውን ባገኙት አጋጣሚ የማስገባት ፍላጎት አላቸው።

እንደ አቶ ዋስይሁን ገለጻ፤ የውጭ ኃይሎች በኢትዮጵያ ላይ ጣልቃ በመግባት ፍላጎታቸውን ለመተግበር ጥረት ያደርጋሉ። ቁልፉ ጉዳይ የምዕራባውያን ጣልቃ ለመግባት መሞከር ሳይሆን ኢትዮጵያውያን ክፍተቶችን በመሙላት በአንድነት የመቆም ቁርጠኝነት ነው። የነሱን ጣልቃ ገብነት ለማስቆም ሁሉም ሀገርን በማስቀደም በአንድነት መቆም ወሳኝ ነው።

የውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት ሊቀጥል የሚችለው የእኛ አንድነት እስከሌለ ድረስ ነው ያሉት የድርጅት ጉዳይ ኃላፊው፤ በተከፋፈልን ቁጥር የትኛውም የውጭ አካል ጣልቃ ለመግባት ፍላጎት አለው። ሁሉም በአንድነት በመቆም ለየትኛውም የውጭ ኃይሎች ጫና የማንበገር መሆናችን ማሳየት አለብን። ይህንንም ከቃል በዘለለ በተግባር ማሳየት አስፈላጊ ነው ብለዋል።

በአገር ላይ የሚደረጉ ጣልቃ ገብነቶችን እንደማንቀበል ለማሳየት የሚደረጉ ሰላማዊ ሰልፎችም ተገቢ መሆናቸውን ኢዜማ ያምናል ያሉት አቶ ዋስይሁን፤ በአንድነት ቆመን ከየትኛውም ወገን የሚመጣ ጣልቃ ገብነት መታገል አለብን ብለዋል። እንዲህ አይነት ጣልቃ ገብነቶች ሁልጊዜም እንደሚመጡ በመረዳት ልዩነቶቻችንን ከሀገር በታች በማድረግ በአንድነት መቆም አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል።



አቶ ዋስይሁን ተስፋዬ



አቶ ቶሌራ አደባ

ኢዜማ በሀገር ላይ የሚመጣን የውጭ ጣልቃ ገብነት መታገል እንደሚገባ በተደጋጋሚ የሚገልጸው የማይለወጥ አቋሙ በመሆኑ እንደሆነ ያስታወሱት አቶ ዋስይሁን፤ መከላከያ የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች ሁሉ እንደሚደግፉ ጠቁመዋል።

አቶ ዋስይሁን፤ መንግሥት እየወሰደ ያለው የሕግ ማስከበርና የአገር ሉዓላዊነትን የማስጠበቅ እርምጃ በተራዘመ ቁጥር ብዙ ችግሮችን ያስከትላል። ስለሆነም መንግሥት በአጭር ጊዜ መፍትሔ ሊሰጠው ይገባል። ከወታደራዊ አማራጭ በተጨማሪ የሚወሰዱ የሰላም አማራጮች ሁሉ ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው። የወደሙ ተቋማትን በመገንባት ወደ ልማት ለመመለስ የተጀመሩ ሥራዎችም ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ቃል አቀባይ አቶ ቶሌራ አደባ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ አሸባሪው ሕወሓት ከአፈጣጠሩ በአፈሙዝ ኃይል ወደ ሥልጣን የመጣና በአምባገነንነት ኢትዮጵያን ለ27 ዓመታት ያህል የገዛ ቡድን ነው። ከቡድኑ ጋር በሰላማዊ ውይይት የሚፈታ አንዳችም ነገር እንደሌለ የፓርቲያቸው አቋም ጭምር ነው።

ያለው ብቸኛው አማራጭ የተጀመረውን ሕጋዊ እርምጃ በማጠናከር ለትግራይ ሕዝብና ለቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ እፎይታን ማረጋገጥ ነው ሲሉም አቶ ቶሌራ አመላክተዋል።

የውጭ ተጽዕኖን ለመግታት ድልድይ ሆኖ የሚያገለግለውን የአሸባሪውን ሕወሓት ቡድን ከድርጊቱ ማስቆም ይገባል ያሉት አቶ ቶሌራ፤ ከዚህ እንቅስቃሴ ጎን ለጎን ከበፊቱ በበለጠ ሕዝቡ የሚጠበቅበትን አገራዊ ግዴታ ለመወጣት አንድነቱን ማጠናከር ያስፈልጋል ብለዋል። ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችም አገርን በማስቀደም ያለምንም የአመለካከት ልዩነት በጋራ መቆም እንዳለባቸው በመግለጽ ፓርቲያቸውም ዝግጁ መሆኑን አስታውቀዋል።

እንደ ቃል አቀባዩ ገለጻ፤ መንግሥት የሀገሪቱን ሉዓላዊነት፣ የግዛት አንድነትና ዘላቂ ሰላም ለማረጋገጥ በሽብር ቡድኑ ላይ እየወሰደ ያለው እርምጃ ትክክለኛነቱን ለዓለም ማኅበረሰብ ለማረጋገጥ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት የተለያዩ የድጋፍ ሰልፎች ማድረግ ጠቃሚ ነው። የተጀመረው ሕግ የማስከበር ዘመቻ ዳር ለማድረስ ለመከላከያ ሠራዊት አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠትም ከሁሉም ይጠበቃል።

# የብዙዎችን ጫና ያቃለለው የትምህርት ቤት ምገባ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

ወይዘሮ አይናለም ጉልላት ይባላሉ። በየካ ክፍለ ከተማ በሚገኘው የካራ አሎ ቅድመ መደበኛና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መጋቢ እናት ናቸው።

ባለቤታቸውን ሞት ከነጠቃቸው ጊዜ ጀምሮ አምስት ልጆቻቸውን ማስተዳደር ፈተና ሆኖባቸው እንደነበር የሚገልጹት ወይዘሮ አይናለም፤ የምገባ መጀመርን ተከትሎ የተፈጠረላቸው የሥራ እድል ተስፋቸውን አለምልሞታል።

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ በመጣው የኑሮ ውድነት መፈተናቸው ባይቀርም ቀድሞ ከነበራቸው ሕይወት ግን በእጅጉ የተሻለ መሆኑን የሚጠቁሙት ወይዘሮዋ፤ ልጆቻችን ብለን የተረከብናቸውን ተማሪዎች በተሻለ ማገልገል እንድንችል አሁንም የመንግሥት የቅርብ ክትትልና እገዛ ያስፈልገናል ይላሉ።

ሌላኛዋ መጋቢ እናት ወይዘሮ ዘነበች ኃይሌ በበኩላቸው፤ ሦስት ልጆቻቸውን በችግር ያሳድጉ እንደነበር በመግለጽ የምገባ ፕሮግራም ሲመጀመር በተፈጠረላቸው የሥራ እድል ብዙ ችግሮችን እንዲሻገሩ አግዞኛል ይላሉ።

አሁን ላይ የኑሮ መወደድ የተበደርነውን ብድር ለመመለስና ተሻሽለን ቦታውን ለሌሎች ለመልቀቅ ፈተና ሆኖብናል የሚሉት ወይዘሮዋ፤ መንግሥት የዋጋ ማሻሻያ ከማድረግ ጀምሮ ሌሎችን አስፈላጊ እገዛዎችን እንዲያደርግላቸው ጠይቀዋል።

የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር አቶ አሰፋ መላኩ እንደሚሉት ደግሞ፤ ምገባ የተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለወላጆችም ብሎም ለመምህራንም እፎይታ ሰጥቷል።

ቀደም ባሉት ጊዜያት መምህራን የተማሪዎቻቸው በልቶ አለመምጣት አሳስቧቸው ከኪሳቸው አውጥተው ለመመገብ ጥረት ሲያደርጉ እንደነበር ያስታውሳሉ።



ፎቶ ፡- አሸናፊ ጉደታ

የምገባው ተግባራዊ መሆን ቤተሰብ ውስጥ የሚፈጠረው የኢኮኖሚ ችግር ጭምር ተቃሏል የሚሉት አቶ አሰፋ፤ ይህ ደግሞ በተማሪው ስነልቦና ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አወንታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል ይላሉ።

መርሐ ግብሩ የወላጆችን ጫና ከማቃለሉ ባሻገር ተማሪዎች ትምህርታቸውን ተረጋግተው እንዲከታተሉም ማድረጉን የሚጠቅሱት ርዕሰ መምህሩ፤ በችግር ውስጥ ለነበሩ እናቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድም የማይተካ ሚና አለው ይላሉ።

የትምህርት ቤቱ የትምህርት መሻሻል ምክትል ርዕሰ መምህርና የምገባ መርሐ ግብሩ አስተባባሪ አቶ አይሸሽም ልየው እንደሚሉት፤ የምገባ መጀመር የተማሪዎች መጠነ ማቋረጥና ማርፈድ እንዲቀነስ በማድረግ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ መከታተል እንዲችሉ ማድረጉን ያነሳሉ።

ምገባው ከመማር ማስተማሩ ባሻገር የብዙ ወላጆችን እንባ የጠረገና እፎይታን የሰጠ ነው የሚሉት አቶ አይሸሽም፤ ችግር ውስጥ የነበሩ በርካታ እናቶችም በተፈጠረው የሥራ ዕድል ተደራጅተው እንዲሠሩ በመደረጉ የኢኮኖሚ አቅማቸው ከፍ እንዲል አስችሏል።

በትምህርት ቤቱ ከሚገኙ 3ሺ 715 ተማሪዎች መካከል ከ60 ተማሪዎች በስተቀር ሌሎች የምገባው ተጠቃሚ መሆናቸውን አስታውሰው፤ 110 እናቶችም በመደራጀት ምገባውን በማከናወን ላይ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ።

እናቶች ተማሪዎችን ልክ እንደልጆቻቸው አድርገው ለመመገብ ቢጥሩም ክፍያቸው ግን በቀን ለአንድ ተማሪ 20 ብር መሆኑ ፈታኝ እንደሆነባቸው በመጠቆም ተጨማሪ ድጎማ ቢደረግ መልካም ነው ይላሉ።

አዲስ አበባ ከተማ እያከናወነች ባለው የተማሪዎች ምገባ መርሐ ግብር ዘላቂ አመጋገብና ሥነ ምግብ በሚል ዘርፍ ከተወዳደሩ ከ133 ከተሞች ጋር ተወዳድራ ማሸነፏ አይዘነጋም።

ዜና

# አንዳንድ የምዕራባውያን ሚዲያዎች አሸባሪው ትሕነግ የተሸነፈ ሲመስላቸው ሕልውናውን ለማቆየት ይረባረባሉ

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- አንዳንድ የምዕራባውያን ሚዲያዎች ሕወሓት ያሸነፈ በመሰላቸው ጊዜ የዘገባ ሽፋን ባለመስጠትና ጉዳዩን ቸል በማለት እንዲሁም መንግሥት ስልጣን እንዲለቅ በመገፋፋት፣ ቡድኑ የተጠቃ በመሰላቸው ጊዜ ደግሞ ጉዳዩን ከትግራይ ሕዝብ ጋር በማያያዝ እና ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት እየተፈፀመ እንደሆነ በማስመሰል ሚዛናዊነት የጎደለው ዘገባን ይሠራሉ ሲሉ በዲላ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ትምህርት ክፍል መምህርና የሦስተኛ ዲግሪ ተማሪው አቶ አበበል ጓንጉል አስታወቁ።

አቶ አበበል ጓንጉል በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፣ አንዳንድ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ከጋዜጠኝነት ስነምግባር እና መርሕ ውጭ ሙሉ ለሙሉ የተሳሳተ መረጃ እያሰራጩ ነው።

እነዚህ ሚዲያዎች ሚዛናዊነት የሚባለውን የጋዜጠኝነት መርሕ ፈጽሞ አያውቁም ያሉት አቶ አበበል፣ ዘገባዎቻቸው በሃገራቸውና በዲፕሎማቶቻቸው የፖለቲካ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ነው ብለዋል።

በዚህ መሠረት አሸባሪው ሕወሓት ያሸነፈ በመሰላቸው ጊዜ የዘገባ ሽፋን ባለመስጠትና ጉዳዩን ቸል በማለት ያልፋሉ፤አልያም መንግሥት ስልጣን እንዲለቅ ይገፋፋሉ፣ በአንጻሩ ቡድኑ የተጠቃ በመሰላቸው ጊዜ ደግሞ ሚዛናዊነት የጎደለው እና የውሸት ዘገባ ጭምር በመሥራት የዓለምን ሕዝብ ለማሳሳት እና ቡድኑን ለመታደግ ይሯሯጣሉ።

አንድ ዜና ዜና ለመባል ከብዙ የመረጃ ምንጮች መረጋገጥ ቢኖርበትም እነዚህ ሚዲያዎች አንድን ነጠላ ምንጭ ወስደው ዜና ይሠራሉ፤ ምንጭ ሳይገልጹም ዜና ሲሠሩ ይስተዋላሉ ብለዋል።

እንደ መምህሩ ገለጻ፣ በነዚህ ሚዲያዎች ሰሞኑን የሚወጡ ዘገባቸው ከሰብዓዊ መብት ጥሰት ጋር የተገናኙ ናቸው። ነገር ግን ትግራይ ክልል ተፈጽሟል የሚሉት የሰብዓዊ መብት ጥሰት ቢፈተሽ እውነታው ከነሱ ዘገባ የራቀ ነው ብለዋል።

አሸባሪው ሕወሓት ወደ አማራና ወደ አፋር ክልሎች በገባበት ወቅት ዝምታን የመረጡት እነዚህ ሚዲያዎች በአንጻሩ አሸባሪ ሕወሓት በሦስተኛ ዙር ወረራው እንዳሰበው ወደመሐል ሃገር የሚያደርገው ግስጋሴ ሳይሳካለት ሲቀር እና ጠንካራ መከላከል ሲገጥመው ለቡድኑ በውሸት ዘገባ ጭምር ድጋፍ ያደርጉለታል ሲሉም ተናግረዋል።

በዚህ መሠረት ሰሞኑን በትግራይ ክልል ትልቅ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እየተፈጸመ እንደሆነ በተሳሳተ መንገድ ይሰብካሉ። ለምሳሌ ከሰሞኑ በትግራይ አካባቢዎች በጭለማ ውስጥ መሆናቸውን የሚያሳዩ የሳተላይት ምስሎችን በማሳየት መንግሥት ሆን ብሎ የትግራይን ሕዝብ ለችግር መዳረጉን ይዘግባሉ። ነገር ግን በአሸባሪ ቡድን የመሠረተ ልማት ውድመት የተነሳ የአማራና የአፋር ክልሎች ለበርካታ ጊዜ በጨለማ ውስጥ ሲቆዩ አንዳችም ዘገባ ሲሠሩ አልታዩም። ዓላማቸው ፖለቲካ ስለሆነ ማጉላት የሚፈልጉት የትግራይ ክልልን ብቻ ነው። ዘገባቸው ከሚዲያ ሕግና መርሕ ይልቅ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ያመዝኑበታል ብለዋል።



አቶ አበበል ጓንጉል

የምዕራባውያን ሚዲያዎች በዋናነት ለተመሠረቱበት ሀገር የቆሙ ናቸው ያሉት አቶ አበበል፤ ዋና ትኩረታቸው የምስራቅ አፍሪካ ጂኦ ፖለቲክስ በመሆኑ እሱን መሠረት በማድረግ ኢትዮጵያ ላይ የሚፈልጉትንና ለነሱ ታዛዥ የሆነ መንግሥት መፍጠር ይፈልጋሉ ሲሉም ተናግረዋል።

አቶ አበበል እንደተናገሩት፣ በኢትዮጵያ የነሱን ዓላማ የሚያስፈጽም መንግሥት አለማግኘታቸው ዕረፍት ነስቷቸዋል፤ ሚዲያዎቻቸው ይህን ታሳቢ አድርገው ነው የሚሠሩት፤ ፍላጎታቸውን ለማሳካት ያልሆነውን እንደሆነ በማስመሰል፤ የሆነውን እውነታ ወደ ጎን በመተው ዘገባዎችን ያሰራጫሉ። የምዕራባውያን ሚዲያዎች ጥቅም እንደሚያስገኙላቸው ካሰቡ ያለ መረጃ የውሸት ዜና ይሠራሉ።

ለዚህ ከሚጠቀሟቸው ስልቶች ውስጥ አንዱ የሰላም አምባሳደር የሆነው የሃገር መከላከያ ሠራዊትን ስም ማጠልሸት መሆኑን የጠቆሙት አቶ አበበል፤ በአንፃሩ የመንግሥትን መልካም ነገሮች ለመዘገብ ፍላጎት የላቸውም ሲሉም ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከሰሞኑን ከሌለው ጊዜ በተሻለ አላማጣና ሌሎች አካባቢዎች ላይ የሰብዓዊ እርዳታ እያደረሰ ቢሆንም መዘገብ እንዳልፈለጉም ገልጸዋል።

በመሆኑም የሚሰራጩ የሐሰት ዜናዎችን ለመመከት የሀገር ውስጥ ሚዲያዎች አጀንዳ በመፍጠር በተደጋጋሚ እውነታውን ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። በርካታ ኢትዮጵያውያን በመላው ዓለም ስለሚገኙ በሀዳሴው ግድብ ዙሪያ ይደረግ የነበረውን ዓይነት ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፤ በተለያዩ የዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ላይ እየቀረቡ የኢትዮጵያን አቋም በየጊዜው ለዓለም ማኅበረሰብ ማሳወቅ ይጠበቃል ብለዋል።

ከዚህ ጎን ለጎን የዲያስፖራው ማኅበረሰብ በማኅበራዊ ሚዲያዎች አማካኝነት መረጃዎችን ለማድረስ በአንድነት መቆምና ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እውነታውን ማሳወቅ እንደሚገባም ገልጸዋል።

## “አሸባሪው ትሕነግ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኪሳራ ለማድረስ የሚያደርገው ጥረት የጸረ ሕዝብ ባህሪው መገለጫ ነው ብለዋል።

እንደ አምባሳደር ድሪባ ገለፃ፣ የሰሜን ዕዝ የመከላከያ ሠራዊት አባላትን ከኋላ በመውጋት የሀገር ክህደት ወንጀል ከፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሦስተኛ ዙር ድረስ ወረራ የሚፈጽመው አርሶ አደሩ ለምርት በሚዘጋጅበት ወቅት ነው። በተለይ የአማራ ክልል አርሶ አደር ፊቱን ወደ ልማት በማዞሩ መንግሥት በሰላም ጥሪ በተዘናጋበት ወቅት ወረራ በመፈጸም ምርቱን ወደ ቤቱ እንዳያስገባ የማድረግ ሥራ ሲሠራ ቆይቷል።

በኢትዮጵያ በሰፈነው አንፃራዊ ሰላም የተጀመረውን የአርሻ ሥራ የስንዴ ምርትና ሌሎች የኢኮኖሚ ሥራዎች በማደናቀፍ እረፍት በመንሳት መንግሥት የልማት ሥራውን በመተው በእሳት ማጥፋት ላይ እንዲጠመድ ለማድረግ ሲንቀሳቀስ ይስተዋላል።

በሰሜን ኢትዮጵያ የሚደረገው ጦርነት የምርት ጊዜን እየጠበቀ የሚያገረሽ በመሆኑ በግብርና ምርት እድገት ላይ አሉታዊ አስተዋጽዖው የጎላ መሆኑን ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የሆነው ግብርና አጠቃላይ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ 30 በመቶ ድርሻ እንዳለው ገልጸው፣ ጦርነቱ በምርት ወቅት ማገርሸቱ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በእጅጉ ይጎዳዋል ብለዋል። አሸባሪው ትሕነግ የኑሮ ውድነትን የሚያባብሱ የኢኮኖሚ አሻጥር በመፈጸም የከተማው ነዋሪ በመንግሥት ላይ ለተቃውሞ እንዲወጣ የማድረግ ዕቅድ እንዳለውም ተናግረዋል።

የሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት የምርት ወቅትን ጠብቆ በአሸባሪው ትሕነግ የሚቀሰቀሰው “የኢኮኖሚ አሻጥር ለመፍጠር ታስቦ ሊሆን ነው” ያሉት አምባሳደር ድሪባ፤ በክረምት የሚረስ ልምድ ላለው የኢትዮጵያ አርሶ አደር አስቸጋሪ እንደሚሆን ገልጸዋል።

ከዚህም ባለፈ ኢትዮጵያ ለውጭ ገበያ የምታቀርበው የግብርና ምርት እንዲቀንስ በማድረግ በሰብዓዊ በዕርዳታ ሰበብ የውጭ ኃይሎች ተላላኪ እንድትሆን የታሰበ አሻጥር ሊሆን ይችላልም ብለዋል።

አሸባሪው ትሕነግ አምራች ድርጅቶችና መጋዘኖችን በማጥቃት፣ ከእርሻ እስከ ገበያ ባለው ሰንሰለት ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ እንዲኖር በማድረግ፣ ከውጭ የሚገቡ ሸቀጦችና ነዳጆችን ለማስተጓጎል የማስገቢያ ኮሪደሮችን በመቆጣጠር የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ችግር እንዲባባስ ማድረግ እንደሚፈልግም ተናግረዋል።

ጦርነት በተከሰተባቸው አካባቢዎች ሁሉ የኢንቨስትመንት ቦታዎችን ሆን ብሎ ማጥቃት፣ ማቃጠል፣ ማውደም በግልጽ ታይቷል ያሉት አምባሳደር ድሪባ፤ በኢትዮጵያ መዋዕለ ንዋያቸውን ለማፍሰስ የሚመጡ የውጭ ባለሃብቶችን እንቅስቃሴ በመገደብ ከውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የሚገኘውን ገቢ ያሳጣል ብለዋል።

ነገር ግን የኢትዮጵያ መንግሥት የቢጋ መስኖ ልማት በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እያሳደገ ይገኛል። ከዚህም ባለፍ በአሸባሪ ቡድኑ የሚደረገው ሀገር የማፍረስ እንቅስቃሴን በሚገባ እየመከተ ለኢትዮጵያ ብልጽግና እና ሰላም ተግቶ እየሠራ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

## በአሸባሪው ሕወሓት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በአስር ቀናት ውስጥ ጉዳቱንና የሚያስፈልገውን ግብዓት ገምግሞ ወደ ሥራ መግባቱን የጠቆሙት አቶ ሞገስ፤ መሥሪያ ቤታቸው ሥራውን ለማጠናቀቅ በሙሉ አቅሙ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል ብለዋል።

ሥራው ፈጥኖ አገልግሎት መጀመር ስለሚገባው በተባለው ጊዜ ለማጠናቀቅም የሁሉም ሪጅን ሠራተኞች በመረባረብ ላይ እንደሚገኙ የገለጹት አቶ ሞገስ፤ በሰሜን ትግራይ ሪጅን ካለው ውጪ ያሉት በሙሉ ተሳትፎ ማድረጋቸውንም ነው አቶ ሞገስ የተናገሩት።

ከወልዲያ እስከ አላማጣ ድረስ ብቻ ሃምሳ አካባቢዎች ላይ ጉዳት ደርሷል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ እያንዳንዱን ሠርቶ ለማጠናቀቅ ወደ ሥራ መግባቱንም ነው ያመላከቱት።

በጥገና ሥራው ከተለያዩ ስፍራዎች በሚመጡ ባለሙያዎች ሥራው እንደሚከወን የገለፁት ዳይሬክተሩ፤ ባለው የሠራተኞቹ ርብርብም መሠረተ ከታሰበው ፍጥነት በተሻለ መንገድ የሚያልቅበት እድል መኖሩንም ነው የገለጹት።

አቶ ሞገስ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎትም ከመሥሪያ ቤታቸው ቀጥሎ ያለውን ሥራ የመሥራት ሁኔታ ስለሚጠበቅበት ሥራዎች መጀመራቸውን መረጃው እንዳላቸው ጠቁመዋል።

መሥሪያ ቤቱ እየከወነ በሚገኘው ከፍተኛ የኃይል መስመር እንዲሁም ማከፋፈያ ጣቢያ ጋር በተያያዘ ጥገናው ሰሜን ምሥራቅ የሚባለውና ደሴን ማዕከል ያደረገው ሪጅን ብቻ የሚከታተለው ሳይሆን የሁሉም አካባቢዎች ተሳትፎ ያለበት ነው ብለዋል።

በሰሜን ኢትዮጵያ በተካሄደው ጦርነት የወደሙ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቶችን በፍጥነት በመጠገን ለረጅም ጊዜ በጨለማ ውስጥ የቆየው ኅብረተሰብ ኃይል እንዲያገኝ ለማድረግ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ሁሉም ሪጅን የጥገና ባለሙያዎች በርብርብ እየሠሩ እንደሆነ አቶ ሞገስ ጠቁመዋል።

የሽብር ቡድኑ ሕወሓት ኢትዮጵያ ላይ ባወጃቸው ሦስት ዙር ጦርነቶች በደረሰባቸው በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ሁሉ የኅብረተሰቡን መገልገያ የሆኑ ለትምህርት፣ ለጤና፣ ለኤሌክትሪክ እንዲሁም ለሌሎች መሠረተ ልማቶች መገልገያ የሚውሉ ግብዓቶችን ሲያወድም እንደነበር አቶ ሞገስ አስታውሰዋል።

## የውጭ ኃይሎች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሀገር ጣልቃ በመግባት የውስጥ ጉዳይሽን እንዲህና እንዲያ አድርጊ ለማለት መሞከር ስህተት መሆኑን ጠቁመዋል።

ለቅኝ ግዛት ተንበርክካ የማታውቅን ሀገር የውጭ ኃይሎች ሀገሪቱ እንዴት መመራት እንዳለባት እንዲመክሩ እና በእጅ አዙር ሊገዙ እንዲሞክሩ ከአሸባሪው ሕወሓት ውጪ የሚፈቅድ ኃይል አለመኖሩንም ሊያውቁ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

አርቲስት ደበበ፣ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ማንኛውም በዲሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጠ መንግሥት እንዲኖር ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ነፃ መሆኑን አስታውሰው፤ እኛ ኢትዮጵያውያን ይህን እናውቃለን፤ ሆኖም አንዳንድ ኃይሎች ተባብረው አሸባሪውን ሕወሓት እየደገፉ ወደ ሥልጣን እንዲመለስ እየሠሩ ነው ብለዋል። ይህም ኢትዮጵያውያን ሊታገሱት የማይችሉት ነገር መሆኑን በአጽንዖት ገልጸዋል።

በተለይ የቅኝ ግዛት አስተሳሰብ ያላቸው አንዳንድ ምዕራባውያን እኛ የምንኖርበትን የዓለማችን ክፍል ጫካ ይሉታል ያሉት አርቲስት ደበበ፤ እኛ አንበሶች መሆናችንንና ስለ አድዋ ልናስታውሳቸው እንፈልጋለን ሲሉ አሳስበው የኢትዮጵያውያን አንበሶች በወቅቱ የሠሩት ጀብዱ የቅኝ ግዛት ምኞትን ፀጥ አድርጎ ማስቀረቱ ሊዘነጋ አይገባውም ብለዋል።

## “የዜጎች ሰብዓዊ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለድርድር እንደማይቀርብ የገለፁት ሚኒስትሩ፣ በተረጂዎች ስም የሚመጣ የእርዳታ እህልና መድኃኒት በየትኛውም የሽብር ብድን እንዲዘረፍ መንግሥት አይፈቅድም ብለዋል።

መንግሥት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል ያለውን የዕርዳታ ሥርጭት በመቆጣጠር በበላይነት እንደሚመራም የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትሩ ለገሰ ቱሉ(ዶ/ር) አስታውቀዋል።

የዜጎች ሰብዓዊ እርዳታም ሆነ ጥበቃ ለድርድር እንደማይቀርብ ጠቅሰው፣ በተመሳሳይ ሁኔታ የትግራይ ሕዝብ ሰብዓዊ እርዳታም ሆነ ጥበቃ ለድርድር አይቀርብም ብለዋል።

በሁሉም አካባቢዎች በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ላሉ ሁሉ ሰብዓዊ ዕርዳታ ለማፋጠን መንግሥት በትጋት እየሠራ መሆኑንም መግለጻቸውን በማኅበራዊ ትስስር ገፃቸው አስፍረዋል።

ይህ ሕገ-መንግሥታዊ ግዴታው መሆኑን በማንሳትም፣ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል እንደሚሠራም አስገንዝበዋል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የወቅታዊ ሁኔታ መረጃ በሚል ሰሞኑን በሰጠው መግለጫም እንደገለጸው፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሰብዓዊ የርዳታ ተቋማት ጋር በመቀናጀት በተቆጣጠራቸው አካባቢዎች ሰብዓዊ ርዳታ እንዲደርስ እየሠራ ይገኛል። የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት በእነዚህ አካባቢዎች አገልግሎት ለመጀመር የሚያስችል ዝግጅት እንዲያደርጉ እያደረገ መሆኑን ገልጿል።

ከየአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር በመነጋገር ሕዝባዊ አስተዳደር የሚቋቋምበትንና ማኅበራዊ አገልግሎቶች የሚጀምሩበትን መንገድ እያመቻቸ እንደሚገኝ ማስታወቁ ይታወሳል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የትግራይ ሕዝብ እየተፈጠረለት ያለውን ዕድል በሚገባ ሊጠቀምበት ይገባል!

አሸባሪው ትሕነግ በትግራይ ሕዝብ ላይ ላለፉት አምስት አስርተ ዓመታት የፈጸመው ግፍ እና በደል በቀላሉ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም። ቢያንስ ቢያንስ አምስት ትውልድን ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዋጋ አስከፍሏል። ያደረሰበት ስነ ልቦናዊ ጫናውም በቀላሉ ሊገመት የሚችል አይደለም።

የትጥቅ ትግሉን በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሞቅታ በደደቢት በረሃ በነፃ አውጪነት ስም ሲወልደው፣ ለትግሉ ስኬት መነሻ እና መድረሻ አድርጎ የወሰደው የትግራይን ሕዝብ የተሳሳተ የፖለቲካ አካሄዱ መጠቀሚያ ማድረግ ነበር። ይህንን በመጠቀምም የተለያዩ የሐሰት ትርክቶችን ፈጥሯል።

እነዚህ ትርክቶች በአብዛኛው ለትግራይ ሕዝብ ጠላት መፍጠር ላይ ያተኮሩ ፤በማርክሲዝም ሌኒኒዝም የመደብ ትንታኔ ገዥና ተገዥ መደቦችን በመፍጠር በመካከላቸው ያለው ተቃርኖ ያለጠበንጃ /ከአንዱ መጥፋት ውጪ/ሊፈታ እንደማይችል በመስበክ ላይ የተመሠረቱና በዚህ አስተሳሰብ የተቃኘ ትውልድ መቅረፅ ላይ ያተኮሩ ነበሩ ።

ይህ ገና ከጅማሮው ከትግራይ ሕዝብ ባህልና እምነት፤ ከሁሉም በላይ ሕዝቡ ከሚመካባቸው ኢትዮጵያዊ እሴቶች ጋር የማይጣጣመው የቡድኑ የፖለቲካ አካሄድ በሕዝቡ ተቀባይነት ባያገኝም ፣ቀስ በቀስ በወቅቱ በነበረው የፖለቲካ ሥርዓትና በቡድኑ ሴራ በሕዝቡ ላይ አስገዳጅ በሆነ መልኩ ተጭኗል።

በዚህም ሕዝቡ አሸባሪው ትሕነግ ከውልደቱ ማግስት ጀምሮ ጠላት አድርጎ ከፈጠረለት /ከሳለለት/ ኃይሎች ጋር ጎራ ለይቶ በነጻነት ስም ለቡድኑ ፍጹም ባሪያ ለሚያደርገው የሕይወት መስዋዕትነት ራሱን አሳልፎ ለመስጠት ተገዷል። በዚህም የከፈለው ዋጋ ልጆቹን ከማሳጣትና ከመጎሳቆል በቀር ያተረፈለት ነገር የለም ።

ያ በነጻነት ተስፈኝነት ስም የተጀመረው የአሸባሪው ትሕነግ የትጥቅ ትግል በቡድኑ አሸናፊነት ሲጠናቀቅ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ወጣቶችን ሕይወት ከመቅጠፍ ፤በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩትን አካለ ጎደሎ ከማድረግ ባለፈ ለትግራይ ሕዝብ እንደተባለውና እንደተሰበከው የፈጠረለት ነገር አልነበረም።

በወቅቱ የተፈጠረው መንፈስ የትግራይን ሕዝብ የነጻነቱ ባለቤት ያደርገዋል የሚለው የታጋዩ ተስፈኝነት ብዙ ሳይቆይ በድሉ ማግስት ወደ ቅዠት ተለውጧል። አብዛኛው ታጋይ ጓዶቹ የተሰዉለት ትግል ፍጻሜው አዲስ አምባገነናዊ የገዥ መደብ በመፍጠር ስለመጠናቀቁ የራሱ የሕይወት ተሞክሮ አርድቶታል።

ሕዝቡም ቢሆን በድሉ ማግስት የጀመረውን የነጻነት ዜማ አጣጥሞ ሳያበቃ፤ በትግሉ የተሰዉ ልጆቹን መርዶ ሰምቶ ኃዘኑን ሳይጨርስ ፤የአዲስ አምባገነናዊ አገዛዝ ሥርዓት ቀንበር ተጭኖበት፤ በራሱ ጉዳይ የመናገር ፍጥረታዊ መብቱን ተነጥቆ የቡድኑ የፖለቲካ መቆመሪያ ካርድ ለመሆን ተገዷል።

ብዙዎች በላቀ ተስፈኝነት ዋጋ የከፈሉለት የነጻነት ትግል ትሕነጋዊ አምባገነናዊ ሥርዓት ከመፍጠር ባለፈ ፤ ጥቂት የሥርዓቱ አባላትን የሚጠቅም የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሥርዓት በመፍጠር መላው ሕዝብ /የትግራይን ሕዝብ ጨምሮ / በሀገሩ ጉዳይ የበይ ተመልካች የሚሆንበትን ሀገራዊ ዐውድ ፈጥሮ ቆይቷል።

ከሁሉም የሚከፋው ደግሞ አሸባሪው ቡድን የፈጠረውን ትሕነጋዊ አምባገነናዊ ሥርዓት እና ጥቂት የሥርዓቱ አባላትን ሁለንተናዊ ተጠቃሚ የሚያደርገውን የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሥርዓት ለመጠበቅ የትግራይን ሕዝብ መያዣ አድርጎ የመውሰዱና ለዚህም ሕዝቡ ተጨማሪ ዋጋ እንዲከፍል ማስገደዱ ነው ።

ቡድኑ ለትግራይ ሕዝብ በተለያዩ ትርክቶች ጠላት በመፍጠርና ራሱን የትግራይ ሕዝብ ጋሻ አድርጎ በመሳል ሕዝቡ ስለ ራሱ በነጻነት እንዳያስብ ከማድረግ ባለፈ ፤በራሱ እንዳይተማመን ከዚህ ይልቅ ተስፋ ቢስ ሆኖ ለቡድኑ ሕልውና ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍል አድርጎታል ። ዛሬም በተመሳሳይ መልኩ እየሆነ ያለው ይኸው ነው ።

ገና ከፍጥረቱ ጀምሮ የትግራይን ሕዝብ የፖለቲካ መቆመሪያ ካርድ አድርጎ የወሰደው አሸባሪው ትሕነግ በዚህ የጥፋት መንገዱ የትግራይን ሕዝብ ቀደም ባለው ዘመን ሆነ አሁን ያስከፈለው እና እያስከፈለው ያለው ዋጋ መራራ ፤ ከሕዝቡም የመሸከም አቅም በላይ ነው።

የትግራይ ሕዝብ እንደ አንድ ትልቅ ሕዝብ ይህን ተጨባጭ እውነታ በአግባቡ በመረዳት የቡድኑ መቆመሪያ ካርድ ያደረገውን ክፍተት በማጥበብ የራሱ ዕጣ ፈንታ ባለቤት ሊሆን ይገባል። በተለይም ዛሬ ላይ በብዙ መስዋዕትነት በእጁ እየገባ ያለውን ነፃነቱን በመስዋዕትነት ላለፈው ትውልድ ሕልም ስኬት አልፋና ኦሜጋ አድርጎ መውሰድ ይጠበቅበታል!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ:- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ኅብረታችን ከመንግሥታችን

ራስወርቅ ሙሉጌታ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ ላይ በፖለቲካ በኢኮኖሚና ማኅበራዊ መስኮች በችግር ውስጥ ትገኛለች። ችግሩ ያልነካው ወይንም የማይነካው ግለሰብም ሆነ ማኅበረሰብ አይኖርም። ችግሩ የሁላችንም መሆኑ ደግሞ ለመፍትሔውም የሁላችንም ተሳትፎ እንደሚያስፈልግ አመላካች ነው። በመንግሥት በኩል ለነገዋ ነጻና ዲሞክራሲ የሰፈነባት ኢትዮጵያ ይበጃል ተብሎ የታመነበት ሁሉ ከፖሊሲ እስከ መመሪያ እየወጣና እየተተገበረ ይገኛል።

የችግሩ ስፋትና ጥልቀት ግን ከላይ እንደጠቀስኩት በፖሊሲና በመመሪያ በመንግሥት እንቅስቃሴ ብቻ የሚቀረፍ እንደማይሆን ያሳለፍናቸው ዓመታት አሳይተውናል። ዛሬ ወያኔና በቀቢጸ ተስፋ ውስጥ ያሉ ደጋፊዎቹ በጦር አውድማ አልሳካ ያላቸውን እኩይ ዓላማ በሽብርና በኢኮኖሚ አሻጥር ለማሳካት እየተንደፋደፉ ይገኛሉ።

የዚህ ሥራቸው የመጨረሻ ግብ ሕዝብ በየመንደሩ በሚፈጸሙ ወንጀሎች፤ የሽብር ሥራዎችና የኑሮ ውድነት ተማሮ በመንግሥት ላይ እንዲዘምት፤ ያንንም ተከትሎ በሀገሪቱ ቀውስና አለመረጋጋት እንዲፈጠር ለማድረግ ነው። እኛ ደግሞ ከሽብሩም ከኑሮ ውድነቱም ከወንጀሉም ጀርባ በዘላቂነት ሊያጠፉን ያሰፈሰፉ ጠላቶች እንዳደሉን በመገንዘብ ሳንማረር ከመንግሥት ጎን በመቆም ልንታገላቸው ይገባል። በተለይም ንጹሐንን በግፍ እየገደሉ እያፈናቀሉ ራሳቸው የዚህ ብሔር ፤ የዚህ ጎሳ ወገን ተጨፈጨፈ አለቀ ሲሉን እኛ «ኢትዮጵያዊ ሞተ» ብለን ራሳቸውን አንገት ልናስደፋቸው ይገባል።

በሌላ በኩል የምዕራባውያኑ መገናኛ ብዙኃንና መንግሥታት በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ላይ እጃችንን ካልጠነቆልን እያሉ ይገኛሉ። ወያኔ በጦርነቱ የበላይነት ያሳየ ሲመስላቸው ጉድጓዳቸው ውስጥ የሚሸሸጉት የዘመናዊ ቅኝ ግዛት ፍላጎት ያናወዛቸው ሀገሮች መንግሥት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት እንደማያስደፍር ሲገባቸው ዳግም ከተሸሸጉበት ብቅ ይሉና በሁሉም ሚዲያዎቻቸው ፕሮፖጋንዳቸውን ያጧጡፉታል።

የውሸት ዜናዎችን እየፈበረኩ በቀን በቀን ይለቃሉ። ሰላም በሚፈልግና በዲፕሎማሲያዊ ምክክር መንግሥት ላይ ጫና ለማሳደር ደጅ መጥናታቸውን ያበዙታል። አንዳንዴ ምክር አለፍ ሲልም ማስፈራሪያ ንግግራቸውን ሳያቋርጡ ያደርሱናል። በጥቂት ወዳጅ ሀገሮች ፍትሐዊ የሕሊና ፍርድ በፀጥታው ምክር ቤት በተደጋጋሚ ከሸፈባቸው እንጂ ኢትዮጵያን ዳግም እንዳትጠገን አድርገው የማፍረስ ሕልማቸውን ለማሳካት ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም።

ይህንን ሙከራቸውን ወደፊትም የሚያቆሙት አይመስልም። በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ኢትዮጵያ ድምፅ እንዳይኖራት፣ የኢኮኖሚ ጫና ውስጥ እንድትገባ እና ሌሎች ሀገሪቱን ያንበረክካል ያሉትን ሙከራዎች በሙሉ ተግባራዊ ሲያደርጉ እየተመለከትን ነው። ይህ ቀጥተኛ የውጪ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት በሕዝቡ አንድነት፣ በመከላከያ ደጀንነትና በወዳጅ ሀገራት ትብብር እንደማይሳካ በተደጋጋሚ እየታየ ይገኛል።

አሁንም ቢሆን መላው የኢትዮጵያ ዜጎች ይህን በሚገባ በመረዳት የኢትዮጵያ መንግሥት የአሸባሪውን ወያኔ ሀገር የማፍረስ ቅዠት ለማክሸፍ የሚያደርገውን ርብርብ በሙሉ ኃይል ልንደግፍ ይገባል ። የመከላከያ ሠራዊት የሚወስደውን እርምጃ በሞራል፣ በጉልበት አለፍ ሲልም በኢኮኖሚ መደገፍና ድሉን ማፍጠን የሕዝቡ ኃላፊነት ነው።

አሸባሪው ትሕነግ በጦር ግንባር ከሚያደርገው ወረራ ባሻገር የምጣኔ ሃብቱን ለማሽመድመድ በርካታ ሴራዎችን በድብቅ በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ደጋፊዎቹ ጋር በማበር እየሠራ መሆኑ እሙን ነው። ይህንን ተከታትሎ ማክሸፍና ድሉን ሁለንተናዊ ማድረግ ያሻል። ይህን ሥራ መንግሥት ብቻውን ሊያከናውነው እንደማይችል እርግጥ ነው።

ለዚህም ማኅበረሰቡ የምጣኔያዊ አሻጥር ውስጥ የሚገቡ አካላትን በማጋለጥና እግር በእግር በመከታተል መጠቆም አለበት። ይህ ሲሆን የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ከውጭና ከውስጥ ለመገዳደር የሚሞክሩ ጠላቶችን በቀላሉ መርታት ይቻላል። በተጨማሪ ምዕራባውያን መገናኛ ብዙኃን ከርቀት የሚያደርጉትን የሳይበር ጦርነት መመከት ከኅብረተሰቡ የሚጠበቅ ነው። በተለይ ለፕሮፖጋንዳዎች ጆሮ ባለመስጠት፤ አለፍ ሲልም ሴራውን በማጋለጥ ሂደት ላይ መሳተፍ ያስፈልጋል።

ወያኔም ሆነ ምዕራባውያን የሚዘምቱብን ከማእቀብ ጀምሮ እኛን ለማንበርከክና አንገት ለማስደፋት የተመቻቸውን ያዋጣናል የሚሉትን በሙሉ በማድረግ ነው። ይህ ደግሞ ሀገራችንንና ሕዝቧን በተለያዩ ችግሮች ውስጥ እንዲያልፉ ማድረጉ አይቀርም። በዚህም ከሞራል ጀምሮ ከሚደርሰው ጉዳት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ተቋዳሽ ከመሆን ባሻገር የከፋው ነገር ሲፈጠርም በእሳቱም መለብለቡ አይቀሬ ነው።

በእሳቱ ብርሃንና ሙቀት የሚጠቀሙትና የሚደሰቱት የቅርብ ጠላቶቻችንና አንዳንድ አውሮፓውያን ብቻ ናቸው። ይህንን ግን ወያኔዎችና አባሪዎቻቸው በቅጡ የተረዱት አይመስልም። በመሆኑም እነዚህን ጠላቶቻችንን ከመንግሥት ጎን በመቆም የምንታገለው ማንንም ለማስደሰት አልያም የተለየ ጥቅም ለማግኘት ብለን ሳይሆን ራሳችንን፤ ሀገራችንንና ትውልድ ለመታደግ መሆኑን ማመን አለብን።

እንደዚህ አይነት ተደራራቢ ቀውሶች በማንኛውም ግዜ በየትኛውም ሀገር ሊከሰቱ ይችላሉ። ከአፍሪካ እስከ መካከለኛው ምስራቅ ተከስተውም አይተናል። የኛን ለየት የሚያደርገው ግን ለሁሉም ችግሮች መፈጠርና መባባስ ምክንያቱ የሀገራችን ጠላቶች ተላላኪ የሆነው ወያኔ መሆኑ ነው።

የወያኔ ባለስልጣናት ዛሬም ሞት አፋፍ ላይ ሆነው ገና በጨቅላነታቸው የሄዱበትን መንገድ በስተእርጅናም ተያይዘውታል። የት እንደሚያደርሳቸው የሚያውቀው ግን ዲያቢሎስ ብቻ ይመስለኛል። የትግራይ ምድር በወያኔ ተንኳሽነት እስካሁን ካሳለፉቸውም ሆነ ወደፊት ከሚያሳልፉቸው ጦርነቶች ውድ ልጆቹን ከመገበርና ሕዝቡን በስቃይ ከማቆየት ውጪ ምንም ጥቅም ሊያገኝ አይችልም።

የትግራይ ሕዝብ ከመቼውም ግዜ በላይ ዛሬ በትልቅ የችግር አረንቋ ውስጥ ተዘፍቋል። የወያኔ ሥራ ደግሞ እየፈጠረ ያለው ጥላቻ በጦር ሜዳ ውሎ ብቻ ሳይሆን የትግራይንም ሕዝብ እንደ ሕዝብ ከቀሪው የኢትዮጵያ እህት ወንድሞቹ ጋር ደም የሚያቃባና የሚያቀያይም ነው። እዚህ ላይ በቀሪው ቦታ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምላሽ ሊሆን የሚገባው ወያኔንና የትግራይን ሕዝብ ለይቶ ማየት ነው።

ትግራይ ታሸንፋለች የሚለው የወያኔ ድንፋታ መነሻው ይህ ካልሆነ «ትግራይ በቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተሸንፋ ትዋጣለች» በሚል እሳቤ ለትግራይ ሕዝብ እየተነገረው እንደሆነ በተደጋጋሚ ሰምተናል። እውነታው ግን በወያኔ መደምሰስ ኢትዮጵያ የምታሸንፈው ለትግራይ ሕዝብ የድል የነጻነትና የዲሞክራሲ ሻማ በማብራት ነው።

በመሠረቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሕዝቦች ሁሉም በየዘመናቱ በአስተዳዳሪዎች በርካታ ችግሮች እንደደረሰባቸው ይታወቃል። ይህ ማለት ግን አንዳንድ ብሔርና ጎሳ ተኮር ፖለቲከኞች እንደሚያራግቡት በኢትዮጵያ በሕዝብ ላይ የዘመተ ሕዝብ ኖሮ አያውቅም። በመሆኑም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አሕመድ በቅርቡ እንደተናገሩት የሰሜኑ ጦርነት እንዲጠናቀቅና ኢትዮጵያና እኛ ሕዝቦቿ ሰላም እንድናገኝ በያለንበት የሚጠበቅብንን ልንወጣ ይገባል እላለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# የሽብርተኛው ትህነግ ክፉ መንፈስ

በለንደን እምብርት ላይ በተገነባው የእንግሊዙ የዜና ማሰራጫ BBC ዋና መስሪያ ቤት መግቢያ ደጃፍ ላይ በእጁ ሲጋራ የያዘ የጆርጅ ኦርዌል የነሐስ ሀውልት በግርማ ቆሟል። ከግርጌው ጥቅሱ ሰፍሯል። «ነፃነት ሌላ ምንም አይደለም። ሰዎች መስማት የማይፈልጉትን የመናገር መብት ነው» ይለናል። እኔም በዛሬ መጣጥፌ መስማት የማትፈልጉትን ነገር የመናገር መብቴን ተጠቅሜ ልነግራችሁ ነው።

ሰሞኑን በማህበራዊ ሚዲያዎች የሽብርተኛው ትህነግ ጥቂት ገዢዎች ለድርድር እንደወጡ በዚያው እንዲቀሩ የሚመኙ ምኞቶችን በስፋት ሲዘዋወሩ ተመለከትሁ። አንዳንድ መደበኛ ሚዲያዎችና ዩቲውበሮች ደግሞ ከደርግና ከትህነግ ጋር በጂሚ ካርተር አደራዳሪነት ለንደን ላይ ከተደረገ የይስሙላ የመጨረሻ ድርድር ጋር እያነጻጸሩ የደቡብ አፍሪካውን መንገድ የማራሚያ መንገድ አድርጎ እስከማየት ከመድረስ ባሻገር ታሪክ ራሱን ደገመ እስከማለት ደርሰዋል።

ንጽጽሩ ከመነሻው ዘመነ ጓዴነት የሚጎድለውና ለአቅመ ሙግት ስለማይበቃ እዚህ ላይ ልለፈው። ይህ በምኞት ላይ ያነጻጸረ ምኞት እንዳይበርደው የእኔን ልደርብለት። መቼስ ምኞት አይከለከል አይደል፤ የእኔ ምኞት ለሀገሬ ፡- በሕግ ተይዘው የነፈጉንን ፍትሕ አግኝተው፤ ጥፋተኝነታቸው ከተረጋገጠ በኋላ የሀገራዊ ምክክሩ አካል ሆነው፤ ኅልቆ መሳፍርት የሌለው ግፍና ሰቆቃ የፈጸሙበትን ሕዝብ እና ደጋግመው ከጀርባ የወጓትን እናት ሀገር ይቅርታ ጠይቀው፤ ለእነዚህ እኩያን ተግባራት በማጣቀሻነት ይጠቀሙባቸው የነበሩ ጥቋቁር መጽሐፎቻቸው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲዘጉ፤ «በእኛ ይብቃ ትውልድ ይዳን፤» እንዲሉ ነው።

ወደተነሳሁበት ነጥብ ስመለስ አመራሮቹ እንደወጡ ቢቀሩ፤ ለግማሽ ክፍለ ዘመን መዋቅራዊና ተቋማዊ አድርገው በትግራዋይም ሆነ በሌላ ማህበረሰብ የዘሩት ጥላቻ፣ ልዩነት፣ ሀሰተኛ ትርክት፣ ኩርንችትና አሚካላ አብሯቸው አይወጣም። አይሰደድም። እነሱ እንደወጡ ከቀሩ እዳው ገብስ ነው የሚለው ሀሳብ ውሃ አያነሳም፤ የሽብርተኛው ትህነግ ክፉ መንፈስና አመለካከት ከገዢዎቹ አልፎ በማህበረሰብም በትውልድ የተጋባ መሆኑን በውል ካለመረዳትና መገንዘብ የተቀነቀነ ገራገርና የዋህ ሀሳብ አድርጌ ነው የወሰድሁት።

አይደለም በጣት የሚቆጠሩ ገዢዎች በየደረጃው እስከ ጎጥ ያሉ የ1ለ5 ጠርናፊዎች ሳይቀሩ በሆነ ተአምር ብን ብለው ከትግራይና ከመላው ኢትዮጵያ ፖለቲካዊ መልክዓና አየር ቢጠፉ ክፉ ሀሳቡና የተሳሳተ ትርክቱ ላልተወሰነ ጊዜ አብሮን እንደሚኖር ያለምንም ማቅማማትና ማወላወል ተቀብለን፤ ለወታደራዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ድሉ የሚጠበቅብንን እልህ አስጨራሽ ትግል የምናፈሰውን ሀብት፣ ጉልበትና ጊዜ ያህል፤ የሽብርተኛውን ክፉ መንፈስና የተሳሳተ አመለካከት ከአብዛኛው ትግራዋይ አስተሳሰብ ለማስጣል እንደሚያስፈልገን አበክረን አስበንና አቅደን መሥራት ይጠበቅብናል። ተገዶም ሆነ ፈቅዶ የሽብርተኛውን ክፉ መንፈስና የተሳሳተ ትርክት እንደ ቀኖና የተቀበለ፤ እንደ ክፉ ደዌ በሰራ አካላቱ የተሰራጨበት ትግራዋይ ቁጥር ቀላል አይደለምና ከፊታችን ገና ከባድ ፈተና ይጠብቀናል።

ከኢትዮጵያና ከእውነት አምላክ ጋር ተገደን የገባንበት ጦርነት በእኛ አሸናፊነት እየተቋጨ ነው። የድህረ ጦርነቱ ዳፋ ግን ላልተወሰነ ጊዜ አብሮን ይኖራል። አሸባሪውና ከሀዲው ሕወሓት የትግራይን ሕዝብ ይዞ ለመጥፋት ታጥቆ እየማሰነ ነው። ትግራይን ሴቶችና ጨቅላዎች ብቻ የሚባዝኑበት የመናፍስት ክልል ሊያደርገው ቆርጦ ተነስቷል። እያደረገውም ነው። አሁንም ባለቀ ሰዓት እንኳ በፈጣሪ ምህረት የተራረፈውን ወጣት ለማስጨረስ ትህነግ ጉድጓዱ ከተማሰ ልጡ ከተራሰ በኋላ እንኳ ለማስጨረስ በዚህ ሰዓት መርዙን እየነዛ ነው። መጀመሪያ ወጣቱን በመቀጠል ሕፃናትን ከዚያ አረጋውያንንና አካል ጉዳኞችን በጦርነት እየማገደ እየጨረሳቸው ነው።

በእብሪትና በማንአለብኝነት እያስገደደና እያታለለ ትግራዋይን በሕዝባዊ ማዕበል በየግንባሩ እየማገደ እያስፈጃቸው ነው። አሸባሪው ሕወሓት ካፈርሁ አይመልሰኝ ብሎና ተስፋ ቆርጦ ትግራዋይን ይዞ እየሞተ ነው። ከዚህ የከፋና የባሰ ምን ይመጣል በሚል ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ጣዕረ ሞት ላይ ሆኖ እንኳ ትግራይን የወላድ መካን እያደረጋት ነው። በ17 አመቱ ጦርነት 70ሺህ ልጆቹን በመነጠቁ ጧሪና ቀባሪ ማጣቱ ሳያንስ ዛሬ የተረፉ ልጆቹና የልጅ ልጆቹ ትርጉም ለሌለው ጦርነቱ ተማግደው ሲያልቁ ዛሬ ተረኛው እሱ ሆኗል።

አሸባሪውና ከሀዲው ትህነግ የእሱን ተስፋ መቁረጥ ወደ ሕዝቡ በማጋባት ስለነገ ሕይወቱና ኑሮው ተስፋ እንዲቆርጥና እንዳይጨነቅ በማድረግ፤ ከአማራ ከኤርትራ ከአፋርና ከተቀረው ኢትዮጵያዊ ጋር ተቆራርጦ ከጎኑ እንዲሰለፍ እያደረገ ይገኛል። ሆኖም የተረፈውን ትግራዋይ ከአሸባሪው ሕወሓት መንጋጋ ለመታደግ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጠላትነት እንደማያየው ለማረጋገጥና የአሸባሪው ሕወሓትን ሰንኮፍ ለመንቀል የትግራዋይን ልብ ስለመማረክ አበክሮ ማሰብና መሥራት ይጠይቃል። የጸረ ሽብር ትግሉ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው የትግራዋይን ልብ በመማረክ ሲታጀብ ነውና።

የጸረ ሽብር ትግል በአውደ ወጊያ በሚቀዳጁት ድል ብቻ አይረጋገጥም። የአሸባሪው ፖለቲካዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሠረት የሆነውን ሕዝብ ልቦና እና አመለካከት ከወዲሁ መማረክ ግድ ይላል። አሸባሪውን ከሕዝብ የመነጠል የተቀናጀ ርብርብ ይጠይቃል። አሜሪካ ለ20 አመታት ከ2 ትሪሊዮን ዶላር በላይ ገፍግፋ በብዙ አስር ሺዎች የሚቆጠሩ ወታደሮቿን ሰውታና አካል ጉዳተኛ አድርጋ በባዶ እጇ አጨብጭባ ተሸንፋና ተዋርዳ የወጣችው የአፍጋኒስታውያንን ልቦና ማሸነፍ ባለመቻሏ ነው። የግንባሩን አውደ ውጊያማ ከ20 አመት በፊት ታሊባንን አይቀጡ ቅጣት ቀጥታ አሸንፋ ነበር።

በኢራቅ፣ በሶሪያ፣ በሶማሊያ፣ በየመን፣ በሊቢያ፣ በናይጄሪያ፣ በማሊ፣ በሞዛምቢክ ወዘተረፈ አሸባሪዎችን በቀላሉ ማሸነፍ ያልተቻለው ለዚህ ነው። አሸባሪዎችን በጦርነት ለማንበርከክ ከሚደረገው ፍልሚያ ባልተናነሰ ርዕዮተ ዓለማቸውን እንደ ሰብዓዊ ጋሻ ከሚጠቀሙበትና በአካልም በሥነ ልቦናም ካገቱት ሕዝብ ማውጣትና ማጽዳት ይጠይቃል። በአሸባሪው ሕወሓት ላይ ከሦስት ሳምንታት ባነሰ ጊዜ የተቀዳጀነውን አንጸባራቂና በጥብቅ ወታደራዊ ዲሲፕሊን የተዋጀውን ድል ማጽናት ያልቻልነው የትግራዋይን ልቦና በቅጡ ባለመማረካችን ነው። አሁንም የማይቀረውን ወታደራዊ ድል ለማጽናትና ለማዝለቅ ከወዲሁ የትግራዋይን ልብ በማሸነፍ ልናጅበው ይገባል። ይበል የሚያሰኙ ሕዝባዊ ውይይቶችና ሌሎች ጅምሮች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው። ከሸኔ፣ ከጉሙዝ ታጣቂዎችና ከሌሎች አሸባሪዎችና ሽፍቶች ጋር የምናደርገውን ትግልም እንደዚሁ።

በውል ባንገነዘበውም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ወደ ኃላፊነት ከመጡበት ሰዓት አንስቶ የኢትዮጵያውያንን በተለይ ደግሞ የትግራዋይን ልብና አመለካከት ለማሸነፍ ብዙ ጥረዋል። ሩቅ መንገድ ተጉዘዋል። ዋጋም ከፍለዋል። ለሰላም ካላቸው ቁርጠኝነትና ጦርነት ምን ያህል አስከፊ እንደሆነ በውትድርና ሕይወታቸው ጠንቅቀው ስለሚያውቁት፤ ጓደኞቻቸውንና ወንድማቸውን ስለነጠቃቸው፤ ጦርነት የአገርን ኢኮኖሚ ምን ያህል እምሽክ ድቅቅ እንደሚያደርግና እንደሚያወድም አበክረው ስለተገነዘቡና የትግራይ ሕዝብም ጦርነት ይበቃዋል በሚል ጽኑ እምነትና የጦርነት ነጋሪት የሚጎስሙ ኃይሎች የድሀን ልጅ የእሳት ራት ያደርጋሉ እንጂ እነሱ አይዋጉም በማለት ለትግራይም ሆነ ለሌሎች ሕዝቦች ደህንነት ሲሉ እስከ መጨረሻው ሰዓት ሆደ ሰፊነትንና ትዕግስትን መርጠዋል።

አበው «ጎሽ ለልጇ ስትል ተወጋች» እንዲሉ በከሀዲውና የእናት ጡት ነካሹ በሆነው ትህነግ መከላከያችን ፣ ሉዓላዊነታችን ፣ አገራችንና ሕዝባችን ለሰላም በታመኑ ከጀርባ ተወጉ። ባጎረሱ ጣታቸውን ተነከሱ። አሸባሪው ሕወሓት በእብሪት በጫረው እሳት ክቡር የሆነው የሰው ልጅ ሕይወት ጠፋ፤ አካል ጎደለ፤ የአገር ኢኮኖሚ ክፉኛ ደማ፤ የሽብር ኃይሉ ያወደማቸውን የመሠረተ ልማቶች መልሶ ለመጠገን ብቻ ከ100 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ሆነ። አሁንም ከዚህ ያልተናነሰ የመልሶ ግንባታ ወጪ ይጠይቀናል።

ዛሬም ጥምር ኃይሉ በየደረሰበት ሽብርተኛው ሕወሓት ከትግራዋይ ጉሮሮ ቀምቶ ለሰራዊቱ ስንቅ ሊያውለው የነበረውን እና ከመሐል አገር የገባውን የዕለት ደራሽ እህል እያሰራጨ ነው። በወረራው ለተፈናቀሉ ወገኖች ዕለታዊ እርዳታ ለማቅረብ ወደ 10 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ወጪ ተደርጓል። ልብ አድርጉ ይህ ወታደራዊውን ወጪ አይጨምርም። ጥገና ሲያካሒዱ የነበሩ የኢትዮ ቴሌኮምና የኤሌክትሪክ ኃይል ባለሙያዎች በግፍ ተገደሉ። ይህ የትግራዋይን ልብ የማሸነፍ ጥረት አካል ነበር። መንግሥት ከስምንት ወር ቆይታ በኋላ ለሰብዓዊነት ሲል የተናጠል የተኩስ አቁም ያወጀውም ለዚሁ ሰናይ አላማ ነበር።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አገሪቱን ከጠብ መንጃ አዙሪት ለማውጣትና ከዚህ ቀደም የነበሩ ገዥዎች ያልሄዱበትን የሆደ ሰፊነትና ቁጭ ብሎ የመነጋገር አዲስ መንገድ በመምረጣቸው በልኩ እውቅና ሊሰጣቸውና አብዛኛው ዜጋ ከጎናቸው ሊቆም ሲገባ መንግሥታቸው በልፍስፍስነት ከመወቀሱ ባሻገር ፓርቲያቸውም ሆነ እሳቸው ቁጥሩ ቀላል ያልሆነ ደጋፊያቸውና ተከታያቸው ብዥታና ድንጋሬ ላይ እንዲወድቁ አድርጓል።

እነዚህ ሁሉ ጥረቶች የትግራዋይን ልብ ለመማረክ የተደረጉ እንቅስቃሴዎች እንደነበሩ ግንዛቤ አልተያዘም። ይሁንና የእፉኝቱ ትህነግ የጥቅምት 24ቱን ታላቅ ክህደት ተከትሎ የሕግ የበላይነትን ለማስከበርና የአገር ህልውናን ለማስቀጠል ያሳዩት ቁርጠኝነት እና ሰራዊቱ ከተፈጸመበት ታሪክና ትውልድ ይቅር ከማይለው ክህደት በኋላ ሞራሉና ወኔው አንሰራርቶ በእልህና በቁጭት ተነሳስቶ እጅን በአፍ የሚያስጭን አንጸባራቂ ድል በማስመዝገቡ አገራዊ ሞራሉ እንዲያንሰራራ አድርጓል።

እፉኝቱ ትህነግ ይታበይበትና ይመካበት የነበረውን ልዩ ኃይልና ሚሊሻ አይቀጡ ቅጣት ቀጥቶ በሦስት ሳምንታት ውስጥ ኅዳር 19 ቀን 2013 ዓ.ም መቐሌ ሊገባ ችሏል። ለዛውም እጅ የመስጫ የመጨረሻ ቀነ ገደቡን ጨምሮ ስድስቱ ቀናት ሳይታከሉ። በሁለተኛው ወረራም ጣርማ በር ደርሶ የነበረው ወራሪ በሳምንታት ተጠራርጎ እንዲደመሰስና እንዲወጣ ተደርጓል።

## እንደ መውጫ

አሸባሪው ትህነግ እንደ ሰብዓዊ ጋሻና እንደ መደበቂያ የሚጠቀምበትን የትግራዋይ ልብና አመለካከት ማሸነፍ ሳይቻል ወታደራዊ ድሉ ሙሉኡ አይሆንም። በጦር ሜዳ የሚገኘው ወታደራዊ ድል የትግራዋይን ልብና አመለካከት በማሸነፍ ካልታጀበ የአሸባሪው ሕወሓት መደምሰስ ብቻ ድሉን ዘላቂና አስተማማኝ አያደርገውም። የኢፌዴሪ መንግሥት ከጦርነቱ ባልተናነሰ የትግራዋይን ልብና አመለካከት ለማሸነፍ የተግባቦት ስልት ነድፎ ሌት ተቀን መሥራት አለበት። ደጀኑን ሕዝብ ዳር እስከ ዳር ለማነቃነቅ እና የአሸባሪው ትህነግ ጭካኔና አገር የማፍረስ ደባ ለማጋለጥ እየሠራው ባለ ልክ የትግራይ ሕዝብን ለመማረክም በአግባቡ መንቀሳቀስ አለበት።

ለ50 አመታት ያህል እንደ መዥገር ደሙን ከሚመጠው፤ የወላድ መካን ካደረገው፤ በአንድ ለአምስት አደረጃጀት ጠርንፎ በአፈናና ጭቆና ባሪያ ካደረገው፤ ከኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ጋር ደም እያቃባው ካለ፤ በስሙ እየማለና እየተገዘተ የቡድናዊ ጥቅም ማሳደጃ ካደረገው፤ ወዘተረፈ ይልቅ ከተቀረው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር በእኩልነት በፍቅር በሰላም በነፃነትና በአንድነት የመበልጸግ አቅምና ተስፋ እንዳለው፤ ለአሸባሪው ትህነግ ግለኛ ጥቅም ሲባል ልጆቹ ከጉያው እየተነጠቁ ለጦርነት እንደማይማገዱ፤ የትግራዋይ ዕጣ ፈንታ ከተቀረው ኢትዮጵያዊ ጋር በመስዋዕትነት የተሳሰረና የተገመደ መሆኑን ደጋግሞና በጥበብ አዋዝቶ በመግለጽ ልቡንና አመለካከቱን ማሸነፍ አለበት።

በስሙ እየማለና እየተገዘተ ለ27 አመታት አገርንና ሕዝብን በጠራራ በአደባባይ እየዘረፈ ራሱን ሲያበለጽግ እሱን ከድህነት አረንቋ ከሴፍቲኔትና ከተረጂነት ነፃ እንዳላወጣው፤ አንድ ጊዜ ዐቢይ ሊያንበረክክህ ነው ሌላ ጊዜ አማራ ሊያጠፋሽ ነው እያለ ፤ በተሳሳተ ትርክትና ቁጭት ሲያታግለውና ሲማግደው የኖረው ፤ ከተደቀነብህ አደጋ የምታደግህ እኔ ብቻ ነኝ የሚለው ለግል ጥቅሙና ከተጠያቂነት ለማምለጥ መሆኑን ደጋግሞ ማጋለጥ ያስፈልጋል።

# ወቅታዊ

# ‹‹አሸባሪው ትህነግ የተሸነፈው መከላከያ ሰራዊቱን ከጀርባው የወጋ ቀን ነው፤ እስከ ዛሬም ድረስ የሚውተረተረው በተሸነፈ ስነ ልቦና ነው››

- አቶ ቴዎድሮስ ሲሳይ
የኩሓ ወረዳ የቀድሞው የሠራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ

አስቴር ኤልያስ

አቶ ቴዎድሮስ ሲሳይ ተወልደው ያደጉትም ሆነ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተማሩት መቀሌ ሲሆን፣ ከመቀሌ ዩኒቨርሲቲም በምጣኔ ሀብት ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። ከምረቃ በኋላ ዕድሉን አግኝተው ከአንዳንድ ወጣቶች ጋር በመደራጀት በዚያው በመቀሌ የጌጠኛ ድንጋይ ሥራ ላይ ተሰማርተው ሠርተዋል። በጊዜያዊ አስተዳደር ውስጥ በመቐለ ዞን፣ በኩሓ ወረዳ የሠራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ሆነው አገልግለዋል። በዚያን ወቅትም ሕዝቡን ለማገልገል ታች ላይ ብለዋል። ከአቶ ቴዎድሮስ ጋር በአሸባሪው ትህነግ ባህሪ፣ አሁን እየተካሄደ ስላለው የሰላም ንግግር፣ በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ቃለ ምልልስ አካሂደን እንደሚከተለው አጠናቅረነዋል።


ፎቶ፡- አስቴር ኤልያስ

**አዲስ ዘመን፡- አሸባሪውን ትህንግ ጠንቅቀው የሚያውቁ አካላት አገር በመካድ ባህሪው ይታወቃል ይሉታል፤ እርስዎ የዚህን ቡድን ባህሪ እንዴት ይገጹታል? በተለይ ስልጣን ከመያዙ በፊት ከነበረው ባህሪው ቢጀምሩ?**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** የትህነግን ባህሪ በሦስት ከፍሎ ማየት ይቻላል። የትህነግ አባላት አብዛኞቹ የመሳፍንት ልጆች ናቸው። በወቅቱ በደርግ ዘመነ መንግሥት መሬት ላራሹ ታውጆ በነበረበት ጊዜ መሬታቸው ሊቀማ እንደሆነ ተረዱ። ስለዚህ በሁለት መንገድ መሬታቸው የሚመለስበትን ስሌት አካሄዱ። አንደኛ ከደርግ መንግሥት ጋር በመጠጋጋት ሲሆን፣ ይህም አካሄዱ በተለያየ የመንግሥት አደረጃጀት ውስጥ በመግባት ነበር። በዚህ መልክ እንደ ባለስልጣን ሆነው መሬታቸውን መጠበቅ ነበር። በዚህ ሁሉ ውስጥ ደግሞ በደርግ ባለስልጣን ውስጥ እስከ ጀኔራል ድረስ ያሉ ሰዎች ሁሉ በጉዳዩ ያግዟቸው ነበር። ሌላው ቀርቶ የአገር ሽማግሌ ብሎም የኃይማኖት አባት ሆነው ሳለ ያዟቸው የነበሩ አሉ። ይህ ሁሉ የተደረገበት ምክንያት መሬታቸውን ለማስጠበቅ ሲባል ነበር።

ሁለተኛ ደግሞ በዚህ መንገድ መሬታቸው የማያስጠበቅላቸው ከሆነ በረሃ ሆነው ደርግን በመታኮስና እረፍት በመንሳት ሀብታቸውን ማስጠበቅ ነበር። ይህ ጉዳይ በሒደት የፖለቲካ ይዘት እንዲይዝ ተደረገ። ፖለቲካው ደግሞ የደርግን መንግሥት አሃዳዊ ነው በማለት ፕሮፓጋንዳ በመሥራት የሚገለጽ ነበር። በተለይ ደርግ ጨፍጫፊ ነው፤ አጥፊ ነው፤ የትግራይን ሕዝብ አይወደውም፤ ፍትህ እያጓደለ ነው በሚል አዲስ ሥርዓት ያስፈልገናል ብለው መንግሥት መመስረት አለብን ወደሚል ድምዳሜ መጡ።

ስለዚህም ወደበረሃ ገብተው መታገል ቢጀምሩም ተጽዕኖ ፈጣሪዎች እንዲገደሉ አድርገዋል። የእነርሱ ተባባሪ ያልሆነና የኢትዮጵያዊ ስሜት ያለው ሁሉ እንዲገደልና እንዲጠፋ ያደርጉ ነበር። ፍላጎታቸው ብቻቸውን መቆጣጠር ነበርና ይህን አስተሳሰባቸውን አጎሉት። በዚህ መንገድ ለ17 ዓመታት ሲታገሉ በቆዩበት ሁሉ ኃይላችን ሕዝብ ነው፤ ገበሬ ነው ይሉ ነበር። ጠያቂና የተማረ አይፈልጉም። ገበሬው በተለያየ ፕሮፓጋንዳ እንዲሸወድ ያደርጉታል። ስለዚህ በዚህ ዓይነት በ1983 ዓ.ም አዲስ አበባ በመግባት ስልጣን መያዝ ቻሉ። በዚያን ወቅት ያልታገሉትን ዘመዶቻቸውን ጭምር ሽርጥ እያስለበሷቸው በዚህኛውና በዚያኛው ግንባር የታገለ ነው እያሉ ወደፈለጉበት ስልጣን ላይ ያወጧቸው ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- አሸባሪው ትህነግ በስልጣን ዘመኑ የነበረውንስ ባህሪ እንዴት ይገልጹታል?**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** ቡድኑ ከአደዋ ሁለት አውራጃ የተውጣጣ ነው። በኢትዮጵያ ታሪክም ይሁን በትግራይ ታሪክ ይህ ቡድን ወደስልጣን መጥቶ የማያውቅ ቡድን ነው። ስለዚህ በአንድ አጋጣሚ ያገኙት ስልጣን ከእጃቸው እንዳይወጣ የማይፈነቅሉት ድንጋይ አልነበረም። እቅዳቸውም ኢትዮጵያን መቶ ዓመት ለመግዛት ነበር።

ትግራይ ክልል ውስጥ ያለው ሕዝብ እንደየአውራጃው የተለያየ ስነልቦና ያለው ከመሆኑም በተጨማሪ በኢትዮጵያዊነት በጽኑ የሚያምን ነው። ነገር ግን ትህነግ ይህን የኢትዮጵያዊነትን ስነ ልቦና ማጥፋት ሥራዬ ብሎ የያዘው ተግባር ነበር። የተለያየ ስነ ልቦና ያለውንም በአንድ መጨፍለቅን ሙያው አደረገው።

በእርግጥ ጨርሰው ይህን ስነ ልቦና ማጥፋት እንደማይችሉ ስለሚያውቁ ወደእነርሱ ስነልቦና ማፍለስና ታሪኩን በመቀማት ሌላ ማንነት መስጠት ላይ ተግተው የሠሩበት ነበር። በፌዴራል ስልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ ወደስልጣን ያመጧቸው ጀኔራሎችም ቢሆኑ እነርሱን እንጂ የትግራይን ሕዝብ የሚወክሉ አይደሉም። እነርሱ በወቅቱ ራያም፣ እንደርታም የእነርሱ ወገን አይደሉም ብለው በማሰባቸው ‹ከራያ በሬ እንጂ ሰው አይወጣም ይሉ ነበር። እንዲሁም ከእንደርታ ‹ትልቅ አንባሻ እንጂ ትልቅ ሰው አይወጣም› እያሉ ሰውን ከበሬና ከአንባሻ ጋር ያነጻጽሩ ነበር። ከእነርሱ ወገን ሲሆን ግን ‹ያልተማረ አንድ አድዋ አገር ያስተዳድራል› ይላሉ። የአደዋ አራተኛ ክፍል የደረሰ ክልልና ዞን ቢያጣ ወረዳ አስተዳዳሪ መሆን ይችላል የሚሉ ናቸው። ይህን አስተሳሰብ የማይቀበለው ካለ ያሳድዱታል፤ ያጠፉታልም።

አሸባሪው ቡድን አንድን ሰው ሊያሳድድ ከፈለገ አስቀድሞ ክህደት ይፈጽምበታል። ፡ በተለይ ሌላ የሐሰት ታሪክ ይመሰርትና ከአሸባሪ ቡድን ጋር ነበር እያለ ማስወራት ይጀምራል። ይህንን ሥራህን ሕዝቡ እንዲያውቅ አደርጋለሁ፤ አሊያም አገር ለቀህ ሂድ ይባላል፤ ክህደት የተፈጸመበት አካል አሸባሪ ወይም የትግራይን ሕዝብ ከዳ ከመባል ይልቅ አገር ለቆ ይሰደዳል።

አሸባሪው ቡድን ሌላው ባሕሪው ደግሞ አንድ ሰው ከእነርሱ ለየት ያለ አመለካከት ካለው ሊያጠፋው ይፈልጋል። ሊያጠፋው ሲፈልግ ክህደት አይፈጸምበትም፤ ይልቁኑ ጀግና እያለ ማሞካሸት ይጀምራል። እዚህ ላይ የተሞካሸው ሰው በቡድኑ ሊገደል እንደሆነ ማወቅ አለበት ማለት ነው። በዚህ መልኩ ቡድኑ ከእርሱ በስተቀር ለ45 ዓመታት ሌላ ፓርቲም አደረጃጀትም እንዳይኖር አድርጓል።

ትህነግ የኢትዮጵያን ሕዝብንም ሲገዛ እየቀጠቀጠና እያሳደደ ነበር። የትግራይ ሕዝብን ደግሞ የተጫወተበት በስነ ልቦናው ነው። ለትግራይ ሕዝብ መብት የሚቆሙትን ሁሉ የሚያጠፉቸው መሣሪያ ደግኖ አይደለም፤ በትግራዋይ እንዲጠሉና የታገልክለትን ድርጅት ሊያፈርስብህ ነው በማለት እንዲያርቋቸው በማድረግ ነው። ሕዝቡ ደግሞ ማንነቴን ከሚያጠፋ ይህ ሰው መጥፋት አለበት ብሎ ያስባል።

አሸባሪው ኢትዮጵያ የሚለውን ስም የሚጠቀምበት እርዳታ ሊያገኝበት ወይ ጥቅማጥቅም ሊፈልግበት እንጂ አንድም የኢትዮጵያዊነት ስሜት ኖሮት አይደለም። ቡድኑ ለኢትዮጵያም ለትግራይም የሠራለት ነገር የለም። በረሃ እያለ በትግራይ ስም ነገደ። ወደስልጣን ሲመጡ ደግሞ በኢትዮጵያ ስም ነገደ። በመሠረቱ ቡድኑ ኢትዮጵያ ብሎ መጥራት የማያፈልግ ነው። ከጠራም ብሔር ብሔረሰቦች ብሎ ነው። አባላቱ ኢትዮጵያ የሚለው ስም አፋቸው ላይ በጣም ይከብዳቸዋል። መጥራት የሚፈልጉት አጋር ወይም እህት ድርጅት እያሉ ነው።

ሌላው ባህሪው ኢትዮጵያውያን እርስ በእርስ እንዳይስማሙ ለአንዱ ስልጣን ለሌላው ደግሞ ገንዘብ ይሰጡትና አንዱን በአንዱ ላይ እንዲነሳ ያደርጉታል። በዚህ መሃል እየጠፋሁ ነው ብሎ ሮሮ የሚያሰማውን ‹ከእኛ ዘንድ ስላልተጠጋህ ነው፤ ወደእኛ ቅረብ ይሉትና አባል ያደርጉታል። ይሁንና በዚህ መልኩ መቀጠል አልቻሉም። የሚመሩበት ርዕዮተ ዓለም በራሱ ምን እንደሆነ አይታወቅም።

እነርሱ ጥቅም ያግኙ እንጂ ምንም ነገር የማድረጉ ስልጣን ስለነበራቸው አንድ ያልተማረን አካል ምሑር ነው በሚል አንድ ትልቅ መስሪያ ቤት ውስጥ ኃላፊ አድርገው ይሾሙታል፤ እግረ መንገዱን ሰላይ እንዲሆንላቸው ያደርጉታል። ያልተማረን አካል በዩኒቨርሲቲ ውስጥ እንዲያስተምር ያደርጉታል። የእነርሱ ወዳጅ ያልሆነውን የበታችነት ስሜት እንዲሰማው ያደርጉታል፤ ሰውዬው ራሱ የማያውቀውን እስከ ሰባት ቤት ቆጥረው ዘሩን ይነግሩታል፤ አሊያም በኃይማኖቱ ይመጡበታል። ቡድኑ ግን የኋላ ታሪኩ ሲጠና ከጣሊያን ጊዜ ጀምሮ ባንዳ የነበረ ነው።

ትህነግ ከጣሊያን ጋር ወግኖ ኢትዮጵያን የወጉ በመሆናቸው በትግራይ እንደባንዳ የሚታዩ ዝርያዎች ናቸው። እነርሱም ይህን ታሪካቸውን ለመቀየር ነው ወደ ስልጣን የመጡት። ይህን የእነርሱን የባንዳነት ስም የባንዳነት ታሪክ ለሌላው አካል ይሰጡታል። ለምሳሌ እንደርታ፣ ራያም ሆነ ተንቤን ብትሔጂ የባንዳነት ስያሜ የሌለው ሕዝብ ነው። ነገር ግን እነርሱ በባንዳነታቸው ስለሚሸማቀቁ የእነርሱን ታሪክ ወደሌላው በመለጠፍ ለማሸማቀቅ ይጥራሉ።

**አዲስ ዘመን፡- በሕዝብ ለውጥ ፈላጊነት ከስልጣኑ የተባረረው አሸባሪው ትህነግ ወደትግራይ ክልል ከገባ በኋላ ሲያሳይ የነበረውን ባህሪ እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** ከፌዴራል ስልጣኑ ተባርሮ ወደትግራይ ሕዝብ ሲመጣ ለትግራይ ሕዝብ ያሳየው ቀድሞ የነበረውን ቀጣፊነቱን ነው። ቡድኑ የታገለለትን የትግራይ ሕዝብ ላይ ክህደት ፈጽሟል። ንቀትም አሳይቶታል። ቀደም ሲልም ቢሆን መሬቱን እየቀሙ ገበሬው እንዳያርስ አድርገውትም ስለነበር ወደክልሉ ሲመጣ ገበሬው ‹ለምን መጣችሁ፤ እኛም ለውጥ እንፈልጋለን፤ አዲስ ፊትም ማየት እንሻለን፤ የተማሩ ልጆቻችንም ቦታ እንዲያገኙ እንፈልጋለን› ብሎታል። ይሁንና የአሸባሪው ምላሽ የነበረው ‹‹እኛ ለብዙ ዓመታት የትግራይን ሕዝብ ትተን ኢትዮጵያን ስንል ነበር የቆየነው፤ አሁን ግን ኢትዮጵያ አታስፈልግምና የትግራይን ሕዝብ ለመካስ ነው የመጣነው፤ ይቅርታ አድርጉልን፤ እኛ ተበላሽተናል፤ አሁን ግን ሁሉን እናስተካክላለን፤ የትግራይ ሕዝብን ጥያቄ መመለስ እንፈልጋለን› በማለት የለመዱትን ፕሮፓጋንዳ ማስተጋባት ነው የጀመሩት። ሕዝቡ በፕሮፓጋንዳ እንዲሰክር አደረጉት። ጭራሽ ለሕዝቡ የተበጀተውን ለጦርነት ማድረግ ጀመሩ። በአጠቃላይ ትግራይን እንደእስራኤል እናደርጋታለን ብለው ፎክረው ጦርነቱ ሲነሳ ግን ትግራይ እንደሶሪያ ነው የሆነችው። ሕዝቡም መማረር ጀመረ።

ቡድኑ ወደክልል ከመጣ በኋላ በ2012 ዓ.ም ክልሉ ከፌዴራል ጋር ያለውን መዋቅር በጥሶታል። በሌላ በኩል ደግሞ እነርሱን የማይደግፋቸውን አንሳፈፉት። የእነርሱን ካድሬዎች ደግሞ አስተባባሪም በሲቪል ሰርቪስ ውስጥም ገብቶ እንዲሠራ አደረጉት። ተንሳፋፊው ወደሥራ የሚመለስበትን ጊዜ እንዲናፍቅ እንጂ ሌላ ጥያቄ እንዳያነሳ አደረጉት።

ከዚህ ውጪ ሦስት ዙር ዘመቻ ብሎ ያወጀ ሲሆን፣ የመጀመሪያው የሕልውና ዘመቻ፣ ሁለተኛው ደግሞ አንበጣንና ኮሮናን የሚመለከት ዘመቻ፣ ሦስተኛው ደግሞ የሰሜን እዝን ለመውጋት የተደረገ ዘመቻ ነው። ይህ ያወጁት ዘመቻ የትግራይ ሕዝብ በአማራም በአፋርም ሆነ በፌዴራል መንግሥት እንደተከበበ አድርገው ፕሮፓጋንዳ በመሥራታቸው ነው። አንበጣን ራሱ የፌዴራል መንግሥት እንዳስገባ አስመስለው ነው ሲያወሩ የነበሩት። ለኮሮና መከላከያ ማስክ መንግሥት አልሰጠኸም እያሉ ሕዝቡን ለሌላ ዘመቻ እንዲዘጋጅ አደረጉት። ከመንግሥት ደግሞ ምንም እንዳይጠብቅና ሕዝቡ ለጦርነት ራሱን እንዲያዘጋጅ አነሳሱት። ሕዝቡ ቀልቡን እንዳይሰበስብ ተከበሃል እያሉ ያዋከቡት ነበር፤ ጥያቄ እንዳያነሳ አድርገውት ራሱን ለማዳን ብቻ ሲወተውቱት ነበር፤ አሸባሪው ቡድን በአንድ ዓመት ውስጥ 102 መግለጫዎችን አውጥቷል። በወቅቱ አቶ ስዩም መስፍን ራሱ ‹ጦርነቱ አዲስ አበባ ተጀምሮ አዲስ አበባ ያልቃል› ሲል ነበር። ወይዘሮ ፈትለወርቅ ደግሞ ‹እነርሱ ሲወርዱ እኛ እንወጣለን› ስትል ፎክራም ነበር። የትግራይ ሕዝብ አክቲቪስት ነኝ ባዩ አሉላ ሰለሞን ደግሞ ‹ጦርነት ባህለዊ ጨዋታችን ነው› ሲልም ተደምጧል። ሲፈልጉ

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

ደግሞ 300 ሚሊዮን አበል ከፍለው ፌዴራሊስት ኃይሎችን ሰብስበውም ነበር፡ ለትግራይ ሕዝብ ግን የ3 ሚሊዮን ብር መሠረተ ልማት ሠርተውለት አያውቁም።

ኢትዮጵያ የምትባል በትውልዱ አዕምሮ እንዲኖር ስለማይፈልጉ በክልሉ በሚገኙ በትምህርት ቤት እንኳ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር እንዳይዘመር አድርገዋል። እነርሱ በፈጠሯቸው ባይቶና በሚባል ፓርቲ አማካይነት የመገንጠል ጥያቄም ይጠይቃሉ። ቀጥታ ከውጭ ጋር ለምን ግንኙነት አናደርግም ሲሉ ሕዝቡን ያነሳሱት ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- የአገር መከላከያ ሰራዊት በዚህ በአሸባሪው ቡድን ጥቅምት 24 ጀርባው ከመወጋቱ በተጨማሪ በየአጋጣሚው ሁሉ ስሙን ለማጠልሸት ሲታትር ነበርና ሰላሙን ያስጠበቀው፣ ሥራውን ዝቅ ብሎ የሠራለት የአገር መከላከያ ሰራዊት ወሮታው ይህ ነበር ይላሉ?**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** እንደሚታወቀው መንግሥት ወደስልጣን የሚመጣበት መንገድ ወይ በኃይል ነው፤ አሊያም በሐሳብ ልዕልና ነው። እንደ እድል ሆኖ ትህነግ በባህሪው ሐሳብ የለውም፤ በሐሳብም አያምንም። ችግሮችን ለመፍታት የሚጠቀመው በኃይልና በኃይል ብቻ ነው። ሐሳቡን ለመግለጽ እንኳ ሲፈልግ ሕዝብን በግድ አስወጥቶ ሐሳቡን በኃይል ያስርጻል።

የመከላከያ ስም የሚያጠለሽበት የራሱ ምክንያት አለው፤ አንደኛ ከስልጣን መውረዱ ያልጠበቀው ጉዳይ ስለነበር አብሽቆታል። በ2010 ዓ.ም በኢትዮጵያ ውስጥ የመጣው የሕዝብ ማዕበል በመሳሪያ ኃይል ወደስልጣን የመጣውን ቡድን አንድም ጥይት ሳይተኩስበት በሰልፍ ብቻ ነው ከስልጣን ያባረረው። ‹ተራራ ያንቀጠቀጥኩ ትውልድ ነኝ› እያለ ለዓለም ማህበረሰብ ሲናገር የነበረው ቡድን በሰልፍ ብቻ ከስልጣኑ መወገዱ ለእርሱ ትልቅ ሽንፈት ነበር።

በስልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ ያካበተው ሀብት፣ ከልማት ባንክ እንደልብ በብድር መልክ ሲወስደው የነበረው ገንዘብ ሁሉ መቅረቱ ሲያመው ስለነበር፤ ያንን ለመበቀል የአገሪቱ ቆንጮ ነው የተባለለትን የሰሜን እዝን ጀርባውን ለመውጋት እንዲወስን ስላደረገው ወጋው።

መከላከያን እንዲመቱ የተደረገበት ምክንያት እነዶክተር ዐቢይ ወደስልጣን ሲመጡ ሦስት አራት ጊዜ መፈንቀለ መንግሥት ለማድረግ ፈልገው ነበር። ነገር ግን አልተሳካላቸውም። ስለዚህ የአገሪቱ 85 በመቶ የሚሆን ሰራዊት በሰሜኑ ክፍል ስላለ እንደ ድሮው ከኤርትራ ጋር በመሆን ተዋግተው ወደስልጣን ለመምጣት ፈልገው ከኤርትራ ጋር ለመስማማት ቢሹም ኤርትራ ግን እሺ አላለችም። ከአሸባሪው ቡድን በአብዛኛው በአባቱ ወይም በእናቱ ኤርትራዊ አሊያም የአማራ ዝርያ ያለበት ነው። ወይም ደግሞ የወለጋ ሰዎች ናቸው። ግን እነዚህ ሰዎች ኦሮሞ፣ አማራ እና ኤርትራ ጠል ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ልክ ከአማራ፣ ኦሮሞና ኤርትራ በላይ እነርሱ ለእነርሱ አሳቢ እንደሆኑ ያስመስላሉ።

ይህ ቡድን ሰሜን እዝን ከመምታቱ በፊት ፕሮፓጋንዳ ሰራ። አስቀድሞ የኤርትራው ፕሬዚዳንት ሊመታን ነው በሚል መለፈፍ ጀመረ። በተለይ ለሃያ ዓመታት ተራርቀው የነበሩትን ኢትዮጵያንና ኤርትራን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢያ እርቅ እንዲኖር በማድረጋቸው በጣም ተናደውም ነበር። በመሆኑም ይህ ሁሉ ስላበሳጫቸው የመከላከያን ስም ማጠልሸትን ተያያዙ። ቀጥሎውም የኤርትራ ኃይል ሊወረን ነው እያሉ ማስወራት ጀምሩና ድንበር አካባቢ የትግራይ ልዩ ኃይል እንዲተኩስ እያደረጉ ‹ይኸውም ኤርትራ ሊወርህ መጣ› እያሉ ሕዝቡን ማሸበር ተያያዙ።

አድብተውም ሕዝብን ሲጠብቅ ሲያግዘ የነበረውን መከላከያ ሰራዊትን ወድቅትን ተገን አድርገው ጀርባውን ከመውጋታቸው አስቀድመው ጀግና፣ ኅበዝ፣ እያሉ ሲሸለሙና ሲጋብዙትም ነበር። ሟቹ ሴኮ ቱሬ ‹መብረቃዊ ጥቃት ፈጽመናል› እንዳለውም በወቅቱ በሰላም ጠባቂው ላይ ክህደት ፈጽመውበታል። ይህንን ግፍ ሲፈጽሙ አስበው የነበረው ከ85 በመቶ በላይ የአገር መከላከያ ሰራዊትን እንዳጠቁ እና አስፈላጊው መሳሪያ ሁሉ በእጃቸው እንዳለ ነበር። ከዚህ የተነሳ ከፌዴራል መንግሥት የሚሰጥ የመልስ ምት እንደሌለና ቢኖርም ፈጣን እንዳልሆነ ነበር ያሰቡት። ቀሪው ሰራዊት የኢትዮጵያን ቀሪውን ክፍል የሕዳሴ ግድቡን ጨምሮ የሚጠበቅ ስለሆነ ኃይል አደራጅቶ እስከሚመጣ ድረስ እናሸንፋለን ብለው ተስፋ አድርገው ነበር። ልክ ቡድኑ መከላከያ ላይ መብረቃዊ ጥቃት ወስድኩ ባለው ቅጽበት የፌዴራል መንግሥትም መብረቃዊ ሆኖ ተከሰተባቸው። በዚህ ጊዜ 17 ዓመት ሙሉ የታገልን ታላላቅ ጀኔራሎች ነን፤ በዓለም ሁሉ እንታወቃለን ብለው የነበሩ ሁሉ ሮጠው የገቡት ተንቤን ነው። እዚያው በረሃ ሆነው እንኳ ፕሮፓጋንዳ ሲሠሩ ነበር።

ትህነግ ሽንፈት ያጋጠመው መከላከያ ሰራዊቱን



ከጀርባው በወጋበት ቀን ነው፣ እስከ ዛሬ ድረስም የሚውተረተረው በተሸነፈ ስነ ልቦናው ነው። ሰሜን እዝን በመካዱና የማይነካውን ኃይል በመንካቱ ከዚያን ቀን በኋላ መነሳት አልቻለም። ሰሜን እዝን በድፍረት በመምታቱም ኢትዮጵያውያኑን እንዲነሳሱ አድርጓቸዋል፤ ምክንያቱም ኢትዮጵያዊ የሆነው ሁሉ የተመታበት ልጁ፤ አገር ጠባቂው፤ ድንበር አስከባሪው ኃይል ነውና የኢትዮጵያ ሕዝብ ዳር እስከ ዳር ሆ! ብሎ ለመነሳት አፍታም አልፈጀበትም። ምንም እንኳን በመከላከያ ላይ የደረሰው ጥቃት ፍጹም አሳዛኝ ቢሆንም ኢትዮጵያውያኑን ግን አንድ አድርጎታል።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት የሰላም ንግግሩ በአፍሪካ ህብረት ተጀምሯል፤ በአንድ አገር ውስጥም ሁለት ሰራዊት መኖር ስለማይቻል ወደሕግ መምጣት የተገባቸው በርካታ ጉዳዮች አሉና ንግግሩ መቋጫው ምን ይሆናል ብለው ያስባሉ?**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** በአንድ አገር ውስጥ በየትኛውም አገር ቢሆን የሚኖረው አንድ ሰራዊት ነው። ይሁንና ምዕራባውያኑ ለአሸባሪው ሰራዊት ድጋፍ የማድረጋቸው ምስጢር ፍላጎታቸውን በተልዕኮ እንዲፈጽምላቸው ከማሰብ የመነጨ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ቡድኑ ወደስልጣን የሚመለስ ከሆነ የገባለት ቃልም ስላለ ነው።

በአንድ አገር ሁለት ሰራዊት እንዲኖር መፍቀድ ማለት አገሪቱን ለሁለት እንዲከፍላት እድል መስጠት ማለት ነውና ይህን እድል ማምከን ተገቢ ነው። ምክንያቱም ሁለት ኃይል አለ ማለት እንደ ሰሜን ኮሪያና ደቡብ ኮሪያ አሊያም፣ እንደ ሱዳንና ደቡብ ሱዳን ወይም ደግሞ እንደሌሎቹ ለሁለት ወደመከፈል ያመጣል።

በአሸባሪው ክፉ ባህሪ በትግራይ ውስጥ ሦስት ትውልድ አልቋል ማለት ይቻላል። በጣም የሚያሳዝነው የትህነግ ባለስልጣናት የሆኑ ጥቂት ሰዎች እንዲኖሩ ትውልድ ማለቁ ነው። 17 ዓመት ከደርግ ጋር በተዋጋበት ጊዜ በ10 ሺ የሚገመት፣ ከኤርትራ ጋር በተደረገውም ውጊያ ወደ 70 ሺ ያህል ሰው አልቆ ወደ 60 ሺ ያህሉ ቆስሏል። በመጨረሻ ደግሞ በዚህ ሁለት ዓመት ውስጥ በእነርሱ ቆስቋሽነት በተካሄደው ጦርነት የእነርሱ የሆኑትን ሳይነካ በርካታ የትግራይ ሕዝብ እንዳለቀ ይነገራል። የትግራይ ሕዝብ ግን ይህን ሁሉ መከራ ሲከፍል እነርሱ ከነወዛቸው እንዳማረባቸው በሕይወት አሉ። የትግራይ ሕዝብ ግን ተዋርዶና ፍትህ አጥቶ ይሞታል። ይህ ቡድን የትግራይን ሕዝብ እንደ ምሽግ ነው እየተጠቀመበት።

ትህነግ አሁንም ቢሆን የሚደራደረው የትግራይን ሕዝብ ለመጠበቅ ሳይሆን የራሱን እስትንፋስ ለማስቀጠል ነው የሚል እምነት አለኝ። የትግራይ ሕዝብ ሰላም እንዲያገኝ አይፈልግም። ለትግራይ ሕዝብ ከማዘን ይልቅ ለዘረፋት ንብረት ቅድሚያ ሰጥተው የሚያዝኑ ናቸው። ቡድኑ ለትግራይ ሕዝብ በፊትም አልጠቀመም፤ አሁንም አይጠቅምም።

**አዲስ ዘመን፡- ወደአዲስ አበባ የመጡት እንዴት ነበር?**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** ወደአዲስ አበባ የመጣነው ድንገት ነው። እኔ በወቅቱ ለሕዝቡ እህል እያደልኩ ነበር። በወቅቱ መከላከያ እየወጣ ስለነበር እኔንም በ15 ደቂቃ ውስጥ እንድትወጣ አለኝ። ይህ ማለት በትግራይ ክልል ውስጥ መከላከያ መስዋዕትነት ከፍሎ ያመጣውን ድል እና ለውጥ በፖለቲካው ላይ ስላልተደገመ የመጣ ችግር ነው ባይ ነኝ። እሱ ችግር ደግሞ መከላከያ ከትግራይ መልሶ እንዲወጣ አድርጎታል። ይህም ማለት ደግሞ በጊዜያዊ አስተዳደሩ ውስጥ ምንም ዓይነት የፖለቲካ ሥራ እንዲሠራ አልተደረገም ነው።

በተቃራኒው ወደበረሃው ወርዶ የነበረው ጁንታ የፕሮፓጋንዳ ሥራ በደንብ ስለሠራ ሕዝቡ ወደበረሃ እንዲወጣና ትጥቅና ስንቅ ራሱ ሕዝቡ እንዲሆነው ከማድረጉም በላይ ሕዝቡ እንዳይረጋጋ የማድረግ ሥራ ሠርቷል። መከላከያንም መንግሥትንም እንዳያምን የፕሮፓጋንዳ ሥራ ጁንታው መሥራት ችሏል። እንዲያውም መንግሥት ሕዝቡን የማጥፋት እቅድ እንዳለው ሁሉ ነበር ሲነገረው የነበረው። ሕዝቡን ያደናበሩት ከውጭም ከውስጥም ነው። ይህ ሁሉ ፖለቲካው ላይ ባለመሠራቱ ነው።

በጨረቃ ምርጫ ወቅት ተሳታፊ የነበሩት እና በሕወሓት ጊዜ ጡረታ የወጡ ታጋዮች ወደከፍተኛ አመራር ሲያመጡ ነበር። ነገር ግን በዘመናቸው ሁሉ ስለኢትዮጵያ ይታገሉ የነበሩ ሁሉ እንዲገለሉ በማድረግ በኩል ከፍ ያለ ሥራ ሠርተዋል። ቢገቡም እንኳ በሁለት መስመር ጽሑፍ እንዲባረሩ ያደርጉ ነበር። ከዚህ የቀረው ደግሞ እንዲታፈንና ብሎም እንዲገደል የማመቻቸት ሥራ ተሠርቷል። በጥቅሉ በጊዜያዊ አስተዳደር ውስጥ የነበረ ከ90 በመቶ በላይ የሆኑ አካላት ታፍኗል፤ አካሉም ጎድሏል። በዚህ ውስጥ ለአገር ሲሉ የሞቱ እንኳን መንግሥት ራሱ አስታውሷቸው አያውቅም። ደመ ከልብ ሆነው ነው የቀሩት።

ሌላው ለትህነግ ስንቅና ትጥቅ የሚልክ አንዱን እግሩን አንዱ ላይ ሌላውን ደግሞ ሌላው ላይ ያደረገ ግን ሲጎዳ አይታይም ነበር። ይልቁንም ደመወዝ ይከፈላቸው የነበሩ ሁሉ ነበሩ። በጥቅሉ በጊዜያዊ አስተዳደር ውስጥ የጠራ ነገር አልነበረም። የታገለ ሌላ ስልጣን የያዘ ሌላ ነበር። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ለትህነግ ፕሮፓጋንዳ በጣም ምቹ ሁኔታ ነበር የፈጠረለት። ጭራሽ የትግራይ ቲቪና ትግራይ ሚዲያ ሃውስ ተናበው መሥራት ሁሉ የጀመሩበት ጊዜ ነበር።

ለውጥ የሚፈልግና የኢትዮጵያዊነት ስሜት ያለው በጣም የታገለና ዋጋ የከፈለ ከመስመር እንዲወጣ ተደርጎ አንገቱን እንዲደፋና እንዲያቀረቅር ተፈርዶበታል። ከእሱ በተጻጻራሪ ያለው በወንጀል ሊጠየቅ የሚገባው ጭራሽ በስልጣኑ እንዲቀጥል የተደረገበት ሁኔታ አለ። ዋጋ የከፈሉ ሰዎች ግን በሁለት መስመር ጽሑፍ እንዲባረሩ ተደርገዋል። ሌላው ቀርቶ መከላከያ ዋጋ ከፍሎ የማረካቸው ሰዎች በበላይ ባለስልጣናት አማካይነት በሁለት መስመር ጽሑፍ እንዲወጡ ተደርገዋል። እነዚህ አካላት ሕዝቡን በእጅጉ ሲበድሉ የነበሩ አካላት ናቸው።

ወደጊዜያዊ አስተዳደር የገቡ ሰዎች ሲገቡ የካሳ ዘመን መጣልን በሚል ስሜትም ሊሆን ይችላል። ሁለተኛው ደግሞ ይህን እድል በማግኘታቸው በእድሉ ሕዝቡን ሳይሆን ራሳቸውን ለመጥቀም በማሰብ ሊሆን ይችላል። የትህነግን ሀብት ለመጠበቅም ሲባል የገቡ ነበሩ። ሌላው ቀርቶ በረሃ ያለውና በጊዜያዊ አስተዳደር ውስጥ ያለው ኃይል ተናቦ እስከመስራት የደረሱ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- በጊዜያዊ አስተዳደር ውስጥ የነበራችሁና የለውጡ ደጋፊዎች የሆናችሁ መንግሥትን በምን መልኩ ማገዝ ትፈልጋላችሁ?**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** የትግራይ ሕዝብ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደመሆኑ ለውጥ ያስፈልገዋል፤ አዲስ ፊትም ያስፈልገዋል። ስለዚህ ለዚህ ለውጥ የሚታገልና ዋጋ የሚከፍል አለ፤ ይህን የሚያደርገው ደግሞ ለአገሩ ሲል ነው፤ እኛም ከ300 በላይ የምንሆን የለውጡ ደጋፊዎች ከትግራይ ወደአዲስ አበባ ስንመጣ ከመከላከያ ኃይል ጋር በመሆን ነው።

ከጊዜያዊ አስተዳደር ውስጥ ወደአዲስ አበባ የመጣነው አስር በመቶ እንኳ አንሆንም። 90 በመቶው እዛ እንዲቀር የተደረገው ሆን ተብሎ ነው። አንዳንዶቹም የለውጡ ደጋፊዎች ናችሁ በሚል ታስረዋል፤ እስከ 17 ዓመት ድረስ የተፈረደባቸውም አሉ። እጅ እንዲሰጡም ተደርገዋል። ይህ ብቻ አይደለም በርካታ ቁጥር ያላቸውም ሞተዋል። መንግሥት እነዚህን ቡድን ሊጠይቅ ይገባል።

እዚህ ከመጣን በኋላ ግን ከጊዜያዊ አስተዳደር ውስጥ በአሁኑ ሰዓት ከፍተኛ የመንግሥት አመራር ከሆኑት መካከል አንዱ ‹ለምን መጣችሁ?› ሲልም ጠይቆናል፤ ይህን ያለበትም ምክንያት እዛ ሆነን አሸባሪው ቡድን የሚያዘንን እንድንፈጽምም በመፈለግ ነው።

በዚህ በአዲስ አበባ ውስጥ እንኳ ተደራጅተው መንግሥትን የሚደግፉ ትግራዋይ ብዙ ናቸው፤ ግን ማንም ዞር ብሎ አያያቸውም፤ እኛ እንኳ ትናንት የመንግሥት ሠራተኛ ሆነን እስከ ዛሬ ደመወዝ ተከፍሎን አያውቅም፤ በየቤተ ክርስቲያኑ ተጠልለን አለን፤ በአሸባሪው የተመታ አካል እንኳ ቁስሉን የሚያሳክመው እየለመነ ነው። መንግሥት እነዚህን ክፍተቶች መፈተሽ አለበት ባይ ነኝ።

ይህ ካልሆነ አሸባሪው ለአራተኛ ጊዜ ሊያንሰራራ ይችላል፤ ስለዚህም ከመንግሥትም ከአሸባሪውም ጋር በመሆን ሁለት አማራጭ ይዘው የሚንቀሳቀሱትን ሊጠይቃቸው ይገባል። እዚህ ያለ ትግራዋይን ሊያደራጅ ይገባል፤ ለሰልፍ ብቻ መጠራት የለበትም። የትግራይ ሕዝብ ተወካይ በፌዴራል ደረጃ ሊኖረው ይገባል። የሚታገለው ሌላ ለስልጣን የሚፈለገው ሌላ መሆን የለበትም።

ስለዚህ መንግሥት የሚታገሉለትን ሰዎች መለየት አለበት፤ ምክንያቱም እኛን የለውጥ ኃይሎችን አለመደገፍ ሌቦች እንድንሆን ነው ወይ የሚል ጥያቄ እንዲፈጠር ያደርጋል፤ ትግራይ ያለው አካል ደግሞ ምንም እንኳ የለውጡ ደጋፊ መሆን ቢፈልግም እኛ ተጥለን እነርሱ ለለውጥ መዘጋጀት አይችሉም፤ መጀመሪያ እኛ ላይ ለመስራት በአፋጣኝ ችግሩን መፍታት አለበት። ለትግራይ ሕዝብም መንግሥት ያለውን ሁኔታ በአስቸኳይ ሊያሳውቀው ይገባል። መሠረተ ልማቱም ገበያውም የመንግሥት ሥራውም እንዲቀጥል በቶሎ ሊያሳውቀው ይገባል። ዞኖችንም ከፌዴራል መንግሥት ጋር በቶሎ ማያያዝ በተለይ እንድርታ፣ ራያና ክህልተአውላዕሎን ማያያዝ የግድ ይላል፤ ምክንያቱም በአሸባሪው ቡድን የተጨቆነ ነውና፤ የሚሞተው ሌላ ስልጣን የሚያገኘው ሌላ እንዳይሆን መጣር አለበት። መንግሥት እንደ ዶክተር አረጋዊ በርሄ ዓይነት የትህነግ መስራቾች ጋር አብሮ መስራት አለበት፤ በጥቅሉ መንግሥት እኛን ባይተዋር ባያደርገን መልካም ነው። መንግሥት ሕዝቡ እንዲረጋጋ ፕሮፓጋንዳ መሥራት አለበት። ስንዴውን ከእንክርዳዱም መለየት ይጠበቅበታል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ቴዎድሮስ፡-** እኔም ዕድሉን ስለሰጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የደብረ ብርሃንን የኢንቨስትመንት አቅም ዓለም አቀፋዊ የማድረግ ጥረት

አንተነህ ቸሬ

በኢትዮጵያ የባለሀብቶችን ትኩረት ከሳቡ ዋነኛ የኢንቨስትመንት መዳረሻዎች መካከል አንዷ መሆን የቻለችው ደብረ ብርሃን ከተማ፣ የኢንቨስትመንት ስኬቷ ለሌሎች አካባቢዎችም አርዓያ መሆን እየቻለ መጥቷል። ከተማዋ ከአዲስ አበባ ከተማ በቅርብ ርቀት ላይ መገኘቷ፣ አስተማማኝ ሰላም የሰፈነባት መሆኗ፣ የአካባቢዋ ምቹ የአየር ንብረት እንዲሁም ለግብርና፣ ለኢንዱስትሪና ለአገልግሎት ዘርፎች ልማት የሚሆን እምቅ አቅም ያላት መሆኑ ደብረ ብርሃን ተመራጭ የኢንቨስትመንት መዳረሻ እንድትሆን ካስቻሏት ምክንያቶች መካከል ይጠቀሳሉ።

ለቀጣይ 50 ዓመታት የሚያገለግል መዋቅራዊ የከተማ ፕላን እየተዘጋጀላት መሆኑንም መረጃዎች ያመለክታሉ። በቀጣይ ዓመታትም የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዋ እየጨመረ እንደሚሄድ ይጠበቃል።

በከተማዋ በ2014 በጀት አመት ለ300 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ፣ 39 ቢሊዮን ብር ላስመዘገቡ ለ310 ፕሮጀክቶች ፈቃድ ተሰጥቷል። እነዚህ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ወደ ስራ ሲገቡ ከ35ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል መፍጠር የሚችሉ ናቸው። በ2015 በጀት አመት ደግሞ ለ350 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ፈቃድ ለመስጠት የታቀደ ሲሆን፣ ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ ከ100 ለሚበልጡ ባለሀብቶች ፈቃድ መስጠት ተችሏል።

ደብረ ብርሃን ከዚህ የተሻገረ እቅድም አላት። አሁን ያለውን የኢንቨስትመንት አቅሟን በማሳደግ ተመራጭ የኢንቨስትመንት መዳረሻ እምብርት (Investment Hub) ለመሆን አልማ እየተጋች ነው። ይህን እቅዷን ለማሳካትም በአካባቢው እየተበራከተ የመጣውን የኢንቨስትመንት ፍሰት ማገዝና ማበረታታት፣ አዳዲስ የኢንቨስትመንት አቅሞችን በማስተዋወቅና ምቹ አሰራሮችን በመዘርጋት ተጨማሪ ባለሀብቶችን መሳብ፣ አዳዲስ ስራ ፈጣሪ ወጣቶችን ማገዝ እንዲሁም ከዓለም አቀፍ የንግድ፣ የፋይናንስና የኢንቨስትመንት ተቋማት ጋር ትስስር መፍጠር አስፈላጊ ግብዓቶች መሆናቸውን በመገንዘብ እነዚህን ግብዓቶች ለማሟላት እገዛ የሚያደርጉ ተግባራትን እያከናወነች ነው።

በዚህ መሰረት ከእነዚህ የኢንቨስትመንት አቅም ማሳደጊያ ግብዓቶች መካከል አንዱ ይሆናል የተባለው «የደብረ ብርሃን ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት፣ የንግድና የፋይናንስ ኤክስፖ» ከጥር አራት እስከ 14 ቀን 2015 ዓ.ም በደብረ ብርሃን ከተማ ይካሄዳል። ኤክስፖው ከዚህ ቀደም መሰል የኢንቨስትመንት፣ የንግድና የፋይናንስ ኤክስፖ ላልተካሄደባት ለደብረ ብርሃን ከተማ አዲስና በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነ ትልቅ ኹነት ነው። ይህም ኢንቨስትመንት ለሰመረላት ደብረ ብርሃን ተጨማሪ አቅም እንደሚፈጥርላት ይታመናል።

«የደብረ ብርሃን ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት፣ የንግድና የፋይናንስ ኤክስፖ» በኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በተከሰተው ጦርነት ምክንያት ተቀዛቅዞ የቆየው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት እንዲጨምር በማድረግ፣ የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በማስተሳሰርና ሰፊ የስራ እድል በመፍጠር ሀገራዊ ምጣኔ ሀብቱ እንዲነቃቃ ለማድረግ አጋዥ ግብዓት ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

መቀዛቀዝና ውድመት የገጠመውን ምጣኔ ሀብት ማነቃቃት፤ ትርፍ አምራቾችና ለማንኛውም የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ምቹ ለሆኑት የሰሜን ሸዋ ዞን እና አጎራባች አካባቢዎች ከዓለም አቀፉ የኢንቨስትመንት ማኅበረሰብ ጋር የተሳሳረ የምጣኔ ሀብት ስርዓት መዘርጋት፤ የንግድ፣ የኢንቨስትመንትና የፋይናንስ ተቋማት የጋራ የትስስር መድረክ መፍጠር፤ የኢንቨስትመንት ቅስቀሳ በማካሄድ የደብረ ብርሃን ሪጂዮፖሊታን ከተማን የኢንቨስትመንት እምብርትነት በዓለም አቀፍ ደረጃ ማስተዋወቅ እንዲሁም የተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ያሏቸውን የኢንቨስትመንት አቅሞች እንዲያስተዋውቁ እድል መፍጠር ማስፈለጉ ኤክስፖውን ለማዘጋጀት መነሻ የሆኑ ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው።




በኤክስፖው ላይ ከ800 እስከ አንድ ሺ ተሳታፊዎች እንደሚገኙ ይጠበቃል፤ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች፣ አከፋፋዮችና በችርቻሮ ንግድ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎች፣ የምርምርና ፈጠራ ተቋማት፣ የፋይናንስ ድርጅቶች (ባንኮች፣ የብድርና ቁጠባ እንዲሁም የኢንሹራንስ ተቋማት)፣ የወጣት ስራ ፈጣሪ ማኅበራት እና ክልሎች፣ ዞኖች፣ ከተማ አስተዳደሮችና ወረዳዎች በኹነቱ ላይ ይሳተፋሉ። በተሳትፏቸውም አቅሞቻቸውን ያስተዋውቃሉ፤ የልምድ ልውውጥ ያደርጋሉ። ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናትና አምባሳደሮችም እንደሚገኙ ይጠበቃል።

ኤክስፖው የኢንቨስትመንት አቅምን ከማስተዋወቂያነቱና ከልምድ ልውውጥ መድረክነቱ ባሻገር በደብረ ብርሃን የኢንቨስትመንት እድገት ተስፋ፣ ተግዳሮቶችና መፍትሄዎች ላይ ያተኮሩ ውይይቶችም ይካሄዱበታል።

«ተጉለት ሚዲያና ፕሮሞሽን»፣ «ዡማ ፕሮሞሽንና ኹነቶች» እና «ናብሊስ ኢንተርናሽናል ሚዲያ፣ ማርኬቲንግና ኤቨንትስ» ከደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር፣ ከአማራ ክልልና ከፌደራል መንግሥት ጋር በትብብር ለሚያዘጋጁት ለዚህ ኹነት፣ ከጥቅምት 15 እስከ ታኅሳሥ 25 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ የሚቆይ ምዝገባ የሚከናወን ሲሆን፣ አዲስ አበባን ጨምሮ በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ ከ10 በላይ ከተሞች ምዝገባው በይፋ እንደተጀመረ ተጠቁሟል።

### የኤክስፖው ዓላማዎችና ፋይዳዎች

የደብረ ብርሃን ከተማ ተቀዳሚ ምክትል ከንቲባ አቶ ካሣሁን እምቢአለ፤ ኤክስፖው ደብረ ብርሃንን ብቻ ታሳቢ ያደረገ እንዳልሆነና የደብረ ብርሃን መልማት ከአማራ ክልል አልፎ ለኢትዮጵያ አጠቃላይ ሀገራዊ እድገት አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ከግምት ውስጥ ያስገባ ኹነት እንደሆነ ያስረዳሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፤ የኢንቨስትመንት፣ የንግድና የፋይናንስ ኤክስፖው የአማራ ክልል በኢንቨስትመንት ልማትና ፕሮሞሽን ተግባራት ረገድ ቀዳሚ ትኩረት በሚፈልጉ ዘርፎች ላይ አተኩሮ የመስራት አቅጣጫዎችን፣ የኢንቨስትመንትን ዓለም አቀፋዊነትና እና ተወዳዳሪነትን እንዲሁም የተቀዛቀዘውን የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ማነቃቃትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወን ተግባር ነው።

እንደ አቶ ካሳሁን ማብራሪያ፣ በደብረ ብርሃንና አካባቢው እየተበራከተ የመጣውን የኢንቨስትመንት ፍሰት በዓለም አቀፍ ደረጃ ማስተዋወቅ፣ ማገዝና ማበረታታት፤ አዋጭ በሆኑ ዘርፎች የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን መሳብ፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ አዳዲስ ስራ ፈጣሪ ወጣቶች (Youth Entrepreneurs and Start-Ups) ከትልልቅ ኩባንያዎች ጋር ትስስር እንዲኖራቸው እድል መፍጠር፤ የዓለም አቀፍ ንግድ፣ የኢንቨስትመንትና የፋይናንስ ተቋማትን የትብብር ማዕቀፍና ትስስር ማጠናከር፤ የደብረ ብርሃንን የኢንቨስትመንት መዳረሻ እምብርትነት ማሳደግ፤ ወረዳዎች፣ ከተሞችና ዞኖች የኢንቨስትመንት አቅሞቻቸውን ለኢንቨስተሮች ማስተዋወቅ እንዲችሉ መድረክ መፍጠር የኤክስፖው ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው። በኢንቨስትመንትና ፋይናንስ ተቋማት ላይ ያተኮረ ኤክስፖ ተዘጋጅቶ የማያውቅ መሆኑንም ጠቅሰው፣ መድረኩ በዘርፉ አዲስ ልምድ እንዲገኝ መልካም አጋጣሚ መሆኑን ተናግረዋል።

«የአማራ ክልል ዋና ዋና የኢንቨስትመንት የትኩረት ዘርፎችንና አካባቢዎችን በመለየት ዘርፉን ለማሳደግ እንዲሁም ክልሉ በጦርነቱ ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት ለማካካስና የኢንቨስትመንት ተግባራትን ለማነቃቃት እየሰራ ነው» የሚሉት አቶ ካሣሁን፣ ከኢንቨስትመንት መዳረሻዎች መካከል አንዷ የሆነችውን የደብረ ብርሃን ከተማን የኢንቨስትመንት አቅምና እንቅስቃሴዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ማስተዋወቅ እንደሚያስፈልግ አስታውቀዋል።

ከተማዋ ያገኘችውን የኢንቨስትመንት እድል ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር ደብረ ብርሃን ለአማራ ክልል ብቻም ሳይሆን ለኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ዘርፍና ምጣኔ ሀብታዊ እድገት አስተዋፅኦ እንድታበረክት እንፈልጋለን ያሉት አቶ ከሳሁን፣ በኢንቨስትመንት የተገኙ ልምዶችን ለማስፋትና ለማጠናከር የሚያግዝ አቅም ይፈጥራል ተብሎ የሚጠበቀው ኤክስፖው በዚህ መነሻ የተቃኘ መሆኑን ይገልፃሉ።

የደብረ ብርሃን ከተማ የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መምሪያ ኃላፊ አቶ ብርሃን ገብረሕይወት በበኩላቸው፣ ኤክስፖው የደብረ ብርሃን ከተማን የኢንቨስትመንት አቅም በማስተዋወቅ ተጨማሪ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ እንደሚያግዝ ጠቁመው፣ ኤክስፖው የከተማዋን የኢንቨስትመንት ፍሰት ለማሳደግ ያግዛሉ ተብለው የተለዩ የትኩረት አቅጣጫዎችን መሰረት በማድረግ እንደሚከናወን ያብራራሉ።

ትልልቅ የካፒታል አቅም ያላቸውንና ብዙ የሥራ እድል መፍጠር የሚችሉ ባለሀብቶችን መሳብ፣ የአካባቢውን ጥሬ እቃ የሚጠቀሙ አምራቾችንና የኢንቨስትመንት ዘርፎችን ማበረታታት፣ ኤክስፖርት መር የሆነ የኢንቨስትመንት ስራን ማሳካት፣ የተሻለ ቴክኖሎጂ ያላቸው ፕሮጀክቶች ወደ ኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ ማገዝ እና የስራ እድል ፈጠራን በማሳደግ ድህነትን መቅረፍ የኢንቨስትመንት ዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎችና መመሪያዎች ናቸው ይላሉ። ኤክስፖውም እነዚህን የትኩረት አቅጣጫዎች ታሳቢ በማድረግ የደብረ ብርሃን የኢንቨስትመንት አቅም የሚተዋወቅበትና ተጨማሪ ኢንቨስትመንት ወደ ከተማዋና አካባቢው እንዲመጣ የሚደረግበት መድረክ እንደሚሆን ይጠቁማሉ።

«በኤክስፖው ላይ እንደሚሳተፉ ከሚጠበቁት ኢንቨስተሮች መካከል በማምረቻ፣ በግብርናና በአገልግሎት ዘርፎች የተሰማሩ ባለሀብቶች፣ የፋይናንስ ተቋማት፣ ከጥቃቅንና አነስተኛ ሽግግር ያደረጉ ኢንተርፕራይዞች፣ ወጣት ስራ ፈጣሪዎችና የምርምር ተቋማት ይገኙበታል። ተጨማሪ ባለሀብቶች ወደ አካባቢ እንዲመጡ፣ በተለያዩ ሙያዎች ተመርቀው ወደ ስራ ያልገቡ ወጣቶች ከስራ ፈጣሪዎቹ ልምድ እንዲያገኙ፣ የጥሬ እቃ መገኛዎች ከአምራች ፋብሪካዎች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ የሚያግዙ የልምድ ልውጦችና ውይይቶች ይደረጋሉ» ብለዋል።

### የደብረ ብርሃን ዝግጅት

ይህን መሰል ትልቅ የኢንቨስትመንት፣ የንግድና የፋይናንስ ኤክስፖ ለማዘጋጀት ሲታሰብ ተሳታፊዎችን ለማስተናገድ የሚያስችሉ የመሰረተ ልማትና የቢሮክራሲ ዝግጅቶችን ማድረግ እንደሚገባ የታወቀ ነው። ከዚህ አንፃር ደብረ ብርሃን «ደብረ ብርሃን ኤክስፖ 2023»ን በብቃት ለማስተናገድ የሚያስችሏትን ዝግጅቶች እያደረገች እንደምትገኝ ተገልጿል።

አቶ ካሣሁን፣ ለኤክስፖው እስካሁን ከተደረጉት ዝግጅቶች በተጨማሪ፣ በቀጣይ ጊዜያትም በከተማዋም ሆነ በክልሉ አቅም የሚሟሉ የመሰረተ ልማት እጥረቶችን ለመፍታት እየተሰራ እንደሆነ ገልፀዋል። ሰላምና ፀጥታን ለማስጠበቅ በሚከናወኑ ተግባሮች ላይም ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እንደሚሰራም ተናግረዋል። ከዚህ በተጨማሪም፣ «ለዚህ ኤክስፖ እንቅፋት የሚሆኑ የመሰረተ ልማት እጥረቶች አሉ ብለን አናምንም» በማለት ደብረ ብርሃን ትልቁን ኹነት ለማስተናገድ ያላትን ዝግጁነት አረጋግጠዋል።

አቶ ብርሃን ገብረሕይወትም፣ ኤክስፖውን ለማስተናገድ ልዩ ልዩ ዝግጅቶች እየተደረጉ መሆናቸውን ይናገራሉ። «ኤክስፖውን ለማዘጋጀት የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ትኩረት ሰጥተን ስንሰራ ቆይተናል። በከተማ ጽዳት፣ በሆቴል አገልግሎትና በሌሎች የመሰረተ ልማቶች ዝግጅቶች ተጨማሪ የመሰረተ ልማት ክፍተቶች በሚታዩባቸው አካባቢዎችና ዘርፎች ያሉ ጉድለቶችን ለማስተካከል እየተሰራ ነው ሲሉ ያብራራሉ። «በአጠቃላይ ኤክስፖውን ውጤታማ በሆነ መልኩ በማከናወን ባለሀብቶች ወደ ደብረ ብርሃን እንዲመጡ፣ ማኅበረሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆንና ሀገራዊ ምጣኔ ሀብቱ እንዲነቃቃ የሚያስችል ተግባር ለማከናወን ትልቅ ጥረት ይደረጋል» በማለት ደብረ ብርሃን ለኤክስፖው እያደረገችው ያለውን ዝግጅት ያስረዳሉ።

# ጎሜ

# ‹‹ ሳይቸግር ጤፍ ብድር››

**ምሕረት ሞገስ**

‹‹ በአዲስ ዓመት ምርጥ ምርጥ ምግቦችን እና መጠጦችን በአዲስ መልክ ጀምረናል። ›› የሚለው የመጠጥ ቤቱ ማስታወቂያ ዘውዴን አስገርሞታል። ዘውዴ መታፈሪያ ወደ መጠጥ ቤቱ ሲገባ ለራሱ ‹‹ ኑሮ የተወደደው እኔ ላይ ብቻ ይሆን እንዴ ?›› ሲል ጠየቀ። ደገመና ‹‹ እንዴት እንዲህ ኑሮ እየተወደደ በአዲስ መልክ ምግብና መጠጥ መነገድ ይጀመራል? ›› በማለት አጉረመረመ።

ተሰማ መንግስቴና ገብረየስ ገብረማሪያም ግን ዘውዴን ያሳሰበው ጉዳይ እነርሱን አላሳሰባቸውም። እንደውም የኑሮ መወደድ ጉዳይ ሃሳባቸው ላይ አልመጣም። ሰው የሚያየውም ሆነ የሚያዳምጠው የሚፈልገውን ብቻ በመሆኑ ‹‹ በአዲስ ዓመት ምርጥ ምርጥ ምግቦችን እና መጠጦችን በአዲስ መልክ ጀምረናል። ›› የሚለው የመጠጥ ቤቱ ማስታወቂያን ጭራሽ አላዩትም። ስለዚህ እነተሰማ የዘውዴ ዓብይ ጉዳይ ለእነርሱ ተራ ነው። ከኑሮ መወደድ ይልቅ እነርሱ ‹‹የመከላከያ ሠራዊት በወሰደው እርምጃ የሽብር ቡድኑ ታጣቂዎች በሁሉም ግንባር እጅ እየሰጡ፤ እየተበተኑ ነው። ፈርጠጠው በረሀ እየገቡ ነው›› የሚለው ዜና አስደንቋቸዋል፤ እንዲሁም አስደስቷቸዋል። ምክንያቱም ጦርነት ባህላዊ ጨዋታው ከሆነ ቡድን ይህ አይጠበቅማ!

ገብረየስ ከትህነግ ሽንፈት ባሻገር የኢትዮጵያ መንግስት እና ትህነግ ለመጀመሪያ ጊዜ ፊት ለፊት የተገናኙበት የሰላም ንግግር ደቡብ አፍሪካ ላይ መጀመሩ አስፈንጥዞታል። ገብረየስ እርሱ በደስታ ሰምጦ ዘውዴ አኩሩፎ ሲያየው በጥቂቱ ገረመው። ለዘውዴ ጥያቄ አቀረበ። ‹‹ ምነው ብቻህን ስብሰባ ገባህ ? ›› አለው። መተከዙ ፤ዝምታን መምረጡ ስላላስደሰተው። ዘውዴም ‹‹ ያልተነካ ግልግል ያውቃል፤ እናንተማ ምንም የሚያስጨንቃችሁ ነገር ...። ›› ብሎ ንግግሩን እንኳን ሳይቋጭ ። ለምን አንጨነቅም ሁሉም እኮ የሀገር ጉዳይ ነው ! ብሎ ገብረየስ በስጨት ሲል ተሰማ በመሃል ገብቶ ‹‹ ምን ማለትህ ነው? እያለቀ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ እኮ ነው። ›› ሲል ዘውዴን ለመገሰፅ ሞከረ።

‹‹እናንተ! እናንተም አለቅን ትላላችሁ? እኔ እና እንደኔ አይነቱ ይለቅ እንጂ እናንተማ በደህና ጊዜ አጭዳችሁ ጎተራችሁን ሞልታችኋል። ኪሳችሁ አያጣም። ›› ሲል ዘውዴ መለሰ። በዚህ ጊዜ ገብረየስ ተበሳጨ ‹‹ምን ማለት ነው? ወዶ አይደለም ሰውየው ‹ ባልፈጨሁ በንኖብኝ ባላደረግኩት ተመካኘብኝ› ያለው፤ ምንም ባልፈፀምኩት ነገር ትወቅሰኛለህ። በግልፅ ስትዘርፍ ኖረሃል ለምን አትልም? ብዘርፍማ ኖሮ ቤት ተከራይቼ አልኖርም ነበር። ህንፃ ገንብቼ የፎቅ አከራይ እሆን ነበር። አሁንም የምኖረው ደልቶኝ ሳይሆን ብዙ ነገር ጎድሎብኝ ለፍቼ ሰርቼ ነው። ሌላው ቀርቶ ሰላም በሆነና ጎተራዬ በነጠፈ፤ ›› እያለ ዘውዴ እርሱና ተሰማ ላይ የሰጠው አስተያየት ትክክል አለመሆኑን ቃላቶቹን እየደጋገመ ተናገረ።ከፊቱ አንዴ ጎንበስ ሌላጊዜ ደግሞ ቀና እያለ።

ዘውዴ፤ ገብረየስ መበሳጨቱን አይቶ ወደኋላ አላለም፤ የእርሱም ስሜት ቀላል አልነበረም፤ ግለቱን ጨምሯል፤ ‹‹ ነገሩ ‹ሳይርበው የሚበላ ርሃብን አያውቅም› ይባል አይደል? ችግር የማያውቅ ሰው ለተቸገረ አያዝንም፤ ርቧችሁ ስለማታውቁ ለተራበ አታዝኑም። ደግነቱ እኛም አይከፋንም። ጥጋባችሁን በሙሉ ችለን ተሸክመናችሁ እንኖራለን፤›› ሲል ተሰማ ደሙ ፈላ እየተንቀጠቀጠ መናገር ጀመረ።

ተሰማ ‹‹ እኛ ላይ የሚያስቆጣህ ምንድን ነው? የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በወሰደው እርምጃ የትህነግ ታጣቂዎች ተበትነዋል፤ የታደሉት እጅ ሰጥተዋል። ሌሎች ደግሞ በተሳሳተ መረጃ ተደናግረው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ግራ ተጋብተዋል? ሲባል ከፋህ እንዴ? መቼም እስከ አሁን በተከታታይ ከአንተ ጋር ስናወራ ያለኝ መረጃ የጦርነት ዘመንን ማየት እንደሰለቸህ፤ ሕዝቡ ከጦርነት አረፍ የሚልበትን ጊዜ እንደናፈቅክ ስትገልፅ ነበር። አሁን ደግሞ ሰላም እንዲሰፍን ሊነጋገሩ ነው፤ ይሔንን አንተም ስትፈልገው የኖርከው ጉዳይ ነው። አሁን ምን አዲስ ነገር መጣ? ›› ብሎ ዘውዴ ላይ ሲያፈጥ ዘውዴ መታፈሪያ ተሸማቀቀ። እነርሱ የሚያስቡት እና እርሱ እያሰበ የሚናገርበት ርዕስ ጉዳይ ራሱ የተለያየ መሆኑን ተረዳ።

ዘውዴ ቀጠል አደረገና ላለመረታት ‹‹በእርግጥ እኔ እየተብሰከሰኩ ያለሁት በኑሮ ውድነት ነው። እኛ ስለምንጎርሰው እየተጨነቅን መጠጥ ቤቱ ‹በአዲስ መልክ ምግብና መጠጥ ጀምረናል› ማለቱ አናዶኛል። እንኳን አዲስ የመጣ መጠጥና በተለየ መልኩ የተሰራ ምግብ ገዝቶ መብላት ቀርቶ መንገድ ላይ የሚሸጥ ሙዝ ገዝቶ መብላት አቅቶናል። በሌላ በኩል ጦርነትና የኑሮ ውድነት ደግሞ ይገናኛል። ጦርነት አውዳሚ ነው። ስለዚህ ኢኮኖሚው ላይ ችግር ከፈጠሩ እና የዋጋ ግሽበት እንዲመጣ ካደረጉ ምክንያቶች መካከል ዋነኛው ጦርነት መኖሩ ነው።

ከጦርነት ውስጥ ዋናው መውጫ መንገድ ሰላም መሆኑ አይካድም፣ አሁን ደግሞ ጦርነቱ ሲያበቃ ሕዝብን ካማረሩ መሠረታዊ ጉዳዮች መካከል ዋነኛው የኑሮ ውድነት በአስቸኳይ መፍትሔ ሊበጅለት ይገባል። የኑሮ ውድነት ጉዳይ መፍትሔ ካልተበጀለት እና በጊዜ እርሱ ላይ ማተኮር ካልተቻለ፤ የሰሜኑ ጦርነት ቢያበቃም የመሃል አገሩ ጥያቄ፣ የኑሮ ውድነት ይሻሻል፤ መልካም አስተዳደር ይስፈን፣ ሙስና... የሚለው ያሰጋል።

አፍነዋለሁ ቢባል ደግሞ የሚቻል አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብ በነፃነቱና በእኩልነቱ ላይ ድርድር አያውቅም፤ አስተዋይ፣ ጨዋ፣ ታጋሽ፣ አገሩን ከልቡ የሚያፈቅርና ኩሩ ሕዝብ ነው። ነገር ግን የኑሮ ውድነቱ በዚሁ ከቀጠለ፤ ማጉረምረሙ አይቀርም፤ ገፍቶ ከወጣ ጥያቄ አታንሳ ተብሎ ከታፈነ አላስፈላጊ መስዋዕትነት እስከመክፈል እንደሚደርስ ከገብረየስ ዘመዶች መማር ይገባል። ›› ብሎ ፈገግ በማለት ውጥረቱን አረገበው።

ገብረየስ ‹‹ ዛሬ በደንብ ግራ ተጋብተህ ግራ እያጋባኸን ነው። ›› ብሎ በረዥሙ ተነፈሰ። ቀጠለና ‹‹ የኑሮ ውድነት፣ ጦርነት፣ ዕልቂት፣ መፈናቀልና ውድመት የሚያሳቅቀን እኛንም ጭምር ነው። ግለሰብ ባለሥልጣናት በሥልጣን ላይ እየባለጉ በሕዝብ ስም ሊነግዱ ይችላሉ። ይህ ቢያማርርህ ቢያሳዝንህ ተገቢ ነው። ነገር ግን እኛን ከእነርሱ ጋር ጨፍልቀህ እንደዘራፊ መግለፅህ ደስ አያሰኝም። አንዳንዴ ብትበሳጭም ንግግርህ ምን ያህል የሰዎች ስሜትን እንደሚጎዳ መገንዘብ አለብህ። በሌላ በኩል ከትህነግ ነን ባዮቹ ጋር የትግራይ ተወላጆች ተሰልፈው የተዋጉት አንዳንዶቹ በስርዓቱ ተጠቃሚ ስለነበሩ፤ አንዳንዶቹ ተታለው ሲሆን ብዙዎቹ ግን ተገደው ነው። ዘመዶችህ ላልከው ደግሞ እነርሱ የእኔ ብቻ ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያውያን ዘመዶች ናቸው›› አለው።

ዘውዴ ገብረየስ ማምረሩ ገባው። የበለጠ ማብራራት ፈለገና ‹‹ በአንድ መልኩ ጦርነት አለ ብሎ መሰለፍ የሚዋጉትን ማወቅና ማሸነፍ በጣም ጥሩ ነው። ነገር ግን የሕዝብ ምሬትና ለቅሶ ሲጥል እንጂ ሲቆርጥ አይታይም፤ የሚገዘግዘው ሳይታይ በድብቅ ነው። መጨረሻ ላይ ቆርጦ ሲጥል ለሁላችንም አደጋ አለው። ሳይርቅ በቅርብ ሳይደርቅ በርጥብ ብዬ ነው። አንድ ችግር ከማደጉ በፊት ወይም መጥፎ ደረጃ ከመድረሱ በፊት በቅርብ ማስተካከል ካልተቻለ አደጋው የከፋ ይሆናል። ለኔ የታየኝ ለእናንተ አልታያችሁም። የተበሳጨሁት ለዛ ነው። ሰው የሚያየው መቼም የቸገረውን ነው። ያው በገቢ ከእኔ መሻላችሁ የሚታይ ሃቅ በመሆኑ እንደኔ የኑሮ መወደድ ላያሳስባችሁ ይችላል። ›› ብሎ ፈገግ አለ።

ተሰማ በበኩሉ፤ ‹‹ ያልዘሩት አይበቅልም፤ ማንኛውም ነገር የአንድ የተፈፀመ ነገር ውጤት ነው። ከጣርክ ከለፋህ እንደኛ ብቻ ሳይሆን ከእኛም በላይ ገቢ ማግኘትህ አይቀርም። የራስህን ድክመትና ስህተት ሁሉንም ነገር ወደ መንግስት እና ወዳለውና ወደነበረው ስርዓት ካላከከው ችግሩ የእነርሱ ብቻ ሳይሆን የአንተም ጭምር ነው። ችግርን ወደ ውስጥም ማየት ጥሩ ነው። ሰው ከስህተቱ ይማራል አይደል የሚባለው፤ ደግሞ አንድ አባባል አለ ብልጥ ልጅ ከሰው ሞኝ ደግሞ ከራሱ ይማራል። አሁን ሁላችንም ከራሳችን የምንማረው ብዙ ነገር አለ ። ስለነርሱ ማሰብህን ትተህ ስለራስህና ስለቤተሰብህ ከጀርባህ ስላሉት ዘመዶችህ አስበህ ብትንቀሳቀስ አሁንም ቢሆን ገቢህ ያድጋል ብዬ አምናለሁ። ችግሩ

> ‹‹ በዚህ ሰዓት አስፈላጊ ቢሆንም እንኳን ሁሉንም ነገር አጥብቆ መሻት አይጠቅምም። ለጊዜው የሚያስፈልገን የሰላም ጉዳይ ነው። ሌላው ከዛ በኋላ ይደረስበታል። ሰላም ከሌለ ዳቦ ቢሞላ ማን የት ቦታ ሆኖ ሊበላው ብለህ፤ኢኮኖሚውም ሆነ ሌላ ሌላው በቅደም ተከተል ይደረስበታል፡፡ይህን አጠናቅቀን ፊታችንን ወደ ቀጣዩ ችግራችን...››

አንተ እኔ ዘውዴ ስለሆንክ የፈለገውን ያህል ብጥርም ምንም ነገር ማግኘት አልችልም ብለህ ራስህ ላይ ቆልፈሃል። ›› ብሎ ለመገሰፅ ሞከረ።

ዘውዴ ከት ብሎ ሳቀ፤ ቀጠለና ‹‹ ብልህን ሰው ለማሞኘት መሞከር ትዝብት ማትረፍ ነው። በእውነት እናንተ ከኔ የተሻለ ገቢ ያገኛችሁት ከእኔ በላይ ሰርታችሁ ነው? ይሔ በእውነት ያስቃል። እኔንስ ተዉኝ! በምግብና በነዳጅ ዋጋ ላይ የታየው ከፍተኛ ጭማሪ፣ እንደእናንተ አይነት አንዳንዱ ካልሆነ በቀር በመላው ኢትዮጵያውያን ኑሮ ላይ ያደረሰውን መቃወስ ለመረዳት መንገደኛ ጠይቆ ለማወቅ አያዳግትም፤ ወጣ ብሎ ማንንም መንገደኛን መጠየቅ ብቻ በቂ ነው። ትክክል ነው! ሰላም እጅግ ወሳኝ ነገር ነው። ነገር ግን ሰላም ብቻውን ዳቦ አይሆንም። በአሁኑ ጊዜ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚስተዋለው ችግር በደንብ ታስቦበት ካልተሔደ አደጋው ከሰላም መደፍረስ በላይ መሆኑን አትዘንጉ ለማለት ነው። ›› የተሰማውን ሀሳበ ሰነዘረ ።

ተሰማ በበኩሉ፤ ‹‹ ሳይቸግር ጤፍ ብድር እንደሚባለው በዚህ ሰዓት የሚያስፈልግ ነገር ቢሆንም እንኳን ሁሉንም ነገር አጥብቆ መሻት አይጠቅምም። ለጊዜው የሚያስፈልገን የሰላም ጉዳይ ነው። ሌላው ከዛ በኋላ ይደረስበታል። ሰላም ከሌላ ዳቦ ቢሞላ ማን የት ቦታ ሆኖ ሊበላው ብለህ ፤ኢኮኖሚውም ሆነ ሌላ ሌላው ሁሉ በቀደም ተከተል ይደረስበታል። ይህን አጠናቀን ፊታችንን ወደቀጣዩ ችግራችን ›› ሲል ዘውዴ ከተሰማ ከተል አድርጎ ‹‹ አንድ ችግር ከመድረሱ በፊት መጠንቀቅ፤ ከደረሰም ሳይባባስ ቀድሞ መከላከል እንጂ መዘናጋት ተገቢ አይመስለኝም። የምግብ ምርቶች፣ የግንባታ ቁሳቁሶች፣ ተሽከርካሪዎችና ሌሎችም አቅርቦቶች በተወሰኑ የተደራጁ ኃይሎች ቁጥጥር ሥር እንዳይውሉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። መንግሥት ገበያውን ለመቆጣጠር ዋጋ መወሰን ባይኖርበትም፣ የአቅርቦት ሰንሰለቱን መቆጣጠርና በየዘርፉ የትርፍ ህዳግ ምጣኔ ማውጣት አለበት። ምክንያቱም በእያንዳንዱ ጉዳያችን እጁን የሚሰድ ነጋዴ አለ። አየር አመጣሽ ትርፍ ብለው በዚህ ሰሞን እንኳ አታይም ከውጪ በሚገቡ የቅንጦት ሸቀጦች ላይ ወደ ሀገር ቤት እንዳይገባ እገዳ ተደረገ ሲባ ምድረ ነጋዴ በመደርደሪያው የሞላውን በየመጋዘኑ ያከማቸውን ሁሉ ከእጥፍ በላይ አናረው እኮ። ስለዚህ ነጋዴው ላይ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይገባል። ይህ አንደኛው መፍትሔ መሆኑን መስሪያ ቤት ውስጥ አንድ የኢኮኖሚክስ ምሩቅ የተናገረው ነው። በእርግጥ ሌሎችም የተለያዩ መፍትሔዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን የሚመለከታቸው መንግሥታዊ ተቋማት ድንገት እየተነሱ መደብር ማሸግ፣ መጋዘን ውስጥ ያሉ ሕጋዊ ዕቃዎችን እንደ ሕገወጥ ክምችት መውረስና በጥናት ላይ ያልተመሠረቱ ዕርምጃዎችን መውሰድ አያዋጣም። ስለዚህ አስቀድሞ በሳይንሳዊ ጥናት ላይ ተመስርቶ ለዚህ የዋጋ ግሽበት መላ ማዘጋጀት ዛሬ ነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም።


አንዳችም የገቢ ጭማሪ ሳይኖራቸው እንደ ሰደድ እሳት የሚንቀለቀለውን የኑሮ ውድነት መቋቋም የተሳናቸው ሰዎች ቁጥር ቀላል አይደለም። የምግብ፣ የቤት ኪራይ፣ የትራንስፖርት፣ የልጆች ትምህርትና ልብስ፣ እንዲሁም ሌሎች ተደራራቢ ወጪዎች ኑሮን እያከፉት ነው። የኢኮኖሚ ጠቢባንም ሆኑ የሌሎች ባለሙያዎች ዕገዛ ታክሎበት፣ ኢኮኖሚው ከገባበት ማጥ ውስጥ መውጣት ካልቻለ መጪው ጊዜ ከባድ ነው። ›› ብሎ ራሱን ነቀነቀ ።

ተሰማ በበኩሉ ‹‹ ትክክል ነው፤ ሳይቃጠል በቅጠል ማለትህን ማንም አይቃወምም፤ ነገር ግን የማያውቁትን ነገር አውቃለሁ ማለት ያስገምታል። መቸኮልም አይገባም። እኛ የኢኮኖሚ ባለሞያዎች አይደለንም። ስለኑሮ ውድነትም ሆነ ስለዋጋ ግሽበት እንዲሁም ስለኢኮኖሚው መቃወስ ምንም ማለት አንችልም። ምክንያቱም ሳይማሩ መተርጎም ዕባጭን ሳይበጡ እንደማከም ነው። ሃሳብ ለመስጠትም ትንሽም ቢሆን ማወቅን ይጠይቃል። ማማረርም፤ መቸኮልም አይገባም። ›› በማለት ምላሽ ሰጠ።

‹‹አሁን እንኳን ሰው ቤተሰቡን አጥቶ ያለዘር እየቀረ ባለበት በዚህ ጊዜ ስለኑሮ ውድነት ለመነጋገር ሌላ ሞራል ያስፈልጋል። በኑሮ ውድነት ተጎዳሁ ማለት ከባዱን ጉዳቱ ካለማየት የሚመነጭ ነው። ›› በማለት ገብረየስ ሲናገር ዘውዴ ተናደደ። ‹‹ ምንድን ነው? ‹በጦርነቱ የተጎዳሁት እኔ ብቻ ነኝ› አልክ እኮ! በጦርነቱ የተጎዳው መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው። ሰላሙም ሆነ የኢኮኖሚው ጉዳይ በአገር ዕጣ ፈንታ ላይ የሚኖራቸው ተፅዕኖ ተመሳሳይ ነው። በሰላም መደፍረስ ምክንያት ከሚደርሰው ዕልቂትና ውድመት በተጨማሪ፣ ሳይቀጠል በቅጠል ተብሎ ተከታታይነት ያላቸው ፈጣን እርምጃዎች ካልተወሰዱና ዘላቂ መፍትሔ ካልመጣ ወደፊትም ሰላም ይኖራል ብሎ ማሰብ ዘበት ነው። እኔ የኑሮ ውድነት የጠጣሁበትን ሂሳብ መክፈል እንዳልችል የገደበኝ በመሆኑ ክፈሉልኝ›› ብሎ ሲወጣ፤ ተሰማ እየሳቀ ‹‹ በቀን በቀን እየጠጣህ የሚልሰው ዳቦ እንዳጣ ድሃ ታለቃቅሳለህ። ›› ብሎ የጠጡበትን ሂሳብ ከፍሎ እጁን ኪሱ ከቶ ወደ ውጪ ወጣ።

# የሙዚቃ ታሪክ በኢትዮጵያ

ዋለልኝ አየለ




የቴሌቭዥን ቻናሎችን ስቀያይር የርቀት መቆጣጠሪያው ባላገሩ ቴሌቭዥን ላይ ጣለኝ። የባላገሩ መሥራችና ባለቤት አብርሃም ወልዴ የባላገሩ ተወዳዳሪዎችን የሆነ ካምፕ የሚመስል ቦታ ውስጥ ሰብስቦ ያስተምራል። አጋጣሚ ሆኖ ደግሞ ስለቅዱስ ያሬድ እያወራ ነው የደረስኩት። የቴሌቭዥኑን የርቀት መቆጣጠሪያ አስቀምጬ በተመስጦ ማድመጥ ጀመርኩ። ተወዳዳሪዎችን ወደ መዝናኛ ቦታ (ደብረ ዘይት ኩሪፍቱ ሪዞርት) ወስዶ ገለጻ እያደረገላቸው ነው።

ፕሮግራሙ ከጀመረ በኋላ ስለነበር የደረስኩበት ያለፈኝን ክፍል ለመስማት በጣም ጓጓሁ። የዩትዩብ ቻናላቸው ላይ ይጭኑት ይሆን? ብየ በስስት መፈለግ ጀመርኩ፤ ሁሉንም ክፍሎች አገኘኋቸው። ስለሙዚቃ ምንነትና ታሪክ እነሆ ከባለሙያው አፍ የሰማኋቸውን ማካፈል ፈለኩ።

ሙዚቃ የሚለው ቃል ሞዚክ((mousike) ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ነው። አጻጻፉቸው(Spelling) የተለያየ ሊሆን ቢችልም በላቲን እና እንግሊዘኛም ቃሉ ተመሳሳይ ነው። ጥንታዊ አመጣጡ ግን ሞዚክ ከሚለው የግሪክ ቃል ነው። ትርጉሙም የድምጽ ጥበብ ማለት ነው። ሀሳብን እና ስሜትን መግለጽ ማለት ነው።

ሙዚቃን አብርሃም ወልዴ በአማርኛ ሲያብራራው ‹‹የአዕምሮን ኬሚስትሪ የሚቀይር ኃይል›› ይለዋል።

ሙዚቃ ጥበብም ሳይንስም ነው። የሒሳብ ባለሙያዎች ይስማማሉ አይስማሙም የሚለው ክርክር እንዳለ ሆኖ ‹‹ሙዚቃ የሒሳብ አባት ነው›› ይባላል። ሳይንስ ነው ማለት ነው። የራሱ ስሌቶችና ቀመሮች አሉት። በልምድ ብቻ ዘፈን የሚችሉ ሰዎች ሙዚቃን ሲማሩ ግን ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ይከብዳቸዋል። በልማድ ግን ሙዚቃን ትምህርት አልሳካላቸው ያሉ ሰዎች የሚሰሩት ይመስላል፤ ግን ከባድ ሳይንስ ነው።

ሙዚቃ የሚሰራው ከድምጽ እና ከዝምታ (ፀጥታ) ነው። በሙዚቃ ውስጥ ዝምታ ከድምጽ እኩል ዋጋ አለው። በሙዚቃው መሃል ውስጥ ፀጥታው ባይኖር ረባሽ ድምጽ ነው የሚሆን።

ሙዚቃ መደበኛ እና ኢመደበኛ የሚባል አለው። መደበኛው፤ ቀደም ሲል በሸክላ እና በካሴት አሁን ደግሞ በሲዲ እና በተለያዩ ማጫወቻዎች በስቱዲዮ የተሰሩ መደበኛ ሙዚቃዎች ማለት ነው። ኢመደበኛ የሚባሉት ደግሞ በስሜት የምናንጎራጉረው ማለት ነው። በሰርግ እና በለቅሶ፣ እንዲሁም በተለያየ ሥራ ላይ ሆነን የሚዜሙት ማለት ነው። እነዚህ ዘፈኖች አንዳንድ ጊዜ በመደበኛ ዘፈኖች ሊዘፈኑ ይችላሉ። ለምሳሌ የእነ ፈረደ ጎላ፣ ሸሽግ ቸኮል፣ ንጋቷ ከልካይ፣ ካሳ ተሰማ፣ አሰፋ አባተ፣ ባህሩ ቃኜ የመሳሰሉት ዘፋኞች ከኢመደበኛ ዘፈኖች ተነስተው የዘፈኑ ናቸው። ኢመደበኛ ሙዚቃዎች በጭብጨባ የታጀቡ ነበሩ።

በመደበኛው ሙዚቃ ዘፈን የተጀመረው በእነ ጥላሁን ገሰሰ፣ መሀሙድ አህመድ፣ አስቴር አወቀ፣ ብዙነሽ በቀለ፣ አለማየሁ እሸቴ፣ ምኒልክ ወስናቸው.... የመሳሰሉት መደበኛ የሚባለውን የጀመሩ ናቸው።

አብርሃም እንደሚለው፤ መደበኛ የሚባለው ዘመናዊ (ኦርኬስትሬሽን) የተጀመረበት ስለሆነ ነው። ልጅ ሆነው ኢመደበኛውን ዘፍነው ይሆናል (የአሁን ወጣቶችም ኢመደበኛ ይዘፍናሉ)፤ ግን በአሁኑ የሙዚቃ ዓለም መደበኛ የሚባለው የኦርኬስትሬሽን ፎርም የያዘው ነው።

**ሙዚቃ ከምን ይሰራል?**

ከመሳሪያ አንፃር ሙዚቃ ከምን ይሰራል ከተባለ፤ ከክር፣ ከትንፋሽ እና ከምት ነው። የክር መስሪያ ማለት በንዝረት የሚመጣ ነው። መሳሪያዎቹም ከጅማት፣ ከጭራ(የፈረስ) እና ከሌሎች ንዝረት ከሚፈጥሩ ክሮች የሚሰራ ነው። ለምሳሌ፤ በገና፣ ክራር፣ መሰንቆ፣ ዲታ፣ ዱል፣ የመሳሰሉት ናቸው። ዲታ እና ዱል ጋምቤላ እና ሲዳማ አካባቢዎች የሚታወቁ ናቸው።

የትንፋሽ መሳሪያዎች ደግሞ ዋሽንት፣ እምቢልታ፣ መለከት፣ ድንኬ(ሲዳማ ውስጥ)፣ ፓሬረሳ፣ ሁራ፣ ሁልዱዱዋ፣ ጨቸዝያ (ጋሞ ውስጥ)፣ ዛክ(ከፋ)፣ ፋንፋ፣ አኮርዲዮን፣ የመሳሰሉት ናቸው።

የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች፤ ከበሮ፣ አታሞ፣ ነጋሪት፣ መቋሚያ፣ ጸናጽል፣ ቅል፣ ቻንቻ፣ የመሳሰሉት ይካተታሉ።

**ቅኝት (Scale)**

አራቱ የሙዚቃ ቅኝቶች በመባል የሚታወቁት፤ ትዝታ፣ ባቲ፣ አንቺ ሆዬ እና አምባሰል ናቸው። እነዚህ የቅኝት አይነቶች በእነዚህ ስያሜዎች የተጠሩበት ምክንያት ቅኝቶቹ ታዋቂ በሆኑባቸው ዘፈኖች ነው።

ትዝታ የሚባለው ቅኝት የትዝታ ዜማዎችን ስለሚይዝ በዚሁ ተሰየመ። ቅኝቱ መጀመሪያ ነው የመጣ፤ ያኔ ስም አልነበረውም። የትዝታ ስሜት ቀስቃሽ ሆኖ ሲገኝ ግን ትዝታ ተባለ። ባቲ ደግሞ ‹‹ባቲ›› በሚለው የጥንት ዘፈን ነው። አንቺ ሆዬም ‹‹አንቺ ሆዬ ለኔ›› በሚለው ዘፈን ነው። አምባሰልም ‹‹አምባሰል›› በሚለው ዘፈን ነው።

ከአራቱ የሙዚቃ ቅኝቶች በተጨማሪ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ‹‹መንዙማ ቅኝት›› የሚባል አምስተኛ ቅኝት ይሆናል እየተባለ ነው።

**ሙዚቃ እና ትምህርት (ቅዱስ ያሬድ)**

ዘመናዊ የሚባለው የሙዚቃ ትምህርት የውጭውን ዓለም መሰረት ያደረገ ነው። በተለይም ምዕራባውያን በሰፊው ሰርተውበታል። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ኢትዮጵያዊውን ቅዱስ ያሬድ ስሙን ማንሳት አይፈልጉም። ለእነርሱ የዓለም የሙዚቃ ጀማሪዎች እነ ሰባቲያን፣ ባክ፣ ቤትሆቨን ናቸው። እነዚህን ሰዎች የሙዚቃን ኖታ የጻፉ ናቸው በማለት ልክ እንደ ሙዚቃ ፈጣሪ ነው የሚተርኩላቸው።

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ስለኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ ምንም ማለት አይፈልጉም። የሚገርመው ግን እነዚህ የእነርሱ ሰዎች የተፈጠሩት ቅዱስ ያሬድ የሙዚቃ ኖታዎችን ከሠራ ከአንድ ሺህ 500 ዓመታት በኋላ ነው። የዓለም ስመ ገናና የሆነው ሞዛርት የተወለደው ከቅዱስ ያሬድ ከአንድ ሺህ 243 ዓመታት በኋላ በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን (1748 ዓ.ም) ነው። ቤትሆቨን የተወለደው ከቅዱስ ያሬድ አንድ ሺህ 258 ዓመታት በኋላ በ1763 ዓ.ም ነው።

አውሮፓውያን የዓለም የሙዚቃ ፈጣሪ በሚሏቸው እና በኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ መካከል በሺህ የሚቆጠሩ ዘመናት ልዩነት አለ። ስለቅዱስ ያሬድ ግን ምንም ማለት አይፈልጉም።

በነገራችን ላይ የአብርሃም ወለዴን ማብራሪያ እንደሰማሁ የኢትዮጵያን ሙዚቃ በተመለከተ በፈረንጆች የተሰሩ ጥናቶች ካሉ ብየ የበይነ መረቡን ዓለም ማሰስ ጀምሬ ነበር። ‹‹Some aspects of indigenous Ethiopian music, Ecclesiastical and Secular›› በሚል ርዕስ የተሰራ ጥናት አገኘሁ። የኢትዮጵያ ሙዚቃ መነሻው ከሃይማኖት ጋር የተገናኘ መሆኑን ይገልጻል። በነገራችን ላይ የእነ ሞዛርትም እንደዚሁ ነው፤ መነሻቸው ሃይማኖት ነበር።

በጥናቶቻቸው ላይ ግን የምንታዘበው ነገር በራሳቸው ዘመናዊ ሙዚቃዎች ነው የሚገልጹት። ክራሩን፣ ዋሽንቱን፣ ከበሮውን... በራሱ ከማብራራት ይልቅ ወደ እነርሱ ያጠጋጉና ከእነርሱ የተኮረጀ ለማስመሰል ይሞክራሉ። እውነታው ግን እነዚህ የኢትዮጵያ የባህል የሙዚቃ መሳሪያዎ ለሺህ ዘመናት የኖሩ እና ፈጣሪዎቻቸውም የአውሮፓን ዘመናዊ መሳሪያዎች የማያውቁ መሆናቸው ነው።

የፈረንጆችን ጥናቶች ትዝብት በሌላ ጽሑፍ የምመለስበት ይሆናል፤ አሁን ወደ አብረሃም ወልዴ ማብራሪያ ልሂድ።

በ505 ዓ.ም የተወለደው ቅዱስ ያሬድ የዜማ ምልክቶችን ፈጥሯል። የራሱ የሙዚቃ ኖት ሰርቷል። ሦስቱ የቅዱስ ያሬድ የዜማ ክፍሎች የሚባሉትም፤ ግዕዝ፣ ዕዝል እና አራራይ ናቸው።

የዜማ አይነቶች የሚባሉት ደግሞ፤ ድጓ፣ ጾም ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬ እና መዋስዕት ናቸው። ለእነዚህ ዜማዎችም ምልክቶች አሏቸው። የዜማ ምልክቶች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው።

ድፋት፣ ደረት፣ ቅናት፣ ጭረት፣ ርክርክ፣ ይዘት፣ ሂደት፣ ቁርጥ፣ ድርስ እና አንብር የሚባሉት ናቸው። የየራሳቸው ቅርጽ ያላቸው ምልክቶች አሏቸው። አንድ ዜመኛ እነዚያን ምልክቶች እያየ ዜማውን ምን ማድረግ እንዳለበት ያስባል ማለት ነው።

ከቅዱስ ያሬድ በፊት (ከ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ማለት ነው) የነበረ ሰው እስካልተገኘ ድረስ የዓለም የሙዚቃ ጀማሪ የሚሆነው ቅዱስ ያሬድ ነው። ግን ማንም አውሮፓዊ ይህ እንድሆን አይፈልግም። የብዙ ነገሮች መነሻና ጀማሪ እነርሱ እንደሆኑ ተደርጎ ነው የሚተረክ። ይህ የበላይነት ሞራል ደግሞ የምርም ጠቅሟቸዋል። በትርክት የጀመሩት የበላይነት የኢኮኖሚም የሥልጣኔም የበላይ እንድሆኑ እያደረጋቸው ነው።

ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ ብዙ ታዳጊ አገራት በራሳቸው የማይተማመኑ ሆነዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ ቅዱስ ያሬድ ማን እንደሆነ የማያውቅ ይኖራል፤ ይሄው ኢትዮጵያዊ ግን ስለእነ ሞዛርት እና ቤትሆቨን ሙሉ ታሪክ ሊነግረን ይችላል። እነ ሸሽግ ቸኮል፣ ንጋቷ ከልካይ፣ ካሳ ተሰማ፣ ጌታመሳይ አበበ..... የመሳሰሉት በአሁን ወጣቶች ብዙም የሚታወቁ አይደሉም፤ ከዚያ ይልቅ የምዕራባውያን ዘፋኞችን የቀለምና የምግብ ምርጫ ሁሉ ሳይቀር መተንተን እንደ ዘመናዊነት የሚያስቆጥር ሆኗል።

ይህ ሁሉ ለምን ሆነ ከተባለ ለራሳችን ዋጋ ስለማንሰጥ ነው። ምዕራባውያን ልጆቻቸውን የሚያስተምሩት

ሙዚቃ መደበኛ እና ኢመደበኛ የሚባል አለው። መደበኛው፤ ቀደም ሲል በሸክላ እና በካሴት አሁን ደግሞ በሲዲ እና በተለያዩ ማጫወቻዎች በስቱዲዮ የተሰሩ መደበኛ ሙዚቃዎች ማለት ነው። ኢመደበኛ የሚባሉት ደግሞ በስሜት የምናንጎራጉረው ማለት ነው

በጦርነት እና በድርቅ ጊዜ ከታዳጊ አገራት የሚያነሷቸውን ፎቶዎች በማሳየት ነው። ‹‹ተመልከቱ የእኛንና የእነርሱን ልዩነት›› እያሉ ነው። ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ፎቶ የሚያነሱት እና ዘጋቢ ፊልም የሚሰሩት ምን ላይ እንደሆነ ግልጽ ነው። የምዕራባውያን መገናኛ ብዙኃን የሳይንስ ሙዚየማችን ላይ ወይም ጎርጎራ ፕሮጀክት ላይ ዘጋቢ ፊልም ሊሰሩ አይችሉም።

የሙዚቃ እና ሌሎች የጥበብ ሥራዎቻችንም እንዲህ ነው በራሳችን ድክመት ዓለም አቀፍ ዝና እንዳያገኙ ያደርግናቸው። በቀጣይ እንዲያውም አስፈሪው ነገር የሙዚየም ታሪክ እንዳይሆኑ ነው። አንዳንድ የሬዲዮ ጣቢያዎች (ፋና እና ኤፍ ኤም አዲስ 97.1) ላይ ካልሆነ በስተቀር የድሮ ዘፈኖች ብዙም አይሰሙም።

አብርሃም እንደሚለው፤ የእነ ቅዱስ ያሬድ ሙዚቃ ጀማሪነት ከተነገረ እነ ቤትሆቨን ይደበዝዛሉ። ስለዚህ በተቻለ መጠን ‹‹ቅዱስ ያሬድ ደግሞ ማነው!›› እንድባል ነው የሚፈልጉት። ኢትዮጵያዊ የሆነ ነገር እንድጎላ አይፈለግም። የራሱ የአብርሃም ወለዴን ገጠመኝ እዚሁ ላይ ልጥቀስ።

ከአንድ የውጭ አገር መምህሩ ጋር ብዙ ጊዜ ይጨቃጨቅ ነበር። ድርሰት ጻፉ ተብሎ አብርሃም ስለ አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ መጻፍ ፈለገ። መምህሩ አልፈቀደለትም። ስለ ሉሲ ወይም ስለ ዓባይ መጻፍ ፈለገ። በእነርሱም ሊስማማ አልቻለም። ‹‹እነዚህ አንተ የምትፈጥራቸው ታሪኮች ናቸው፤ ማን ያውቃቸዋል? ስለሚታወቁ ነገሮች ጻፍ›› አለው። የሚታወቁ ማለት እንግዲህ የግድ ነጭ የሆነ ማለት ነው።

ይህ መምህር ከልጅነቱ ጀምሮ ያደገው የሌላ አገር ነገር ትንሽ እንደሆነ ተደርጎ ነው። ስነ ልቦናው ከራሳቸው ሰዎች ውጭ ያለውን አይቀልም። ስለዚህ ለራሳችን ክብር መስጠት አለብን።

የባህል ሙዚቃ አጀማመር፣ የዘመናዊ ሙዚቃ አጀማመር፣ የሙዚቃ ማህበራዊ ፋይዳዎች እና ለሙዚቃ መበላሸት ችግሮች የተባሉትን በዛሬው ዓምድ መጨረስ ስለማንችል ለሁለተኛ ክፍል የግድ ቀጠሮ ልንይዝ ነው። ሳምንት በክፍል ሁለት እንመለስበታለን። በተለይም ከባህላዊ ወደ ዘመናዊ በሚደረው ጉዞ ከክቡር ዘበኛ ወደ ማዕከላዊ ዕዝ፣ ከዕዞች ወደ ፖሊስ ኦርኬስትራ እና ባንዶች የነበረውን እንቅስቃሴ እንቃኛለን። እስከዚያ መልካም ሳምንት!

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## አክብሮትና ምስጋናን ለአረጋውያን

መልካምሥራ አፈወርቅ

የሰው ልጅ ወደዚህች ምድር ሲመጣ በተሰጠው ዕድሜና ጸጋ የራሱን ሂደት ተሻግሮ እንደሚያልፍ ዕሙን ነው ። በሕጻንነት ዕድሜው በወላጆቹ ዕቅፍ ሆኖ ከእሳትና ውሀው ይጠበቃል ። መሰናክልን ከዕንቅፋቶች አልፎም በታማኝ እጆች ስር እንደሆነ የማንነቱን ነፍስ ያውቃል።

ሕጻንነቱን ተሻግሮ ራሱን በወግ መለየት ሲጀምር ደግሞ ቀጣዩን የወጣትነት ዕድሜ ሊይዝ መንደርደሩ አይቀሬ ነው ። ይህ ዕድሜ እሳትና ውሀን በእኩል የሚያውቅበት፣ የቀጣይ ሕይወቱን ሚዛን የሚያስተካክልበት የሩጫ ዘመኑ ይሆናል።

በዚህ የወጣትነት እርከኑ ስለነገው የመኖር ህልሙን ይቀርፃል፣ ሰርቶ ደክሞ የማደርን ጥቅም ይለያል፣ ትዳር መስርቶ ቤተሰብ የሚመራበትን እውነት በተግባር ይከውናል። ይህን ዕድሜ በወጉ ለተጠቀሙት ደግሞ ከትናንትና ይበደሩበታል፣ የዛሬውን ይኖሩበታል፤ ስለነገም ጥብቅ መሰረት ይጥሉበታል።

ወጣትነት አልፎ ጉልምስና ሲጀምር ይህ ሰው በአካል ብቻ ሳይሆን በዕውቀት ጭምር ይበስላል። ከወጣትነቱ ያተረፈውን ዕድሜና ተሞክሮ አጋምዶ የተሻለ ዓለምን ሊፈጥር ቀጥ ባለው መስመር ሊያልፍ ይተጋል። ልጅነቱን ከወጣትነት ያጣመረበት ልምዱ በዚህ ዕድሜው በአብዛኛው ውጤቱን መልካም ያደርገዋል።

የጉልምስና ዘመን ተጠናቆ ቀጣዩ ምዕራፍ ሲተካ የሰው ልጅ አካል በዕድሜ ሸክም ይደክማል ፣ ዓይኖች በወጉ ሊያዩ ፣ ጆሮዎች በቅጡ ሊያዳምጡ ይሳናቸዋል፣ አዕምሮ እንደትናንቱ ላይሆን ከፍጥነቱ ይገደባል። እርጅና ወገብን እንዲሁም እግርን ይዞ አቅም ጉልበትን ይፈትናል።

የትናንቱ ብርታት ውስጥ አካልን ሲከድ ጤንነት በእጅጉ ይፈተናል ። ይህ ጊዜ በሕይወት ዑደት ጊዜን ጠብቆ ከማንነት ሲደርስ የዕድሜ ጠገብነት፣ የአረጋውያንነት ጸጋ ከነችግሩ ይወረሳል፣ ከነውበት ሞገሱ ከድካም ፣ ከጤና ማጣት ጥግ ያደርሳል። በዚህ ጊዜ ተመልካች ዓይኖች ፣ አጋዥና ደጋፊ እጆች ሊኖሩ ግድ ነው።

ብዙዎች ደጋግመን እንደምንለው የአረጋዊነት፣ የእርጅና ዘመን ዕድሜ ጸጋና በረከት ነው። በዕድሜ ማምሻ ላይ ቆሞ መገኘት ያለፉት ዓመታት የሕይወት አሻራዎች ማድመቅና ማስመሰከር ይሆናል። ይህን እውነት ጨምሮ በአረጋዊነት ዕድሜ በርካታ እሴቶችን ማትረፍ፣ ማትረፍረፍ ይቻላል።

የአረጋዊነት ዕድሜ ጸጋና በረከት የመሆኑን ያህል ለበርካቶች መከራና ችግር ሆኖ የሚያልፍበት አጋጣሚም ይስተዋላል። አፍሪካን በመሰሉ አህጉራት በዚህ ዕድሜ ላይ የሚገኙ አረጋውያን ያለጧሪና ደጋፊ ተንገላተው የማለፋቸው እውነት አዲስ አይደለም። ወደሀገራችን መለስ ስንል ጥቂት የማይባሉ የዕድሜ ባለጸጎች በመደገፊያ፣ በመጦሪያ ዕድሜያቸው ለችግር ተዳርገው የሰው እጅ ሲናፍቁ ማስተዋል ብርቅ አይደለም።

ጥቂት የማይባሉ አረጋውያን ረጅሙን ዘመን በሥራና ቤተሰብን በማስተዳደር ድካም አልፈው አካላቸው ሲደክም፣ ጤናቸው ሲጎድል አስታዋሽ፣ አልባሽ አጉራሽ አጥተው ለእንግልት ይዳረጋሉ። ትናንት አገር ወገናቸውን ያገለገሉበት አቅምና ጉልበት ከአጠገባቸው ሲርቅ ውለታቸውን የሚያስብ ፈጥኖ ደራሽ አጋዥ ከጥጋቸው አይገኝም። አብዛኞቹ ከዕድሜያቸው ጫፍ ሆነው የልጅ ልጆቻቸውን እንዲያሳድጉ ይገደዳሉ። ይህኔ እፎይታ የሚሻው ትካሻቸው ዳግም በሸክም ጎብጦ፣ በዕድሜና ሥራ ብዛት የጠወለገ ውስጠቸው ዘወትር ያለዕረፍት ይናውዛል።

በዚህ አጋጣሚ አብዛኞቹ አረጋውያን የመኖራቸውን፣ የእስትንፋቸውን መርዘም ፈጽሞ አይሹትም። የዕለት ሞታቸውን ይመኛሉ። በክብር የተራመዱትን ያለፈውን መንገድ ትዝታ አድርገው የቆሙበትን ሕይወት ይረግማሉ። ከዕድሜ መግፋት ጎን የሚከሰት ጤና ማጣት ለእነሱ የዘወትር ህመም ነውና የሕይወት ትግላቸውን ያብሰዋል። በዚህ ወቅት አረጋውያኑ አስታወሽ ወገን፣ ጧሪ ደጋፊ ከሌላቸው ሕይወታቸው የጨለማ ጉዞ ይሆናል።

ጥናቶች እንደሚጠቁሙት፤ በሀገራችን ከስድስት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን በላይ አረጋውያን ይገኛሉ። ከእነዚህ አረጋውያን መካከልም በርካቶቹ ለማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ ናቸው ። ከአረጋውያኑ መካከል ጥቂት የማይባሉት የማህበራዊ ዋስትና መድህን የሌላቸውና ጧሪና ተንከባካቢ ያጡ ናቸውም። እነዚህ ወገኖች ካለባቸው የኢኮኖሚ ችግር ሳቢያ የህክምና ደጃፍን የማያውቁ በመሆናቸው ጤናቸው በህመም የተፈነ ይሆናል።

በዘመነ ኮሮና አረጋውያን በበሽታና በርሀብ ሲፈተኑ ቆይተዋል። በርካቶች በመገለልና ራስን በመጠበቅ መስመር ላይ በነበሩበት አጋጣሚም ጧሪና ደጋፊ አጥተዋል። አስታዋሽም አልነበራቸውም። በአሁኑ ጊዜም በሀገራችን በተከሰተው የኑሮ ውድነት የተነሳ ብዞዎቹ በእጅጉ እየተጎዱ ነው። ኑሯቸውን የሚመጥን ገቢና ኢኮኖሚያቸውን የሚደግፍ አቅም በማጣታቸው በርካቶች ሕይወታቸውን የሚገፉት የሌሎችን እጅ በማየት ሆኗል።

የብዙዎቹ አረጋውያን ሕይወት ከእጅ ወደአፍ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ጥቂት የማይባሉት እጃቸውን ለልመና ዘርግተው የሰዎችን ምንዳ ይናፍቃሉ። ለእነዚህ ምስኪኖች እምብዛም የበረቱ ክንዶች፣ የነቁ ዓይኖች ያለመኖራቸው እውነትም በርካቶችን ከቤት ወደ ጎዳና እንዲወጡ አስገድዷል።

የአረጋውያን ዘረፈ ብዙ ችግሮች ዛሬ ላይ ከተለያዩ ስፍራዎች እንዲውሉ አድርጓል። የአብዛኞቹ ሕይወት በአንዳንድ በጎ ፈቃደኛ ወገኖች መስራችነት በተቋቋሙ ማዕከላት ጥላ ስር የተወሰነ ነው። እነዚህ ማዕከላት አረጋውያኑን በስነልቦና፣ በአካልና በኢኮኖሚ ጭምር ያግዛሉ፤ ጫናዎቻቸውንም ለማቅለል ይጥራሉ።

በእነዚህ ድርጅቶች ስር የሚገኙ የዕድሜ ባለጸጎች ፊት ለፊት ከሚታየው ገጽታቸው ባሻገር ያልተነበበው በጎ ማንነታቸው እንደተሸፈነ በሞት ይሸኛሉ። እነዚህ አረጋውያን ጥቂት የማይባሉት የእድሜ ዘመናቸውን ለሀገርና ወገናቸው ያዋሉ፣ ዕውቀትና ችሎታቸውን ለነበሩበት ትውልድ ያካፈሉ፣ድንቅ ዜጎች ናቸው።

እነኝህ ታላላቅ ሰዎች በዕድሜያቸው ማምሻ እርጅና ከህመም በፈተናቸው ጊዜ ትናንቱን የሀገር ባለውለታነታቸው ይዘነጋል። በመከበሪያና መመስገኛ ዕድሜያቸውም ተመጦ እንደሚጣል ሸንኮራ ይሆናሉ። አብዛኞቻችን እነሱን በታላቅነታቸው ከማክበር ይልቅ ፈጽሞ እንተዋቸዋለን። የህብረተሰቡ አንዱ አካል መሆናቸውን ረስተን ትኩረታችን በራሳችን ኑሮና ሕይወት ላይ ብቻ ይሆናል። የትውልድ ቅብብሎሽን ዕውን የሚያደርጉ አረጋውያን ክብርና ሞገስ እንደሚያሻቸው ቢታመንም ትኩረት የመነፈጉ እውነት የጉዳዩን ባለቤቶች ዋጋ እያስከፈለ ይገኛል።

በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ ስፍራዎች የተከፈቱ የምገባ ማዕከላት በልተው ለማያድሩ በርካታ ወገኖች የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። የማዕከላቱ መከፈት በተለይ ጧሪና ደጋፊ ለሌላቸው አቅመ ደካማ አረጋውያን ተስፋን አጭሯል።

በየዓመቱ በሀገራችን አረጋውያንን ምክንያት በማደረግ የምስጋና መርሀግብር ሲካሄድ ቆይቷል። በየዓመቱ በተለያዩ መሪ ቃሎች በሚከበረው የአረጋውያን ቀንም የግንዛቤ ማስጨበጫ መልዕክቶች በማድረስ ትኩረት ሁሉ ለሀገር ባለውለታዎቹ አረጋውያን እንዲሆን ጥረት ተደርጓል።

ዘንድሮ በጥቅምት ወር የመጀመሪያው ሳምንት የተከበረው 31ኛው የአረጋውያን ቀንም « የአረጋውያን ኢትዮጵያዊነት አሻራ፣ ለትውልድ አደራ» የሚል መልዕክትን አንግቧል። ዕለቱን በማክበር መርሀግብሩ ላይ የአረጋውያንን እግር የማጠብ ስነስርዓት የተካሄደ ሲሆን፤ ፕሬዝዳንት ሳህለ ወርቅ ዘውዴና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተገኝተው በዕለቱ ባለውለታ ለሆኑ አረጋውያን ምስጋና ተችሯል። እኛም እንዲህ እንላለን። « አክብሮትና ምስጋና ሁሉ ለአረጋውያን ይሁን» ።

# ዓለም አቀፍ

## በፕሬዝዳንት ባይደን ላይ ስጋትን የደቀነው የአሜሪካ ምክር ቤት ምርጫ ከሁለት ሳምንት በኋላ ይካሄዳል



በምክር ቤቱ ምርጫ ሪፐብሊካኖች አብላጫ መቀመጫዎችን ካገኙ ፕሬዝዳንት ባይደን ፈተና ይበዛባቸዋል ተብሏል። የአሜሪካ ምክር ቤት አባላት በየሁለት ዓመቱ ሲካሄድ ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ደግሞ በየአራት ዓመቱ ይካሄዳል። በዚህ መሰረትም የአሜሪካ ምክር ቤት ምርጫ ከሁለት ሳምንት በኋላ ይካሄዳል።

የአሜሪካ ዋነኛ የስልጣን ማዕከላት የሚባሉት የኮንግረስ እና ሴኔት ምክር ቤቶች ምርጫ በየሁለት ዓመቱ የሚካሄድ ሲሆን የዘንድሮው ምርጫ ከሁለት ሳምንት በኋላ እንደሚካሄድ ተገልጿል።የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ጆ ባይደን በምክር ቤቱ ምርጫ ሪፐብሊካኖች አብላጫ መቀመጫዎችን ካገኙ ፕሬዝዳንት ባይደን ፈተና ይበዛባቸዋል ተብሏል።

የአሜሪካ ዋነኛ የስልጣን ማዕከላት የሚባሉት የኮንግረስ እና ሴኔት ምክር ቤቶች ምርጫ በየሁለት ዓመቱ የሚካሄድ ሲሆን የዘንድሮው ምርጫ ከሁለት ሳምንት በኋላ እንደሚካሄድ ተገልጿል።435 መቀመጫ ያሉት የአሜሪካ ምክር ቤት ምርጫ ሪፐብሊካን እና ዲሞክራት ፓርቲዎች አንዱ በአንዱ ላይ ከ30 እስከ 40 መቀመጫዎችን በበላይነት ለመቆጣጠር ፍላጎት አላቸው ተብሏል።

የወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ጆ ባይደን ፓርቲ የሆነው ዲሞክራት ፓርቲ አሁን ላይ ከ435 መቀመጫዎች 220ዎቹን የተቆጣጠረ ሲሆን ከሁለት ሳምንት በኋላ በሚካሄደው የምክር ቤት ምርጫ አብላጫ ወንበሮች ሊወሰድባቸው እንደሚችል ተሰግቷል።

በአሁኑ ጊዜ 212 የምክር ቤት መቀመጫዎችን የተቆጣጠረው ተቀናቃኙ የሪፐብሊካን ፓርቲ በዚህ ምርጫ ላይ አብላጫ መቀመጫዎችን ከተቆጣጠረ ለፕሬዝዳንት ጆ ባይደን ፈተና ሊሆንባቸው እንደሚችል ሮይተርስ ዘግቧል።

ሪፐብሊካኖች ከሁለት ሳምንት በኋላ የሚካሄደውን የምክር ቤት ምርጫ አብላጫ መቀመጫዎችን ከተቆጣጠሩ በፕሬዝዳንት ጆ ባይደን ላይ ምርመራ እንዲጀመር እና ከስልጣን እንዲለቁ የሚያደርጉ ስራዎች ሊጀመሩ ይችላሉም ተብሏል።

ይሁንና ዲሞክራቶች በቀላሉ በሪፐብሊካኖች ብልጫ እንዲወሰድባቸው እንደማያደርጉ የተገለጸ ሲሆን በተለይም ከፍተኛ ፉክክር ሊደርግባቸው በሚችልባቸው እንደ ፔንሲልቫኒያ፣ ጆርጂያ፣ ዊንስኮንሲን እና ኔቫዳ ግዛቶች ላይ ያልተጠበቁ ውጤቶች ሊመዘገቡ እንደሚችሉ ተገልጿል።

የሩሲያ እና ዩክሬን ግጭት ያስከተላቸው ጉዳቶች፣ የጽንስ ማቋረጥ ህግ፣ የኑሮ ውድነት፣ የጦር መሳሪያ አዋጅ፣ የስደተኞች አዋጅ፣ የድንበር ቁጥጥር ፖሊሲ እና ሌሎች ጉዳዮች መራጮችን ያልተጠበቀ ውሳኔ እንዲወስኑ ሊያደርጋቸው ይችላል ተብሎ ተሰግቷል ሲል የዘገበው አል ዐይን ነው።



## በሱዳን ህዝባዊ ተቃውሞ ተቀሰቀሰ

የሱዳን ጦር የተቃውሞ ድምጽ ለማሰማት ወደ ፕሬዝዳንቱ ቤተ መንግሥት ሲያመሩ የነበሩ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ተቃዋሚዎችን በአስለቃሽ ጭስ በተነ።የአገሪቱን ዲሞክራሲያዊ ሽግግር የገታውን መፈንቅለ መንግሥት አንደኛ ዓመት በማስመልከት በመላ አገሪቱ ተቃውሞው እየተካሄደ ነው።

የጦር ኃይሉ አዛዥ አብደል ፋታህ አል-ቡርሃን ስልጣን ከያዙ ወዲህ በየሳምንቱ በሚባል ደረጃ የጸረ መፈንቅለ መንግሥት ሰልፎች ሲካሄዱ ቆይተዋል።የጸጥታ ኃይሎች ባለፈው ዓመት ከ100 በላይ ተቃዋሚዎችን ገድለዋል በሚል ይከሰሳሉ።ጦሩ ስልጣኑን መያዙ ለጋሾች ዕርዳታ እንዲያቋርጡ ያደረጋቸው ሲሆን ይህም የሱዳን ኢኮኖሚም እንዳይረጋጋ አድርጎታል ተብሏል።

ማክሰኞ ዕለት በአስር ሺህዎች የሚቆጠሩ ተቃዋሚዎች ወደ ጎዳና መውጣታቸውን ሮይተርስ የዜና ወኪል ዘግቧል።ተቃዋሚዎቹ ካርቱም ወደሚገኘው የፕሬዝዳንቱ ቤተ መንግሥት ሲያቀኑ የጸጥታ ኃይሎች ጣልቃ በመግባት አስለቃሽ ጪስ በመጠቀም ለመበተን ሞክረዋል።

ለቤተ መንግስቱ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ሲቀራቸው ጆንበር ከመጥለቋ በፊት ተቃዋሚዎቹ መበተናቸው ታውቋል።እስከ ምሽት 12 ሰዓት ድረስ የኢንተርኔት አገልግሎት መቋረጡን ኔትብሎክስ የተሰኘው ተቆጣጣሪ ቡድን አስታውቋል።በጸጥታ ኃይሎች መኪና ተገጭቶ ኡምዱሩማን ላይ አንድ ግለሰብ ሕይወቱ ማለፉን ተቃውሞን የሚደግፉ የሱዳን ዶክተሮች ማዕካለዊ ኮሚቴ አስታውቋል። ይህም በታቃውሞ ምክንያት የሞቱትን ሰዎች ቁጥር 119 አድርሶታል።

ከዓመት በኋላም የጦሩ አመራሮች ጠቅላይ ሚንስትር እስካሁን አልሾሙም። በ2019 ከስልጣን የወረዱት አማር አል-በሽር ደጋፊዎች ወደ ስልጣን መጥተዋል።አልበሽር ወደ ስልጣን ካመጣቸው መፈንቅለ መንግሥት እና ከዳርፉር ጦርነት ጋር በተያያዝ ጉዳያቸውን በእስር ቤት ሆነው እየተከታተሉ ነው።

መንግሥት ሲቋቋም ስልጣናቸውን እንደሚያስረክቡ የገለጹት የጦሩ አመራሮች 'ፎርስስ አፍ ፍሪደም ቼንጅ' ከተባለው እና ከመፈንቅለ መንግሥቱ በፊት ስልጣን ከሚጋራው ጥምረት ጋር ውይይት እያደረጉ ነው። ብዙ ተቃዋሚዎች ውይይቱን እንደማይቀበሉት ቢቢሲ ዘግቧል።

# ስፖርት



## ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በፍራንክፈርት ማራቶን ለድል ይጠበቃሉ

ቦጋለ አበበ

በዓለማችን ታላላቅ ከተሞች በየአመቱ ከሚካሄዱ የማራቶን ውድድሮች አንዱ የሆነው የፍራንክፈርት ማራቶን በመጪው እሁድ ይካሄዳል። በጀርመኗ ከተማ ፍራንክፈርት የሚካሄደው ይህ ውድድር በኮቪድ-19 ስጋት ባለፉት ሁለት አመታት ሳይካሄድ ቆይቶ ዘንድሮ ሲመለስ በርካታ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች እንደሚሳተፉ ታውቋል።

በወንዶች መካከል በሚካሄደው ውድድር ርቀቱን ከ2:10 በታች ማጠናቀቅ የቻሉ ዘጠኝ አትሌቶች ጠንካራ ፉክክር እንደሚያደርጉ ይጠበቃል። በተመሳሳይ በሴቶች መካከል በሚካሄደው ፉክክርም ርቀቱን ከ2:25 በታች ማጠናቀቅ የቻሉ ስምንት አትሌቶች እንደሚሳተፉ የውድድሩ አዘጋጆች ገልጸዋል።

በወንዶች መካከል በሚካሄደው ፉክክር ሁለት ወጣት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የተለየ ብቃት እንደሚያሳዩ ተስፋ የተጣለባቸው ሲሆን፣ ፈጣን ሰዓት በሚመዘገብበት በዚህ ውድድር የቦታውን ክብረወሰን እንደሚያሻሽሉ ይጠበቃል። በተለይም የሃያ አራት አመቱ ኢትዮጵያዊ አትሌት በተስፋ ጌታሁን ማራቶንን ለመጀመሪያ ጊዜ በ2019 አምስተርዳም ላይ ሮጦ 2:05:28 የሆነ የራሱን ፈጣን ሰዓት ያስመዘገበ በመሆኑ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ችሏል። ይህ አትሌት በዘንድሮው የፍራንክፈርት ማራቶን ከሚሳተፉ አትሌቶች ሁሉ የመጀመሪያ ፈጣን ሰዓት ያለው ነው። ሁለተኛውን ፈጣን ሰዓት የያዘው ሌላኛው የሃያ ሁለት አመት አትሌት ገብሩ ረዳኸኝ በተመሳሳይ ባለፈው ግንቦት ባርሴሎና ላይ 2:05:58 ማስመዝገብ የቻለ ጠንካራ አትሌት በመሆኑ ትልቅ የአሸናፊነት ግምት ሊሰጠው ችሏል።

ሁለቱ ወጣት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በፍራንክፈርት አዲስ የማራቶን ታሪክ የመጻፍ ዕድላቸው ሰፊ እንደሆነ አዘጋጆቹ ያላቸውን እምነት ገልጸዋል። ከሁለቱ አትሌቶች በተጨማሪ በውድድሩ ሁለት ጊዜ ሁለተኛ ደረጃን ይዞ ያጠናቀቀው ኬንያዊው አትሌት ማርቲን ኮስጌ ጠንካራ ተፎካካሪ ከመሆን ባለፈ ለአሸናፊነት ግምት ከሚሰጣቸው ጠንካራ አትሌቶች ዋነኛው ነው። ይህ አትሌት በ2016 እና 2018 ሁለተኛ ሆኖ ማጠናቀቅ የቻለ ሲሆን 2017 ላይ ደግሞ አራተኛ ደረጃን ይዞ እንደጨረሰ ይታወቃል። በ2018 ውድድሩም ላይ 2:06:41 የሆነ የራሱን ፈጣን ሰዓት ማስመዝገብ ችሏል። ሌላው ኢትዮጵያዊ አትሌት ደሬሳ ኡልፋታ በ2:08:42 ሰዓት ጠንካራ ተፎካካሪ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል። አትሌት አሸናፊ ገብሩም የመጀመሪያውን የማራቶን ውድድር እንደሚያደርግ ታውቋል።

በሴቶች መካከል በሚካሄደው ውድድር ማራቶንን ከ2:25 በታች ማጠናቀቅ የቻሉ በርካታ አትሌቶች ሲሳተፉ የዘንድሮው ሁለተኛው ነው። ከዚህ ቀደም በ2018 አስር ያህል አትሌቶች ከ2:25 በታች ሰዓት ይዘው አስደናቂ ፉክክር አሳይተዋል። ዘንድሮ ደግሞ ስምንት ያህል አትሌቶች ይህን ሰዓት ይዘው የሚያደርጉት ፉክክር ተጠባቂ ነው። ኬንያዊቷ አትሌት ሳሊ ካፕቲች በቀዳሚነት የሚጠቀሰው 2:21:09 ሰዓት ያስመዘገበች ጠንካራ አትሌት ስትሆን ኢትዮጵያዊቷ አትሌት የሺ ቸኮል በ2:21:17 የሁለተኛው ፈጣን ሰዓት ባለቤት ሆና ብርቱ ፉክክር ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል። በተጨማሪም እኤአ በ2015 የቤጂንግ የዓለም ቻምፒዮና አሸናፊ የነበረችው ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ማሬ ዲባባን ተከትላ በሁለተኝነት ያጠናቀቀችው ኬንያዊቷ ሄላህ ኪፕሮፕ በ2:21:27 ሦስተኛውን ፈጣን ሰዓት ይዛ ትፎካከራለች። አታለል አንሙት፣ዝናሽ ለማና መሠረት አበባየሁ የተባሉ ኢትዮጵያውያን አትሌቶችም በውድድሩ ተፎካካሪ ይሆናሉ።

ለሰላሳ ዘጠነኛ ጊዜ በመጪው እሁድ በሚካሄደው የፍራንክፈርት ማራቶን ከአስራ ሁለት እስከ ሃያ ሺ ተሳታፊዎች የጀርመኗን ከተማ እንደሚያደምቁ ታውቋል።

«በኮሮና ወረርሽኝ ስጋት ከሁለት አመት ቆይታ በኋላ ውድድሩ ሲመለስ በማራቶን ጠንካራ አትሌቶችን አካቶ ነው፣ በሺዎች ለሚቆጠሩ ለተሳታፊዎችም ውድድሩ አስደናቂ ይሆናል፣ ያለፉት አመታት የውድድሩን ባህል በማስቀጠልም የፍራንክፈርት ማራቶንን ዳግም ታላቅ የማድረግ ጥረታችን ይቀጥላል» በማለት የውድድሩ ዳይሬክተር ጆ ሺንድለር ለመገናኛ ብዙኃን አስተያየት ሰጥተዋል።




በወንዶች መካከል በሚካሄደው ውድድር ርቀቱን ከ2:10 በታች ማጠናቀቅ የቻሉ ዘጠኝ አትሌቶች ጠንካራ ፉክክር እንደሚያደርጉ ይጠበቃል፣


## የጨረታ ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 የትምህረት ብልጭታ የመ/ደ/ት/ቤት ለ2015 ዓ.ም የበጀት አመት ለአገልግሎት የሚውሉ የፅዳት ዕቃዎች፣ የደንብ ልብስ ከነስፌቱ፣ ቋሚ እቃዎች፣ የስፖርት ትጥቅ፣ አላቂ የትምህርት ዕቃዎች፣ አላቂ የቢሮ እቃዎች፣ ልዩ ልዩ መሳሪያዎችን፣ አላቂ የህክምና እቃዎች፣ የህንፃ ጥገና፣ የፕላንት ማሽነሪ ጥገናና ሰርቪስ አወዳድሮ መግዛትና ማሰራት ይፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት በጨረታው መሳተፍ የምትፈልጉ ተጫራቾች የሚከተለውን ሁኔታ ማሟላትና ማቅረብ አለባችሁ፡፡

1.በአቅራቢነት የተመዘገቡበትን የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፣

2. ተጫራቾች በተሰማሩበት የንግድ ዘርፍ የዘመኑን ግብር የከፈሉና የታደስ ንግድ ፈቃድ ያላቸውና ዋናውን በማሳየት ኮፒውን ማያያዝ አለባቸው።

3.የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (ቲን ሰርተፊኬት) ያላቸውና ቫት ተመዝጋቢ የሆኑ።

4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 100.00/ አንድ መቶ ብር /በመክፈል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከፋይናንስ ቢሮ ቁጥር 6 በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡

5.ተጫራቾች ባሸነፏቸው ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች የሁለት አመት ዋስትና እና የተለያዩ የፕሪንተርና የፎቶ ኮፒ የማባዣ ቀለሞች የአንድ አመት ዋስትና መስጠት አለባቸው፡፡

6. ተጫራቾች ለሚያቀርቡት እቃ አይነት ናሙና ማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡

7. ተጫራቾች ያቀረቡትን አጠቃላይ ዋጋ 2% ፐርሰንት ያልበለጠ /በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ወይም ጥሬ ገንዘብ ማስያዝ አለባቸው፡፡

8. ተጫራቾች ያሸነፉበትን ዋጋ 10% በሲፒኦ ማስያዝ አለባቸው፡፡

9. በሚያቀርቡት ዋጋ VAT 15% ተሰልቶ መካተት ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ ግን VAT እንደተካተተበት ተደርጎ ይወሰዳል።

10. ተጫራቾች የገዙትን የጨረታ ሰነድ ኦሪጅናል ላይ ሞልተው በታሸገ ፖስታ ላይ ማህተም በማድረግ ከ1 ኮፒ ጋር በፋይናንስ ቢሮ ቁጥር 6 በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ማስገባት አለባቸው፡፡

11. የጨረታው ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10/አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት የሚቆይ ሲሆን በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰአት ተዘግቶ በእለቱ 4፡30 ሰዓት ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በመ/ቤቱ ፋይናንስ ቢሮ ቁጥር 6 ውስጥ ይከፈታል። ነገር ግን የመክፈቻው ቀን በዓል ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ይከፈታል፡፡

12. መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

13. መ/ቤቱ የሚጫረተውን እቃ ብዛት እንደ አስፈላጊነቱ 20% በመጨመር ወይም በመቀነስ ማዘዝ ይችላል።

14.ተጫራቾች ያሸነፉትን እቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት የጉልበት ወጪ በተቋሙ ቅጥር ግቢ በሚገኘው ንብረት ክፈል ማድረስ አለባቸው፡፡

15. ጨረታው ከተዘጋ በኋላ የሚመጣ የተጫራች ሰነድ ተቀባይነት የለውም።

ለበለጠ መረጃ፡-ስልክ ቁጥር 011 1 26 62 73/ 0111 58 57 06/

አድራሻ ፡- አዲስ አበባ ሬስቶራንት ወረድ ብሎ የአራዳ ክ/ከተማ ትምህርት ፅ/ቤት በወረዳ 05 የትምህርት ብልጭታ የመ/ደ/ት/ቤት

**በአራዳ ክ/ከተማ ወ/5 የት/ት ብልጭታ የመ/ደ/ት/ቤት**



## INVITATION FOR BID
## Bid No [LTLD/FECO/PO/NCB/NO 01/2022]

1. Lege Tafo Lege Dadi Town Administration Education and Municipality Office with their Budget need to Construct G+4 Lege Tafo Lege Dadi Administration Police Office Building.
2. Therefore Lege Tafo Lege Dadi Town Administration Finance and Economy Cooperative Office now invites all contractors of Category General Contractors or Building Contractors of Category of GC/BC-4 & Above.

**All of the bidders shall submit**

A. Renewed Certificate of registration in Contractors of Category from Ministry of Construction or from Oromia Construction Bureau for this budget year (2014 EC)
B. Renewed Trade License for this budget year (2014 EC)
C. Renewed Registration Trade Certificate for this budget year (2014 EC)
D. VAT Registration Certificate
E. TIN Certificate,
F. Tax clearance certificate valid during the bidding period from Federal Revenue and Custom Authority or Oromia Revenue and Custom Authority.
G. PPA's Suppliers registration list Certificate or full information about the bidder.

3. Bidding document shall be purchased at Lege Tafo Town Administration Finance and Economy Cooperative Office with non-returnable fee of Birr 500.00 (Five hundred Birr) starting from the date of announcement for 21 working days and hours, at Commercial Bank of Ethiopia 1000061739274.
4. All documents will be submitted according to guidelines given on instruction to bidders.
5. All bids Must be accompanied by a bid security in CPO or bank guarantee of Birr 500,000.00 (Five hundred Thousand) birr valid for 90 days after the date of bid opening, the bid security must be addressed "LTLD CITY ADM FIN ECO DEV" separately.
6. Submission and opening of the bid : The dead line of bid submission shall be on 22nd date of announcement from 2:30-4:00 local time, simultaneously it will be opened on the same date at 4:30 local time but if the 22nd date is holyday, or weekend it will be conducted on the next working day at Lege Tafo Lege Dadi Town Administration Finance and Economy Cooperation Office.
7. Lege Tafo Lege Dadi Town Administration Finance and Economy Cooperation Office Reserves the right to reject partially or all of these bids.
8. The successful bidder must give 20% subcontract for town administration Micro and Small Enterprise Construction.

**Address:** Lege Tafo Lege Dadi Town Administration Dessie Avenue 21 KM away from Addis Ababa

Telephone: +251-116-67-94-95, +251-910-22-22-57

**Lege Tafo Lege Dadi Town Administration Finance and Economy Cooperation Office**